መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ማዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ዮን ቅጽ 1 ቁጥር 43 የካቲት 2011 ዓ.ም ዋጋ 14.99




## የዘመናዊ ፖለቲካችን ፍኖተ ካርታ

አንዷለም አራጌ



## "የ 43 ዓመት ፖለቲከኞች ከ43 ዓመት ጎልማሳ ጋር"

## የዚያ ትውልድ እና የዐቢይ ፖለቲካ



## "የአንድነትና የዜግነት ፖለቲካ እንዲኖር ነው የምፈልገው"

ኢንጅነር ግደይ ዘረአጽዮን



## "የኢትዮጵያ ፖለቲካ የዝንጀሮ ፖለቲካ ነው"

"ኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠሏን አምኜ አላውቅም"

ፕ/ር ፍስሃጽዮን መንግሥቱ



## ሕወሓት እና ዛዲግ ለምን ተለያዩ

ዝርዝር ጉዳዩን ይዟል

# ግዮን


4 “የ 43 ዓመት ፖለቲከኞች ከ43 ዓመት ጎልማሳ ጋር” የዚያ ትውልድ እና የዐቢይ ፖለቲካ
መለክ ቢ.


7 የዘመናዊ ፖለቲካችን ፍኖተ ካርታ
አንዷለም አራጌ

8 ፍሬ አልባ ከሆነው የፓርቲዎች የውይይት አዙሪት መውጣት ይኖርብናል!

12 ከግጭቶች ጀርባ ያለው የሃይማኖት አጀንዳ
ተስፋዬ ሽብሩ

13 ዘመናችንን ዘካሪ ጨዋታዎች
በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

19 ከዘውግ ፌዴራሊዝም ጋር ያለው ግብግብ
መሐመድ ማምዳኒ






14 “የኢትዮጵያ ፖለቲካ የዝንጀሮ ፖለቲካ ነው”
“ኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠሏን አምኜ አላውቅም”
ፕ/ር ፍስሃጽዮን መንግሥቱ





2 ጫንቃዬ ሕወሐትን ከዚህ በላይ ሊሸከም አይችልም
አቶ ዛዲግ አብርሃ


9 “በትግራይና በአማራ የተፈጠረውን ግጭት የክልሉ አመራሮች ናቸው የወለዱት”
ኢንጅነር ግደይ ዘረአጽዮን

21 ከመንገዱም እንዳያስወጡን
ተመስገን ዘገየ

22 ባህማን

23 ታላቋ ኢራን ና የ1979 አብዮት

25 የጠቅላይ ሚኒስትሩ አስደንጋጩ የፓርላማ ሪፖርት
ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

28 ከተማ ይፍሩ ፓንአፍሪቃዊው ዲፕሎማት
ብሩክ መኮንን




ቁጥር 42 ዕትም

ግዮን

ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ የካቲት 09
ይጠብቁን!

# ጨንቃዩ ሕወሓትን ከዚህ በላይ ሊሸከም አይችልም



## አቶ ዛዲግ አብርሃ

በሚኒስትር ዲኤታ ማእረግ የዴሞክራታይዜሽን ማእከል አስተባባሪ በመሆን የሚያገለግሉት አቶ ዛዲግ አብርሃ ጫንቃዬ ሕወሓትን ከዚህ በላይ ሊሸከም አይችልም በማለት አምስት ገጽ የመልቀቂያ ደብዳቤ ለድርጅቱ ልዩ ዞን ጽ/ቤት ማስገባታቸው የሰሞኑ ርእሰ ጉዳይ መሆኑ የሚታወስ ነው፡፡ቀደም ሲል የኮምኒኬሽን ዲኤታ እና የፍትሕ እና የሕግ ሥርዓት ዋና ዳይሬክተር የነበሩት አቶ ዛዲግ አብርሃ አዲስ አባባ ለሚገኘው የሕወሓት ጽ/ቤት ባስገቡት የስንብት ደብዳቤ ከራያ ሕዝብ መውጣታቸው በጥርጣሬ ሲታዩ እንደቆዩ በማስታወስ ነው በይፋ ራሳቸውን እንዳገለሉ የገለጹት፡፡የእኚህ ከፍተኛ አመራር ከድርጅቱ መለየት የሕወሓትን ውድቀት ሊያፈጥን እንደሚችል አንዳንድ የፓለቲካ ታዛቢዎች ግምታቸውን ይሰነዝራሉ፡፡

የዛዲግ አብርሃ ደብዳቤ ይህን ይመስላል

ጥር 29, 2011

**ለ — ህወሐት ልዩ ዞን ጽ/ቤት**

**አዲስ አበባ**

ላለፉት አመታት በህወሓት ድርጅት ስር ተደራጅቼ እንቅስቃሴ ሳደርግ እንደቆየሁ ይታወቃል፡፡ ምንም እንኳን ከዚህ ቀደም በፖለቲካው መስክ የመሳተፍ ፍላጎቱ ያልነበረኝ ቢሆንም በታሪክ አጋጣሚ የአገራችንን ፖለቲካ የመቀላቀል ዕድሉን አግኝቻለሁ፡፡ በተፈጠረው አጋጣሚም ስለሃገሬ የፖለቲካ ምንነት እና በፖለቲካ ገበያው ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ግለሰቦችንና ተቋማትን በቅርበት የማወቅና የመሳተፍ እድሉ ገጥሞኛል፡፡ በዛው ልክ ደግሞ በህወሀት ውስጥ አደርግ በነበረው ትሳትፎ በር የመዘጋት የመጠራጠርና እንደ ባዳ የመታየት ስሜት ከላይ እስከ ታች ድረስ አጋጥሞኛል፡፡ ገና ከጅምሩ ትግሉ ድርብ ድርብርብ ነበር፡፡ በአንድ በኩል የመጣሁበት አካባቢ በክልሉ ፖለቲካ ውስጥ በዳርነት የሚመደብ ነውና አጠቃላይ ጉዞው እጅግ አቸጋሪ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ድርጅቱ ወጣቶችን የመጠራጠርና ያለማመን ከፍተኛ ችግር የተንሰራፋበት ነውና እኔም እንደማንኛውም ወጣት ጉዞዬ በሳንካ የተሞላ እንዲሆን አድርጎብኛል፡፡ ነገር ግን ሁሉንም በአንድ ሙቀጫ መውቀጥ ጥሩ አይደለምና በህይወቴ ነገሮችን በተለየ መልኩ እንዳይ ያደረጉኝ እንዲሁም ትምህርት የሰጡኝ ጥቂት ሰዎች ነበሩና በነሱ ድጋፍና ምክር በችግርም ውስጥ ቢሆን እስካሁን ድረስ ለመዝለቅ ችያለሁ፡፡

በእርግጥም! በሃገሬ ፖለቲካ ረጅም ርቀት ተጉዤ አስተዋጽኦ ላደርግበት የምችልና የሚገባ መሆኑን የማታ ማታ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ ይሁንና ገና ከማለዳው ጀምሮ በህወሓት ውስጥ የነበረኝ የፖለቲካ ተሳትፎ አልጋ በአልጋ አልነበረም፡፡ በአጭሩ በሴራና በአሜኬላ የተሞላ ነበር ብሎ መናገር ማጋነን አይሆንም፡፡ ሆኖም ችግር ሲመጣ መሸሽና ማፈግፈግ ሳይሆን ፊት ለፊት ተጋፍጦና ተፋልሞ ማሸነፍ እንደሚገባ ላስተማረኝ ለውድ አያቴ ለሃዋደ ሻረው አቢቱ አበራ እና በአጠቃላይ ለራያ ማኅበረሰብ ምስጋና ይግባውና ምርጫዬ “እግሬ አውጭኝ” ብሎ መሸሽ ሳይሆን አሜኬላውን መንቀልና ሴራውን ደግሞ ማፈራረስ ነበር፡፡

በአንፃራዊነት ከእድሜዬና ከቆይታየ አንፃር ሲታይ በእርግጥ እድገቴ ፈጣን ነበር ብሎ መናገር ይቻላል፡፡ ነገር ግን እድገቱ የመጣው በእኔ የስራ ፍላጎት እምነት ያላቸው የሌሎች ደርጅቶች የግንባሩ አመራሮች እየገፉና እየጠየቁ እንጅ በህወሓት በኩል እንደዛ አይነት ፍላጎት ስለነበረ አይደለም፡፡ እንዲያውም ቅናት ያደረባቸው አንዳንድ የህወሓት አመራሮች እድሉን ለማሰናከል ሲተጉ ተስተውለዋል ፡፡ አንዳንድ ግብዝ የዚሁ ድርጅት አመራሮች ተመልሰው የማይገኙ በትላልቅ የአሜሪካ ትምህርት ቤቶች የመማር የነፃ የትምህርት እድልን ሳይቀር ትቼ አገሬን ለማገልገል በመወሰኔ በስልጣን ፍላጎት ከሰውኛል፡፡ በየቢሮው እየዞሩ የስልጣን ያለህ እያሉ የሚውሉት እነዚህ ግለሰቦች ከስልጣን ሲነሱ ደግሞ እንደ ልጅ እያለቀሱ የሚማፀኑ ናቸው፡፡ ከሁሉም በላይ የሚያስገርመው ነገር ደግሞ እያንዳንዱን እንጥፍጣፊ ስልጣን ለግል ጥቅምና ዝና ያላንዳች ርህራሄ የሚያውሉትና ስልጣናቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ የስንቱን ምስኪን ህይወት የቀጠፉት እነዚህ ጨካኞች በግሌ ያገኘሁትን የነፃ የትምህርት እድልን መሰዋእት ያደረኩትን እኔን በስልጣን ፍላጎት ይከሳሉ፡፡

ይህን የመልቀቂያ ደብዳቤ እንዳዘጋጅና ከህወሓት ራሴን በፈቃዴ እንዳሰናብት በርካታ ገፊ ምክንያቶቼን እንደሚከተለው በዝርዝር የገለጽኩ ሲሆን የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ሊረዱት የሚገባ ትልቅ ቁም ነገር ቢኖር ድርጅቱን በይፋ ለቅቄ ከመውጣቴ በፊት እንዲስተካከል የምችለውን ሁሉ ጥረት ማድረጌን ነው፡፡

እስካሁን መልቀቂያ ሳላቀርብ የቆየሁበት ዋና ምክንያት ከዛሬ ነገ ወደ ማስተዋልና ካለፈው ተምረው በስህተታቸውም ተጸጽተው ነገሮችን ያስተካክሉ ይሆናል በማለት ለዚህም ጊዜ መስጠቱ መልካም ነው ብዬ በማሰብ ነበር፡፡ ነገር ግን ይህንን እንደማያደርጉና ምንም የሚለወጥ ስብዕና እንደሌላቸው የስካሁኑ አካሄዳቸው ግልጽ ስላደረገልኝ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ደርሻለሁ፡፡

በነዚህ ዓመታት በግሌ የምከተለውን አቋም እና የነበረኝን የትግል

ቀጣዩን በገጽ 24 ይመልከቱ

# የቀድሞ ጦር ሠራዊት አባላት ሕወሓት ያደረሰባቸውን በደል ገለጹ

*በተስፋዬ ሽብሩ*



የምስራቅ ጎጃም ዞን የቀድሞ ጦር ሠራዊት አባላት ጥር 19 ቀን 2011 ዓ.ም የምስረታ ጉባኤያቸውን አካሄዱ።የቀድሞ የሰራዊቱ አባላት ማኅበሩን ለማቋቋም የተነሳሱት በሶስት ምክንያቶች መሆኑንም የማኅበሩ የሥራ አስፈፃሚ አባል የሆኑት መቶ አለቃ ብርሃኑ ተረፈ ለግዮን መጽሔት ገልፀዋል። የሠራዊቱ አባላት ለ27 ዓመታት ከኢትዮጵያ የፖለቲካና ማኅበራዊ መድረክ ተገልለው የቆየ ሲሆን ለአገሩ የከፈለው የሕይወት መስዋዕትነት እና የአካል መጉደል ቦታ ሳያገኝ፤ የሚገባው ጥቅማ ጥቅምና ጡረታ ሳይከበርለት በመቆየቱ ለከፍተኛ ችግር እና መከራ ተዳርጎ መቆየቱን አስረድተዋል።

የማኅበሩ መመስረት ለቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ከፍተኛ ድል በመሆኑ አባላቱ እርካታ እንደተሰማቸው የተናገሩት መቶ አለቃ ብርሃኑ፤ አነሳሾቹ የምስራቅ ጎጃም የቀድሞ ሰራዊት አባላት ይሁን እንጂ ወደፊት ሌሎችንም የቀድሞ ሠራዊት አባላት በማካተት ማኅበሩን በአገር አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ ያለመ ነው ብለዋል።

ለአገር ዳር ድንበር መከበር የከፈለው የሕይወት እና የአካል መስዋዕትነት ተረስቶ፣ ሠራዊቱን የደርግ እና የመንግስቱ ኃይለማርያም ሰራዊት በማስመሰል፤ በሕዝብ ዘንድ ያለውን ከበሬታና ልዕልና በመናድ፤ ሕወሓት መራሹ መንግስት ከፍተኛ የሞራል ጉዳት ሠራዊቱ ላይ አድርሶበታል፤ በማለት የሰራዊቱ አባላት ባለፉት ዓመታት የተቀበለውን መከራ አስታውሰዋል ።


ኅብረተሰቡ ለቀድሞ ሠራዊት ያለው አመለካከት ሊቀየር እንደሚገባ፤ እንደ ጨፍጫፊ አካል መታየት እንደሌለበት የገለፀው ማኅበሩ ይልቁንም ለአገሩ በፈፀመው አኩሪ ተግባር ጥቅሞቹና ጡረታው ሊከበርለት እንደሚገባ የማኅበሩ የስራ አስፈፃሚ አባል የሆኑት መቶ አለቃ ብርሃኑ ጨምረው አብራርተዋል። የሠራዊቱ አባላት አንዲት ሉዓላዊት ሀገር እንድትኖር እና በዘር እና በጎሳ የተከፋፈለችውን አገር ለመርዳት ከለውጡ ኃይል ጋር አብሮ የመስራት ፍላጎት እንዳላቸውም አስገንዝበዋል።

በምስረታ ጉባኤው ላይ "የኢትዮጵያ ሠራዊት የመዘመን ባህሪው ከ1845 ደረስጌ መድኃኔ ዓለም - 1983 መባቻ" በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሁፍ በመቶ አለቃ ብርሃኑ ተረፈ ፤ ከሠራዊቱ ጋር የተያያዙ የቪዲዮ ቅንብሮች ታይተዋል።

በማኅበሩ ምስረታ ላይ የቀድሞ የሠራዊቱ አመራሮች ብ/ጄነራል ዋሲሁን ንጋቱ ፤ብ/ጄነራል ካሣዬ ጨመዳ እና ብ/ጄነራል አሰፋ አፍሮም የተገኙ ሲሆን ከሰሜን አሜሪካ ሻለቃ አበበ ይመኑ በክብር እንግድነት ተገኝተዋል። የምስራቅ ጎጃም አስተዳደር አስተዳዳሪ አቶ አብርሃም አለኸኝ፤ የዞኑ ፖሊስ ኮሚሽነርና የፀጥታ ኃላፊው ተገኝተዋል። ማኅበሩ በምስራቅ ጎጃም ዞን 20 ወረዳዎች የሚገኙ 7ሺህ የቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት አባላትን አካቷል።

# "የባከኑ ጭኖች" መጽሐፍ ሽያጭ ገቢ ለጌርጌሴኖን የአእምሮ ህሙማን መርጃ ይውላል

*በሔማስ ታፈረ*




የባከኑ ጭኖች በሚል ርዕስ በ228 ገጾች የተቀነበበው የግሩም ተ/ሃይማኖት መጽሐፍ የካቲት 4 ቀን 2011 ዓ.ም በሀገር ፍቅር ትንሿ አዳራሽ ከ11፡00 ሰዐት ጀምሮ ይመረቃል። የመጽሐፉ ጭብጥ ሴቶች በተለያዩ የአረብ ሀገራት በመሄድ የቤተሰቦቻቸውን ችግር ለመቅረፍ ሲሉ የራሳቸውን ሕይወት ሳይኖሩ የሚያቃጥሉትን የሕይወታቸውን ከንቱ እድሜ የሚያሳይ ነው።

መጽሐፉ በራሳቸው የሕይወት ምዕራፍ ውስጥ ለማለፍ ያልታደሉ ምስኪን እህቶች ታሪክ ሲሆን በተጨማሪም እነዚህ ሴቶች ከሻማም በላይ እንደሆኑ የመጽሐፉ ደራሲና የፍካት ኢትዮጵያ መስራች የሆኑት አቶ ግሩም ተ/ሀይማኖት ለመጽሔታችን ገልጸዋል ። የመጽሐፉ ሙሉ ገቢ ለጌርጌሴኖን የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል የሚውል ሲሆን ደራሲው ይህንን ለማድረግ ያነሳሳቸውን ምክንያት ሲያብራሩም በዚ ማዕከል ውስጥ የሚገኙት አብዛኞቹ የአእምሮ ህሙማን ከአረብ ሀገራት የመጡ መሆናቸው ነው ብለዋል።

እንዲሁም መንግስት ለዚህ ማእከል ለሕንፃ ግንባታ የሚሆን ቦታ እንደሰጠና ይህንንም በይፋ ለመረከብ አንዳንድ ሄደቶች እንደሚቀሩ ገልፀው፤ ከመጸሐፉ ሽያጭ የሚገኘው ገንዘብ ለህንፃ ግንባታው የሚውል እንደሆነ ተናግረዋል። በፕሮግራሙም ላይ የመቄዶንያ የአረጋውያንና የአእምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል መሥራች አቶ ቢኒያም፤ ታዋቂው ምሁር ዶክተር ዳኛቸው አሰፋ፤ ደራሲያን፤ የፍካት ኢትዮጵያ አባላት በእንግድነት ይገኛሉ።

# የድሬዳዋ ቀላል ፕሮጀክቶች ዕቅድ በ15 ቀናት ውስጥ ይፋ ይደረጋል

*በሔማስ ታፈረ*

የድሪዳዋ ቀላል ፕሮጀክቶችን ክንውን በ15 ቀናት ውስጥ ይፋ ለማድረግ መታቀዱን እና የሕዝቡን የዓመታት ጥያቄም በተቀላጠፈ መንገድ ምላሽ ለመስጠት የ60 ቀናት እቅድ መዘጋጀቱን የድሬዳዋ ከተማ ከንቲባ አቶ ኢብራሒም ዑስማን ተናገሩ።

የመልካም አስተዳደር እና የስራ አጥነት ጥያቄን በመፍታት፤ እንዲሁም የተጀመሩ ፕሮጀክቶችን በማጠናቀቅ፤ ለከተማዋ ነዋሪዎች የሚሆን ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት እንደሚሰራ ጠቁመው፣ በተለይ በየስፍራው የተገነቡ የመሸጫና የማምረቻ ቦታዎች ለወጣቶች እንደሚሰጡ ተናግረዋል።

የውይይት መርሃግብር እንደሚዘጋጅ እና ውይይቱ እንደ ከዚህ ቀደሞቹ ሕዝቡን ለማረጋጋት ብቻ ለይምሰል የሚደረግ ሳይሆን ጉዳዩን በዝርዝርና በጥልቀት በመመልከት ፈጣንና ዘለቄታዊ የሆነ መፍትሄ ለማምጣት የታለመ መሆኑን ኃላፊው ከመጽሔታችን ጋር በስልክ ባደረጉት ቆይታ ገልጸውልናል።

ሲጓተቱ የነበሩ ቀላል ፕሮጀክቶችን በተቻለ መጠን በ15 ቀን ውስጥ ለመፍታት እንዲሁም ከበድ ያሉትንና ጊዜ የሚወስዱትን ደግሞ በተገቢው መንገድ ድጋፍ በማድረግ መፍትሔ ማምጣት ዋነኛው እቅዳቸው መሆኑን አስታውቀዋል። አጠቃላይ ኅብረተሰቡ የሚያነሳቸው ችግሮች ተመርጠው እና ትኩረት ተደርጎባቸው ይሠራሉ ብለዋል።

# “የ 43 ዓመት ፖለቲከኞች ከ43 ዓመት ጎልማሳ ጋር”

## የዚያ ትውልድ እና የዐቢይ ፖለቲካ

**መለክ ቢ.**

የተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን አዳራሽ ምናልባትም በሁለት አስርተዓመታት የኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ አይቶት በማያውቀው አዲስ የፖለቲካ አጀንዳ ስብሰባ እየተካሄደበት ነው፡፡ በሁለት ጽንፎች ላይ ቆመው የጎሪጥ ሲተያዩ የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ መድረክ በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ እየተወያዩ ነው፡፡መድረኩ ላይ የተቀመጡትን ሰዎች ከስር የተቀመጠው ታዳሚ ያያቸዋል፡፡ ከመካከላቸው አዲስ ፊት የለም፡፡ አዳራሹ ዘመንን በሚያስታውሱና ዘመንም በማይዘነጋቸው አንጋፋ የፖለቲካ ሰዎች ተሞልቷል፡፡ ከነዚህ አራቱ ደግሞ ለእለቱ መወያያ የሚሆን ምልከታ እና የዳሰሳ ወረቀት አቅራቢዎች ናቸው ፡፡

### ከግራ ወደቀኝ

### አረጋዊ በርኼ (ዶ/ር) ፣

የዛሬ 44 ዓመት (በ1967 ዓ.ም) ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይን ከመሰረቱ ሰዎች አንዱ ናቸው፡፡ በዚህ አራት አስርተ ዓመታት ደፍኖ ወደአምስተኛው እየተንደረደረ ባለ የፖለቲካ ትግል ታሪካቸው ድርጅቱን ከመምራት ጀምሮ በመካከላቸው በተፈጠረ የአመለካከት እና ርዕዮት አለመግባባት ሳቢያ ድርጅቱን ለቅቀው እስከመውጣትና መሰደድ በደረሰ ታሪክ ውስጥ አልፈዋል፡፡ ለዶክትሬት ዲግሪያቸው በሰሩት የጥናት ጽሁፋቸው የህወሃትና የትግራይ ህዝብ የትግል ታሪክ ሲነሳ ጉልቶ ሁሌም የሚጠቀስ A Political history of the Tigray People’s Liberation Front 1975-1991 revolt, ideology and mobilization in Ethiopia በሚል ርዕስ የተጻፈ የታሪክ ሰነድ አኑረዋል፡፡  ዛሬ በአዲሱ የአብይ  አህመድ አስተዳደር ዘመን ከተሰደዱበት ተመልሰው ከ30 ዓመታት ወዲህ አይተውት በማያውቁት አዲስ አበባ ላይ ኖረው በሃገራቸው ውስጥ የጀመሩትን የፖለቲካ ትግል ለማስቀጠል የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ትዴት) ፓርቲን ከነኢንጂነር ግደይ ዘርዐጽዮን ጋር መስርተው በሊቀመንበርነት እየመሩ አሉ፡፡ዛሬም በዚህ አዲሱ የአብይ ዘመን ፖለቲካ ውስጥ ናቸው፡፡

### አቦ ሌንጮ ለታ ፣

በ1966 የኢትዮጵያ የተማሪዎች ንቅናቄ ገና ሲቆሰቆስና በንጉሱ ላይ የመጨረሻ ዘመን ተቃውሞ ሲነሳ መብላላት ሲጀምር አቦ ሌንጮ ለታ የኦነግ ምክትል ዋና ጸሃፊ ሆነው ተመረጡ፡፡ ከተመሰረተ ግማሽ ምዕተ ዓመት ያስቆጠረው የኦሮሞ ነጻነት ግንባርን ከመሰረቱ ሰዎች አንዱ ናቸው አቦ ሌንጮ፡፡ እስከፈረንጆቹ 1995 ድረስ በኦነግ ቆይተው በአመለካከት ልዩነት ሳቢያ ድርጅቱን ለቅቀው የወጡ እና በስደት ላይ እያሉም የኦሮሞ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኦዴግ) የሚባል ድርጅት አቋቁመው በፖለቲካ ትግሉ ጥርሳቸውን የነቀሉ ሰውም ናቸው፡፡ አሁን በተፈጠረውና ብዙዎች አካታች ነው በሚሉት የፖለቲካ ዘመን ስደት ላይ የነበሩት አቦ ሌንጮ ፓርቲያቸውን ይዘው በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ኢትዮጵያ ገብተዋል፡፡ ከኢህአዴጉ የኦሮሞ ዴሞክራቲክ ፓርቲ ጋር ውህደት ከፈጸሙ የኦሮሞ ፓርቲዎችም አንዱ ነው የርሳቸው ፓርቲ፡፡አቦ ሌንጮ በፖለቲካ ተሳትፎ ዘመናቸው ሶስት መንግስት ያዩ ነገር ግን ትግላቸው ለመንግስት አመራርነት ሊያበቃቸው ያልቻለ ጉምቱ የፖለቲካ ሰው ናቸው፡፡

### በየነ ጴጥሮስ (ፕሮፌሰር) ፣

በ1943 ዓ.ም ሃዲያ ውስጥ የተወለዱት የ68 ዓመቱ አዛውንት ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በባዮሎጂ ትምህርት ዘርፍ በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር እውቀት ከሸመቱ በኋላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዚሁ ዘርፍ ከሌክቸረር እስከፕሮፌሰርነት የዘለቀ አገልግሎት ያበረከቱ እና በማበርከት ላይ ያሉ ምሁር ናቸው፡፡ ፕሮፌሰር በየነ ወደፖለቲካ የተቀላቀሉት በ1983 ዓ.ም ኢህአዴግ ደርግን ጥሎ መንግስት የሆነ ወቅት ሲሆን አገዛዙ የትምህርት ሚኒስትር አድርጎ ሾሟቸውም ነበር፡፡ ስልጣናቸውን በገዛ ራሳቸው ከለቀቁ በኋላ በፖለቲካው መስክ በነበራቸው ንቁ ተሳትፎ ግንባር ቀደም የኢህአዴግ መንግስት ተቃዋሚ ሆነው ኖረዋል፡፡ ፕሮፈሰር በየነ ከአማራጭ ሃይሎች እስከ ደቡብ ህብረት ከዚያም ከሃዲያ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት እስከ ውሁዱ ፓርቲ መድረክ ሊቀመንበርነት አገልግለዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ሊቀመንበር ናቸው፡፡ ያለፉትን 28 ዓመታት ሙሉ በፖለቲካ ውስጥ የቆዩት ፕሮፌሰር በየነ አሁንም ንቁ ፖለቲከኛ ሆነው ቀጥለዋል፡፡

### ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር)

በ1950 የተወለዱትና የ61 ዓመቱ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ፖለቲካን የጀመሩት የተማሪዎች ንቅናቄ ዘመን አብቅቶ ኢህአፓ ሲመሰረት ፓርቲውን በመቀላቀል ነው፡፡ ከዚያ ዘመን ጀምሮ በፖለቲካው መስክ ተጠቃሽ አክቲቪስትና ምሁር ሆነው ከቆዩ በኋላ በ1990ዎቹ የቀስተደመና ፓርቲ መስራች ሆነው፣ ከዚያም ኢህአዴግን በብርቱ ተገዳድሮ አዲስ አበባ ላይ በዝረራ ያሸነፈውን ቅንጅት ለአንድነት እና ዴሞክራሲ ፓርቲን አዋቅረውና መርተው የአዲስ አበባ ከንቲባነትን ስልጣን እስከማግኘት ደርሰዋል፡፡ ከዚያም ▶

በስርዓቱ ታስረው ከተለቀቁ በኋላ በአሸባሪነት የተፈረጀውን ግንቦት 7 ፓርቲ አቋቁመው በአብይ ዘመን ወደሀገራቸው እስኪመለሱ ድረስ አስተዳደሩን በትጥቅ ትግል ጭምር ሲገዳደሩ ቆይተዋል። አሁንም በድጋሚ የዚሁ ፓርቲ ባለቤት ሆነው በሰላማዊ መንገድ ለመታገል ኢትዮጵያ ገብተዋል። በአዲሱ አስተዳደር ውስጥም በፖለቲካው የጠነከረ ተሳትፎ ላይ ናቸው።

## መረራ ጉዲና (ፕሮፌሰር)

50 ዓመታትን በደፈነው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል ውስጥ ተዋናይ የነበሩት መረራ ጉዲና ከአብዮቱ በኋላ መኢሶን የተባለውን ፓርቲ ተቀላቅለው በዚያ ትውልድ ፖለቲካ ውስጥ ብዙ ሰርተዋልም ኖረውበታልም። ፕሮፌሰር መረራ ከአካዳሚያዊ ተሳትፏቸው ባሻገር በፖለቲካው መስክ የነበራቸው የግማሽ ምዕተአመት ተሳትፎ አሁን ድረስ የዘለቀው የኦሮሞ ብሄራዊ ኮንግረስን መስራች እና ሊቀመንበር ሆነው ሲያገለግሉ ጭምር ነው። በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረትም እንዲሁ ሊቀመንበር ነበሩ። መድረክንም ሊቀመንበር ሆነው መርተውታል። የዘመኑን ፖለቲካ በግልጽ ንግግር በመተቸት እና ከብሄር ስሜት ወጥተው አንድነት ላይ በማትኮር የሚታወቁት መረራ ጉዲና እየታሰሩም እየተፈቱም ገና አፍላ ፖለቲከኛ በሚያስመስላቸው ቁመና ላይ ሆነው አባርሮ በመለሳቸው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፖለቲካን እያስተማሩ ነው። በቅርቡ ከዚሁ ዩኒቨርሲቲ የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ አግኝተዋል። አሁንም ይህንኑ ፓርቲያቸውን ይዘው ፖለቲካው ውስጥ በንቃት እየተሳተፉ አሉ።

የዶክተር አብይ አህመድ ተራ ሲደርስ በንግግራቸው መሃል ይህቺን ብዙ ሰው ያላስተዋላትን፣ ነገር ግን ብትዘረዘር መጽሃፍ የሚወጣው ታሪክ ያዘለች ሃረግ ጣል አደረጉ።

"43 ዓመት የታገለን ሰው 43 ዓመት የሆነው ሰው (በእጃቸው ወደርሳቸው እያመለከቱ) እየናቀው አብሮ መኖር አይቻልም"

## የዚያ ትውልድ ፖለቲካ

እነዚህ የ1960ዎቹ የፖለቲካ ትውልድ ቀሪ ምስክሮች የሆኑና ከ40 ዓመት በላይ በፖለቲካ ያገለገሉ ሰዎች ናቸው። ከ43 ዓመቱ ጎልማሳ አብይ አህመድ ጋር በአንድ መድረክ ላይ ተቀምጠው የተወያዩት። እነዚህ ሁሉ የያ ትውልድ አባላት ናቸው፣ ዛሬ ድረስ እየታገሉ ነው፣ መሃላቸው አንድም የዚህ ዘመን ሰው የለም፣ በነዚህ ሰዎች ፖለቲካ እና በ43 ዓመቱ አብይ አህመድ ፖለቲካ መካከል ያለው ርቀት የትየለሌ ቢሆንም ፣ ሰዎቹ ፖለቲካን አንደጥጥ አባዝተው የሚፈትሉ የሚባልላቸው አይነት ቢሆኑም፣ እነሆ የተከተሉት የፖለቲካ መስመር ይሁን በሃገሪቱ የነበረው አፋኝ ስርዓት አላንቀሳቅስ ብሏቸው ሃገርን ቀርቶ የእነርሱን አስተሳሰብ ተከትለው የተመሙትን ብዙዎች መለወጥ ሳይችሉ አሁን ድረስ አሉ። በዚህ ሳቢያም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ባለበት ቆሟል ብለው የሚከራከሩ ብዙ ናቸው።

ያም ሆኖ "በእናሸንፋለን እና እናቸንፋለን" የቃላት ልዩነት ጦርነት ገጥሞ የተንኮታኮተው የዛሬ 40 እና 50 ዓመት የፖለቲካ ትውልድ ዛሬም ድረስ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ መኖሩ ለብዙዎች እንግዳ ነው።በኢትዮጵያ ሰፍኖ ለኖረው የሴራ ፖለቲካ መሰረታዊ ምክንያቱ አንድም "የኔ ብቻ" እና "እኔ ያልኩት ብቻ" የሚል ግትር አስተሳሰብ ገዢ ሆኖ መቆየቱ ሲሆን በሌላ በኩልም ለሩሲያ የተሰራ እና ለኢትዮጵያ የማይገጥም የፖለቲካ ፕሮግራም ይዞ መውጣቱ ነው። በአጠቃላይ ማለት በሚቻል መልኩ ሶሻሊስት የሆነውና ሊበራሊዝምን በነፍሱ የሚጠየፈው የ60ዎቹ ፖለቲካ ኢትዮጵያን ወደአንድ አስተሳሰብ ለማቅረብ ሞክሮም አያውቅም፣ ራሱም ወደአንድ አስተሳሰብ መጥቶ አያውቅም።ከደርግ እስከ ኢህአዴግ ድረስ የሶሻሊዝም አቀንቃኝ ርዕዮት በኢትዮጵያ የነገሰበት ዋና ምክንያት ሁለቱንም ስርዓት የመሰረቱት የፖለቲካ ኤሊቶች የፈለቁት ከተማሪው ትግል ውስጥ በመሆኑ ነው።

ዓለምአቀፍ የግጭት አፈታት እና የእርቀሰላም ምሁሩ ፕሮፌሰር ህዝቅያስ አሰፋ እንደሚናገሩት የ1960ዎቹ ትውልድ የፖለቲካ ኩረጃ ሃገሩን የሚገነባለት ሳይሆን የሚያፈርስለትን መስመር ይዞ እንዲተም ምክንያት ሆኖታል።

" [የ1966ቱ ትውልድ] የቀደመውን የሌኒንን እና የስታሊን ፖለቲካ ህልዮት እንዳለ ቀድቶ ወደኢትዮጵያ አመጣ። የሩሲያ ችግር ለኢትዮጵያ ተሰጠ። ደግሞም ችግሩ ብቻ ሳይሆን ከነመፍትሄው። የኢትዮጵያ ጥያቄ የብሄር ጥያቄ ነው ተባለ። በዚህ ሳቢያም ማንኛውም ብሄር እስካልተስማማው ድረስ እስከመገንጠል የደረሰ መብት አለው ተባለ። ይህ ችግርም መፍትሄም ለኢትዮጵያ ተብሎ ያልተሰራ ነገር ግን በወቅቱ የነበረው ትውልድ ወድዶና አፈቅሮ የወሰደው ህልዮት ነው። ለኢትዮጵያ የማይጠቅም መሆኑ እስኪታይ ድረስ ግን ብዙ ደም ፈሰሰ፣ ጥፋትም ሆነ…. ነገር ግን እውን የኢትዮጵያ ጥያቄ የብሄር ጥያቄ ነውን? …በአጠቃላይ ግን አሁን ላለንበት ዘመን የኢትዮጵያ ፖለቲካ የ60ዎቹ ትውልድ ትልቅ አስተዋጽዖ ነበረው።"

የዚያ ትውልድ ትልቁ ችግር ቆም ብሎ ለመግባባት ሳይሆን ተሯሩጦ ለመጠፋፋት የፈጠነ መሆኑ ነበር። ለህዝቡ ለመቆም ሳይሆን ህዝቡን አውቅልሃለሁ ለማለት መፍጠኑ ነው። የራሱን ሰው በራሱ ይበላል። ራሱን በራሱ ያዳክማል። በዚህ ሳቢያም ይመስላል ኢትዮጵያ ውስጥ ራዕይ ያለውና ደህና መስመር ላይ ኖሮ የሁሉንም የህብረተሰብ ክፍል በሚያማክል አስተሳሰብ ሃገርን ለማገልገል የተነሳ እከሌ የሚባል ሰው የጠፋው።

እንዲያም ሆኖ ግን የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከደርግ እስከ ኢህአዴግ ድረስ [ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ወደስልጣን እስከመጡበት የዛሬ 10 ወር ድረስ] ይመራ የነበረው ከተመሳሳይ ሃሳብ በተቀዳ ነገር ግን በየራሱ መንገድ በተጓዘ የ60ዎቹ ትውልድ ፖለቲከኛ ነው። ኢህአዴግ በተለይም ህወሃት እና ብአዴን አመራሮቹ በሙሉ የዚሁ ትውልድ አባላቶች ናቸው። ይህን ፓርቲ በተቃውሞ ጎራ ቆሞ የሚሞግተው ሃይልም ይኸው ትውልድ ነበር። አሁንም በአብዛኛው በተለይም አመራር ጫፍ ላይ ያለው እሱው ነው።

## 43 ለ 43

አብይ አህመድ 43 ዓመቱ ነው። አንጋፋ የተፎካካሪ ፓርቲ አመራሮች ተብለው በጋራ ምክክር መድረኩ ላይ ጥናታዊ ዳሰሳ ያቀረቡት ፖለቲከኞች ደግሞ 43 ዓመት ማለት በፖለቲካ ህይወት ውስጥ የቆዩበት ዘመን ነው። የነርሱ ፖለቲካ ከጊዜው ጋር ሊዘምን እድል ቢኖረውም ሥነአእምሯዊ ዝግጅታቸው ግን በዚያ መጠን ለሊበራል አስተሳሰብ ክፍት ሆኗል ብሎ መናገር ግን አዳጋች ነው። ዴሞክራሲን ቢሰብኩም ዴሞክራሲያዊ ባህልን በተግባር ሲተረጉሙት አልታዩም። የሚመርጡት የትግል ስልት ሰላማዊ ቢሆንም ጀብደኞችም ናቸው። ህዝብን የሚያማክል አስተሳሰብ ሳይሆን በጥላቻ ፖለቲካ የታሸ እና በርስ በርስ መጠላለፍ የደረጀ ፖለቲካ ባለቤት ናቸው። ለጠላት የሚመች መከፋፈል ያላቸው፣ በመከፋፈላቸው ውስጥ መነጋገርን የማይወዱ እና ልዩነታቸውን አስፍተው በየራሳቸው መንገድ ለመጓዝ የማያመነቱ ናቸው። ይህ ባህሪ ላለፉት 40 ምናምን አመታት ሲጎዳቸውም ሲያጠፋቸውም ቆይቷል። ነገር ግን ያ ትውልድ የፖለቲካ ባህሉ በዚሁ የተቀየደ ስለሆነ በሃገር እና በህዝብ ላይ ያደረሰው ጉዳት አይታየውም።

እንዲህም ሆኖ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ ተቀራርቦ ስለመስራት እና ተወያይቶ ሃገር በሃሳብ ስለመምራት የተናገሩትን ብዙዎች ተቀብለው እየተጓዙ ያሉ ይመስላል።ተገናኝተው ለመነጋገር የፈጠሩትን እድል ተጠቅመውበትም የጋራ ውይይቶች ተካሂደዋል። ፓርቲዎቹ በተራቸው በራሳቸው አነሳሽነት መድረክ አዘጋጅተው "የሚበጀን ፖለቲካ የቱ ነው" የሚል አይነት ውይይት አካሂደዋል። ጠቅላይ ሚኒስትርር አብይ እንዳሉት እዚህ መካከል ከነዚህ የፖለቲካ ጉምቱዎች ጋር መሆን መማር ነው። ነገር ግን በሌላ በኩል መልካም ያልሆኑትንም ጎኖች መሸሽ እና መራቅም ግድ ነው።በዚህ መካከል መልካም ነገር ጎልቶ ወጥቶ ሃገርም በአዋቂ ልትመራ የምትችልበት እድል አለ። ለዚህም ነው የኢሲኤው ስብሰባ በብዙዎች ዘንድ ሊደጋገም የሚገባው የተንሻፈፈ ፖለቲካ አካሄዳችንን የሚያርቅ ውይይት ነው የተባለው።

## የአዲና አሮጌ ሃሳቦች ግጥሚያ

በዚህ ሰፊ የስብሰባ አዳራሽ ታዳሚ የሆኑት ወጣትና የዕድሜ ባለጸጋ የፖለቲካ ሰዎችና ምሁራን ፊት ለፊታቸው መድረኩ ላይ ተደርድረው የሚያዩዋቸው የፖለቲካ ልሂቃን በፖለቲካው ዓለም የሁለት ትውልድ አድሜ ያሳለፉ አንጋፋ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች በትግል እና በፖለቲካ ተሳትፎ በግራም ሆነ በቀኝ ከአራት አስርተ ዓመታት ዘለግ ያለ ተሳትፎ የነበራቸው ሰዎች ሲሆኑ በአንጻሩ በከፊል ፓርቲያቸው ኢህአዴግን፣ በአብዛኛው ደግሞ የግል የፖለቲካ ራዕያቸውን ወክለው በስፍራው የተገኙት ወጣቱ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ናቸው። የዕለቱ ውይይት ተፎካካሪዎች ከገዢው ፓርቲ ጋር ከማለት ይልቅ ተፎካካሪዎች ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር ያደረጉት ውይይት ነበር ለማለት ይቀላል።ውይይቱ መሰረት አድርጎ የተነሳው መድረኩ ላይ የተደረደሩት የፖለቲካ አመራሮች ባቀረቧቸው ወረቀቶች እና ለኢትዮጵያ ይበጃሉ ባሏቸው መንገዶች ላይ ነው።ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ በፖለቲካ ዓለም ከሁሉም ያነሰ የተሳትፎ ልምድ፣ በእድሜም ቢሆን ከሁሉም ያነሰ እድሜ ላይ የሚገኙ ትንሹ ፖለቲከኛ ናቸው። እርሳቸው ሳይወለዱ በፊት እና በተወለዱበት ዘመን አካባቢ ፖለቲካ የጀመሩት የዚያ ትውልድ አባላት

ናቸው ዛሬም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ቀዳሚ ተሰላፊ ሆነው በሃገሪቱ መጻኢ የፖለቲካ እድል ላይ ከወጣቱ ጠቅላይ ሚኒስተር አብይ አህመድ ጋር የሚወያዩት።የዕለቱ ታዳሚም የሚያስተውለው ይህንን የዘመን ልዩነት እና የአስተሳሰብ መጠን ነው። በዚያ ዘመን የነበረ ፖለቲካ ኢትዮጵያን ጋት ሳያራምዳት በመጠውለጉ የአዲሱንና በጥቂት ጊዜ ውስጥ ብዙ ለውጦችን ማስመዝገብ የቻለውን የአብይ አህመድን ፖለቲካ በአድናቆት የሚመለከቱ ናቸው በዚያ አዳራሽ የታደሙት።

## የአረጋዊ በርኼ "መንግስታዊ ስርዓት"

ዶክተር አረጋዊ በርሄ ወረቀት ያተኮረው "በኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦች ጥያቄ ምን ይመስላል፣ እንዴትስ ሊስተናገድ ይገባል" በሚለው፣ ራሳቸውን ለትግል ጫካ በከተታቸውና በ1966 ተማሪዎች ፖለቲካ መፈክሮች አንዱ በሆነው ሃሰብ ላይ ነው። ያኛውም ይኸኛውም ትውልድ ሳይፈታው ሲንገዋለል እዚህ የደረሰው የብሄር ጉዳይ ችግር ሳይሆን ነው ስለተባለ እዚህ ደርሷል። ዛሬም ዶክተር አረጋዊ ችግሩ እንዴት ይፈታል የሚል ሃሳባቸውን አካፍለዋል። በዚህ ውስጥ በዋናነት ያዩት መንግስት እና መንግስታዊ ስርዓትን መለየት ላይ ነው። መንግስታዊ ሰርዓት (state) መንግስት ቢቀያየርም ጸንቶ የሚኖር የማህበረሰብ መልካም ኑሮና ደህንነት ማስተማመኛ በመሆኑ ከመንግስት (government) ጋር ሊቀላቀል አይገባውም የሚል ፖለቲካዊ ፍልስፍናን የሚሻ ሃሳብ የዘው ቀርበዋል።መንግስታዊ ስርዓት ለመገንባት ውስብሰብ ሂደት ቢኖረውም ከዚህ የቀረ አማራጭ ግን እንደሌለው ተናግረው ይህ ህግ የበላይ የሚሆንበት ስርዐት ባለመኖሩ በኢትዮጵያውያን ህይወት ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ቀላል የማይባል መሆኑንም ተናግረዋል።

ስርዓት ካለ ህዝብ መንግስት መኖርና አለመኖሩን አያጠይቅም፣ መንግስታዊ ስርዓት አልባ መንግስት ግን በራሱ የመቆየት እድሉ የተመናመነ መሆኑንም ተናግረዋል። ዶክተር አረጋዊ መንግስት የሚለው አካል ከመንግስታዊ ሰርዓት ትርጉም ጋር እንዲለያይ የቋንቋ ልሂቃን አዲስ ስያሜ እንዲሰጡትም ጠይቀዋል።

## የመራራ ጉዲና "ኢትዮጵያዊ ማነው"

ፕሮፌሰር መረራ ከ45 ዓመታት በፊት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ወቅት ኢብሳ ጉተማ "ኢትዮጵያዊ ማነው?" በማለት ያነሳውን ሃሳብ ዛሬም ቀስቅሰውታል። የኢትዮጵያን ሁኔታ ከጠፋና መንታ መንገድ ላይ ቆሞ ከየት እንደመጣ ወዴት እንደሚሄድ ግራ የገባው ህጻን (a lost child in a cross road) አድርገው መስለውታል። ለዶክተር መረራ ኢትዮጵያዊነት እና የኢትዮጵያዊነት ፍቅር በግድ አንድ መሆንን የማይጎትት የሌላውን ፍላጎት የሚያከብር ሊሆን እንደሚገባ ነገር ግን አሁን ያለንበት ሁኔታ ይህንን እያስተናገደ አለመሆኑን ጊዜ ሰጥተው ተናግረውታል። በተለይም ከብሄር መሰል ፓርቲዎች አንጻር የርሳቸው የፖለቲካ አቋም ከኢትዮጵያዊ ፍቅር ጋር ተስማምቶ መኳዙ በብዙዎች የሚደነቅበት ምክንያት ኢትዮጵያዊ አቋማቸው ጥርጣሬ ውስጥ ስለሚገባ ለማረጋገጥ መሆኑን መገንዘባቸው እንዳበሳጫቸው ነው ሳይሸሽጉ የተናገሩት።

ዶክተር መረራ ካቀረቡት ጽሁፍ በዋናነት የሚመዘዘው ቁምነገር ይህ ነው። ባለፈ ታሪክ እየተቧቀስን ዛሬንና ነገን መርሳታችን ዋጋ አስከፍሎናል ብለዋል። " ነፍጠኛ ጠባብ ምናምን የሚለውን ነገር አንድ ቦታ ላይ ካላቆምነው ወደፊት ምን ይዘን ልንሄድ ነው? ወደፊት የሁላችንም መንገድ መንግስተሰማያት ነው ብለን ልንቀጥል ነው? ሌላ ሃምሳ አመት ለችግሮቻችን መፍቻ ልንፈልግ ነው?" ሲሉ በግለጽ ቋንቋ ያለፈ ታሪክን መዝጋት ተገቢ መሆኑን አስምረውበታል። "ለ50 አመት የቆዩ ችግር አሉ ዶክተር አብይ የማይፈታቸው ፣ በሃቅ ችግሮቻችንን ተመልክተን ለመፍታት እንጣር፣ ለሚቀጥሉት 10 እና 20 አመታት አሁን ያለው ክልል ስርዓት የቆያል ። ዴሞክራሲያዊ በሆነ አሰራር እናስተካክለው ።ፖለቲካ ማለት የሚቻለውን መስራት (the art of the possible) በመሆኑ ሃቀኛ ድርድር ያስፈልገናል" ብለዋል።

## የብርሃኑ ነጋ " የሃሳብና ፓርቲ ውህደት "

በፖለቲካ አቋማቸው ሶሻል ዴሞክራት መሆናቸውን የተናገሩት ፕሮፌሰር ብርሃኑ በዕለቱ በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሲቪል ተቋማትና የመገናኛ ብዙሃን ላይ ያተኮረ ጽሁፍ አቅርበዋል። የብዙዎችን አድናቆት ባገኘውና ከኢህአፓ ጀምሮ የነበራቸውን የፖለቲካ ትርክት ባሰፈሩበት በዚህ ገለጻ በዋናነት ያተኮሩት ተመሳሳይ አቋም ያላቸው ፓርቲዎች በሂደት ተዋህደው ጥቂት ፓርቲዎች ብቻ ይመስረቱ በሚል ጉዳይ ላይ ነው።

አንድ ትልቅ ፓርቲ መኖሩ ፣ ሌላው በተበታተነ ቁጥር ሁሌም ያንን ትልቅ ፓርቲ የሚመርጥ መሆኑን፣ በተዘዋዋሪ ጭቆናም ካለ ያ ጭቆና እንዲቀጥል እድል እንደሚፈጥር ፣ ይህም ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ለመመስረት አስቸጋሪ እንደሚያደርገው፣ በተለይ የአመለካከት እና የፖሊሲ አንድነት ያላቸው ፓርቲዎች ሰብሰብ ብለው በጋራ ቢሰሩ ምሁሮቻቸውን እና ገንዘባቸውን ሳያባክኑ ለውጤት እንደሚያደርሳቸው ተናግረዋል።

በ80 ብሄረሰብ ልክ 80 ፓርቲ መመስረት ወይም በ100 ሚሊዮን ፍላጎቶች ልክ ማዳረስ እንደማይቻልና የአመለካከት የፖሊሲ ልዩነት ከሌለ መዋሃዱ አማራጭ እንደሌለውም ገልጸዋል። ሰብሰብ ማለት እና በጋራ መስራት ተጠናክሮ ለመስራት ወሳኝ መሆኑን ገልጸው አሁን ባለንበት ሁኔታ እንደ አሸን የሚፈሉ 300 ፓርቲዎችን ይዞ ሃገር ማስተዳደር እንደማይቻል እንዲታሰብበት አስረድተዋል።

ምሁራን በጋራ ተወያይተው መፍትሄ እንዲያፈልቁ ለማድረግ ከመበታተን መሰባሰብ ተገቢ መሆኑንም አስቀምጠዋል።

ሶስቱ የፖለቲካ ጉምቱዎች ሰፊ ነገር ግን በሰዓት እጥረት የታገደ ሃሳባቸውን ካስቀመጡ በኋላ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ ነበሩ ተናጋሪ የነበሩት።

## የአብይ አህመድ "ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲ"

ዶክተር አብይ አህመድ በማብራሪያቸው ያለፈ ዘመን ፖለቲካ እና የአሁኑን ፖለቲካ ነካክተዋል። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ላይ በዙ ጥናትና ምርምር አለመደረጉ ያለብንን ክፍተት ለማወቅ እና ለማሻሻል እድል አልፈጠረልንም ብለዋል።

ያም ሆኖ ሃገሪቱ እስካሁን መቀጠሏን እና በዚህ ዘመን የሚያስፈልገን ባደረ ታሪክ መቆራቆስ ሳይሆን ወደፊት ልንጓዝ በመንችልበት መንገድ መስራት ነው በማለት በተለይም ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲን አስፈላጊነት አጽንዖት ሰጥተው ተናግረውታል።

በፖለቲካ ታሪካችን የዴሞክራሲያችንን አጀማመር ከሃሳብ አንስቶ መሬት አስኪወርድና በተማሪ ጥያቄ አስኪካተት ድረስ የነበረውን ሂደት ጠቅሰው የመሬት እና የብሄር ጥያቄ አስካሁንም ያልተመለሱ ሆነው መዝለቃቸው ውጤታማ አለመሆናችን ያሳያል ብለዋል።

አሁን ማሰብ ያለብን በኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲ ጥላ ስር ተቀራርቦ ከመነጋገር ውጪ ምንም ማድረግ እንደማንችል ነው ብለዋል። እንደ ዶክተር አብይ አቀራረብ ኢትዮጵያዊ ዴሞክራሲ ከሌላ ያልተቀዳ በውስጥ ባህል የሚዳብር እና በጋራ ለችግሮች መፍትሄ የሚፈለግበት አዲስ ያይደለ ስርዓት ነው። በኢትዮጵያ ያለው በጅምላ መሰብ ወደማንስማማበት ደረጃ ስለሚገፋን በዴሞክራሲያዊ ስርዓትና ነጻነት ወደማሰብ እና ለችግሮች መፍትሄ ወደመፈለግ መሸጋገር ይገባናል ብለዋል የአሰራር ባህላችን ለአስተዳደር አመቺ ባልሆነ መልኩ የተቃኘ መሆኑን ሲናገሩ።

እስካሁን በኢትዮጵያ ፖለቲካ ባህል ውስጥ በመነጋገር ችግሮችን መፍታት ሳይሆን በመጠፋፋት አንዱ በአንዱ ላይ መንገስ መሆኑን ፣ በተለይም አዲስ ሲመጣ ያለፈውን መናድ አንደስኬት ብቻ ሳይሆን ግዴታ ስለሚያይ ቋሚ ትውስታ ወይም ሚሞሪ ልንፈጥር አለመቻላችንን በተመጠነ ቋንቋና ገልጽነት አሳይተዋል። ከ1960ዎቹ ፖለቲከኞች ጋር ሊያስማማ በሚችል አካሄድ ተጉዞ ሃገርን በጋራ የማዳን እና ዴሞክራሲን በተለይም ነጻ ምርጫንና ስልጣንን ርስት ያለማድረግን በተግባር ማረጋገጥ የርሳቸው አላማ መሆኑነም ተናግረዋል።

በዚህ አዳዲስ ሃሳቦች በቀረቡበት መድረክ ላይ ዶክተር አብይ ይህንን አይነት ውይይት አስፈላጊ መሆኑንም አስምረውበታል። ከዚህ ቀደም የነበረን የፖለቲካ ባህል መልካም እንደነበር እና እሱን አዳብረን ዴሞክራሲያችንንም በዚሁ መስመር መቅረጽ ይጠበቅብናል ብለዋል። መዋስና መኮረጅ ሳይሆን ወደውስጥ ማየትና ያለንን ማበልጸግ ተገቢ ነው ባሉበት ንግግራቸው ቁምነገሮችን ከውስጥ መማር እና የሲቪል ባህልን መገንባት አስፈላጊነት ላይ አስምረውበታል።

ይህ ውይይት የሁለቱን ዘመን ሰዎች አስተሳሰብ አንድ አድርጎ ለመቀጠል የሚያስፈልገው ምንም ሳይሆን በጋራ መነጋገር መሆኑን ያሳየ እንደነበር ሁሉም ታዝቧል። ከዚህ አንጻር ተደጋጋሚ መድረኮች ቢዘጋጁ የህዝቡን ንቃተ ህሊና በማሳደግና ከዛገብን የቆየ የፖለቲካ ባህልም ተላቅቀን ለመጓዝ ያስችለናል።


እንደአለም አራጌ

# የዘመናዊ ፖለቲካችን ፍኖተ ካርታ

የኋላ ነገራችንን መተረክ ብዙም ደስታ አይሰጠኝም:: ብዙዎች ብዙ ያሉበት ስለሆነ:: የተለየ ምርምር ያላደረኩበትን ጉዳይ የብዙኃንን ጠቅላላ ዕውቀት መልሶ ማስተጋባት ይመስለኛል:: የሚታወቀውን መድገም ደግሞ ብዙም ፋይዳ የለውም:: ነገር ግን ቀጥታ ያለንበትን ዘመን ከመተንተን ይልቅ ከወዲያኛው ዘመን ላይ ሆኖ ወደ አሁኑ ለመመልከት ወታደራዊ ገዥ መሬትን የመቆጣጠር አይነት ስሜት ይፈጥራል::

በእስር ቤት ቆይታዬ ብዙ ካሰብኩባቸውና ከፃፍኳቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የፖለቲካ ባህላችን ነው፡ የሀገራችንን የፖለቲካ ችግሮች በጥልቀት ለማየት ስሞክር ሁልጊዜም ሥራቸው አንድ ቦታ ላይ ተደራርቦ ይታየኛል፤ የፖለቲካ ባህላችን ላይ:: በተለይ የዘመነ መሳፍንቷ ሀገራችን ኢትዮጵያ የቆመችበት የባህል ንጣፍ የተደራረበና በቀላሉ ከፖለቲካ ገፀ ምድራችን ፈንቅለን ለመጣል የሚቻል አልሆነም::

ከዘመነ መሳፍንት እስካሁን የተደረጉ የለውጥ አውዶችን በቅርብ እርቀት ላይ ለመመልከት ስንሞክር ስኬት አልባ የመሆናችን አንኳር ምስጢር በዚሁ የዘመነ መሳፍንት የፖለቲካ ባህል ቅኝት ለውጥ ለማምጣት መሞከራችን ይመስለኛል:: ባልተቀየረ ዘመን ጠገብ የፖለቲካ ባህል ሀገር የመቀየር ትግል በማድረጋችን ይመስለኛል:: ምን አልባት በእንቅርት ላይ እንዲሉ ከ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ በኋላ መሀል ሰፋሪ የተሰኘው ኃይል ያመጣው የተዛባ የፖለቲካ ባህልም በእኔ ዕይታ በይዘቱ ከዘመነ መሳፍንት ፖለቲካ በተወሰነ መልኩ የሚለይና የፖለቲካ ባህላችን ጤና ያወከ ነበር ማለት ይቻላል::

ባህል የሥነ ልቦናችን አዕማዶች የሚቆሙበት ንጣፍ ይመስለኛል:: ዛሬ የፖለቲካ መስተጋብሮቻችን ውጥንቅጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መነሻው ይኸው የሥነ ልቦናችን ውቅር ነው:: በርግጥ ካፈው ስህተታችን እንማራለን ስንል ያለፈውን ስህተት የማድረግ አዝማሚያ ይስተዋላልና መጠንቀቅ ተገቢ ነው:: ዘመናዊ የተሰኘው ሁሉም ዘመናዊና ለእኛ የሚጠቅም ላይሆን ይችላልና ሚዛኑን የጠበቀ ምልከታ ሊኖረን ይገባል:: ይኽን ያክል ስለቀደመው ዘመን ካወሳው ከዚህ በኋላ ሊኖረን የሚገባ የፖለቲካ ባህላችን ድሮች ቢሆኑ ያልኳቸውን ጥቂት ነጥቦች እንዳነሳ ፍቀዱልኝ፤

## 1ኛ. ከሌሎች ምን እንደጎደለ ከመጠየቃችን በፊት ከእኛ ምን እንደጎደለ መጠየቅ

ለአያሌ ዘመናት የፖለቲካችንን ሰማይ በሸፈነው የፖለቲካ መስተጋብራችን በቅርብ የሚገኝና የሚታይ ማንነታችንን ለመፈተሽ አቅም አግኝተን የምናውቅ አይመስለኝም:: እራስን የመተቸት ጀግንነትም እምብዛም የምናውቀው አይመስለኝም:: ሌሎች ላይ አሻግረን ሁሉንም በመምረግ እራሳችን ቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ እናስቀምጣለን:: በሌላ ወገን ያለውም እንዲሁ:: በዚህ ሁኔታ ተቀራርቦ መወያየት ከአድማስ ማዶ ይርቃል:: በቃላት ከመወያየት ይልቅ በአፈ ሙዝ መወያየት ብቸኛው አማራጭ ይሆናል:: ይህ ሁኔታ የሚያሳየው ምን ያህል ለሥልጣኔ እሩቅ መሆናችንን ይመስለኛል:: ምክንያቱም ሰው ሲሰለጥን የሚሰለጥነው በራሱ ላይ ነውና:: በራሱ ላይ የሠለጠነ ሰው ወደ ውስጡ ያያል:: በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያዩ እየታዎች ቢኖሩንም ቀድመን እራሳችን ከፈተሽን ያለ ብዙ ድካም ችግሮቻችንን ለመፍታት ብሎም ለመቀራረብና ለመወያየት እድል እናገኛለን:: የሥልጣኔ የመጨረሻው ጥግ ደግሞ በጉዳዮች ላይ በጥሞና መወያየት ይመስለኛል::

## 2ኛ. የተጠቂነት ሥነ ልቦናን ማሸነፍ

እርስ በርስ የምንባላባቸው ጉዳዮች በዋናነት የተጠቂነት ሥነ ልቦና ተመርኩዘው የሚነሱ ናቸው:: ቀማሪዎቹ የፖለቲካ ልኂቃን ሲሆኑ በተጠቂነትና እራስን በመከላከል ስልት አዙሪት እንዲወድቅ ሙሾ የሚወርድለት ደግሞ ሕዝቡ ነው:: አገዛዝ ሁልጊዜም በእውነት ላይ አይቆምም:: ያልተሰጠውን እንደተሰጠው ተጠልቶ ሳለ፣ ብዙኃን በፍቅር እንደወደዱለት፣ ግቡም የሕዝብ ነጻነት እንደሆነ ይሰብካል:: ይኸንን አስተምሮውን ተቀብሎ የማያደገድገው ሁሉ ይወገራል፤ ይገደላል:: ከየትኛውም ወገን ቢሆን:: ሁሉም የብሔር ነጻ አውጪዎች የእኛ ከሚሉት ብሔር ይልቅ (የእነርሱ ብቻ ከሆነ) የሌላውን ወገን ሰብአዊ ክብር መውደቅ እንዳያዩ አይናቸው ተጋርዷል:: የጣር ድምፁን እንዳይሰሙ እዝነ ልቦናቸው ደንቁሯል:: የሚፈላው የዘረኝነት ጥንስስ የእኛ ከሚሉት ዘር በላይ ሰው ላሳር ይላቸዋል:: ዘረኝነት ልክፍት ስር የሰደደ ደዌ ነው:: ከበታችነት ጥልቅ ጉድጓድ የሚቀዳ ነቀርሳ ነው፤ ማንም ቢያቀነቅነው:: ስለዚህ ከዚህ ደዌ የተፈወሰ የፖለቲካ መስተጋብር ለሁላችም መድህን ይመስለኛል::

## 3ኛ. ፍርሃታችንን ከመኖር ህልማችንን እንኑር

በፖለቲካችን ውስጥ ፍርሃት ሞልቶ ተርፏል:: በአገዛዝና በሕዝብ መካከል የነበረውን የነጻነት ግርዶሽ ሆኖ ህልቆ መሳፍርት ለሌላቸው ዘመናት የዘለቀው የፍርሃት ከል እየተገፈፈ ይመስለኛል:: በፖለቲካ ልኂቃን መሀል ያለው የፍርሃትና ያለ መተማመን ጥቁር ደመና ግን ብዙ ሥራ እንደሚጠይቅ ይሰማኛል:: ስለሌሎቹ በጎ ማሰብና እንደሚያስቡም መገመት ሰብአዊ እድገታችንን የሚያቀጭጭ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባውም፤ እንዲያውም ጤናንም ሆነ ሰብአዊ ልዕልናን የሚያበለጽግ እንደሆነ እገምታለሁ:: ከፍርሃት ይልቅ መተማመን ላይ ለመጀመር ዘመን እንደመጣ ይሰማኛል:: መተማመን ላይ ስንሠራ የጋራ ህልሞቻችንን መኖር እንጀምራለን:: ለጋራ ህልሞቻችን በጋራ ስንሠራ የማይናድ ገደል አይኖርም:: ፍርሃትና አለመተማመን ላይ ቆመን አንድ ዓይነት ህልም አይኖረንም:: ‹‹የሚጋጩ ህልሞቻችንን›› ለመፍታት የማያበራ ግጭት ውስጥ በመዝፈቅ እንቀጥላለን::

## 4ኛ. በተግባር ተፈትኖ የሚያልፍ የፖለቲካ እምነት ማራመድ

እስከዚህ ዘመን ድረስ በፖለቲካ ቤተ ሙከራዎች የታዩ ግኝቶች ሁሉ አገዛዝ ሕዝብንም ሆነ ጎሳን መሠረት ቢያደርግ እራሱን አውሎ ከማሳደር የዘለለ ርዕይ እንደሌለው ይመሰክራሉ:: የአገዛዝ ልዕልና በሕዝባዊ ልዕልና ሊተካ ጊዜው ደርሷል:: አሁንም ግን አንድ የፖለቲካ ስንክሳር ንጋታችንን ሊያጨልም ይችላል:: ዴሞክራሲ በግለሰቡ ልዕልና ላይ እስካልቆመ ድረስ ምንም አይነት አማላይ ስም ብንሰጠው ዴሞክራሲ አይሆንም:: ግለሰቡ ሰብአዊ ግዴታዎችና መብቶቹ የተደራረቡበት የልዕልና ልቃቂት ነው:: በትክክል የግለሰቡ መብት በሚከበርበት በየትኛውም ሁኔታ የሚጣስ ምንም ዓይነት መብት አይኖርም:: ምክንያቱም ሌሎች ሁሉ መብቶች የሚተረተሩት ከዚሁ ከግለሰቡ የልዕልና ልቃቂት ነውና:: ተፈትኖ የሚልፈው የፖለቲካ መስመርም በሐቅ የግለሰቡ መብት ላይ የሚቆም የፖለቲካ ሥርዓት ስለመሆኑ ብዙ እማኞችን ማቅረብ ይቻላል::

## 5ኛ. ከግለሰቦች በጎ ፍቃድ ይልቅ በፅኑ መሰረት ላይ በቆሙ ተቋሞች ላይ እንደገፍ

ኢትዮጵያ መሪዎች የማይከሰሱባት ሕዝብ ደግሞ በእነርሱ አሳሩን የሚያይባት ሀገር በመሆን ትታወቃለች:: በጎበዝ አለቃው የሚምል የሚገዘተው ሕዝብ ከጎበዝ አለቆቹ የሚታደጉት ተቋማትን መገንባት አልቻለም:: እስከአሁን እጣ ክፍሉ በገዥዎች መረገጥ ሆኗል:: ይህ ታሪካችን ወደ ኋላ ላይመለስ ይቀየር ዘንድ ሁላችንም የምናምንባቸውና የምንደገፍባቸውን ተቋማት ለመገንባት የሁላችንም ተሳትፎ ይጠይቃል::

ቀጣዩን በገጽ 27 ይመልከቱ

# ፍሬ አልባ ከሆነው የፓርቲዎች የውይይት አዙሪት መውጣት ይኖርብናል!

የሐሳብ ብዝኃነት  የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዋጋግራ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ አንድ ወጥ የሆነ አመለካከት ወይም የፓለቲካ አቋም ለዴሞክራሲ ባእድ ነው፡፡ እኩዩም ሆነ በጎው እርስ በርስ የሚፋጩበት፣ተፋጭተውም የፓለቲካ እምነታቸውን ለሰፊው ሕዝብ ለአውደ ርእይ የሚያቀርቡበት አቃፊ ምህዳር ይመቻችላቸዋል፡፡ይህንን ዓላማ በየፊናቸው ተሸክመው ለውድድር የሚገቡት ደግሞ የፓለቲካ ፓርቲዎች ናቸው፡፡ሰፊው ሕዝብ ያሻውን ዓላማ የሚገልጽበት ዕድል መፍጠር ስለሚችሉ የፓለቲካ ፓርቲዎቹ ጉራማይሌ ቁመና እንደ በረከት እንጂ እንደ መርገም አይወሰድም፡፡የእኛም ሀገር የፓለቲካ ፓርቲዎች ሚና የሚገመገመው በዚህ ማእቀፍ ውስጥ ነው፡፡ዴሞክራሲ በሀገራችን ገና በአግባቡ  እንኳን መዳህ አልጀመረም፡፡ ባለፉት ሁለት ዐሥርተ ዓመታት የአገዛዝ ዘመን የተተወ ምንም ዓይነት የዴሞክራሲ ቅሪት የለም፡፡ይህኛው የለውጥ አስተዳደር ሁሉንም ከዜሮ ነው የሚጀምረው፡፡

ሕወሓት/ኢሕአዴግ  ሲቀልድበት በነበረው ሀገራዊ ምርጫ ላይ ሻማ ያኸር የነበሩ በርካታ ፓርቲዎች አሁንም ከምህዳሩ ገሸሽ አላሉም፡፡እነዚህ ፓርቲዎች በሕዝብ መብት እና ነጻነት ኪሳራ አፋኙ ሥርዓት ፀንቶ እንዲቆይ የማይናቅ አስተዋፅኦ ሲያበረክቱ ኖረዋል፡፡  አዲሱ የለውጥ አስተዳደርም እነዚህን በፓለቲካ ጥቁር ገበያ የከበሩ እኩይ ኃይሎችን ከምህዳሩ ለማጽዳት ገና የቤት ሥራውን መሥራት አልጀመረም፡፡በርግጥ ፓርቲዎቹ በየጊዜው በሚዘጋጅ የውይይት መድረክ ላይ ሰልፍ ከማበላሸት የዘለለ ጉዳት እንደሌላቸው ከማንም የተሰወረ ሐቅ አይደለም፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በዘመነ ሕወሓት/ኢሕአዴግ በመናኛ ቁመና የገዢው መንግሥት አገልጋይ ከመሆን ያለፈ ሚና ያልነበራቸውን ኃይሎች፣በአልበገርነታቸው እና በቁርጠኝነታቸው ሕዝብ ከሚያውቃቸው የፓለቲካ ፓርቲዎች ጋር በአንድነት ቀይጠው  የውይይት መድረክ ሲፈጥሩ የአሁኑ ሁለተኛቸው ነው፡፡የቀድሞውም ሆነ የአሁኑ የውይይት መድረክ ፍሬውን ከገለባው የለየ አይደለም፡፡ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለተፎካካሪ ፓርቲዎች የከፈቱት መድረክ በአዎንታዊነት የሚወደስ ቢሆንም ከዚህ አስቀድሞ በወጉ መጥራት የሚኖርባቸው ኹነኛ ሥራዎች በአግባቡ መሠራት ነበረባቸው፡፡ በእዛ በጨለማ ዘመን ሕዝብን እንደ መርግ የተጫነውን ሥርዓት የበለጠ ለማጠናከር እሳት ሲያቀብሉ የኖሩ አድርባዮች/ Opportunists/ ቆብ ቀይረው በድርድር ሂደት ውስጥ ያለሀፍረት ፊት ለፊት ሲሰለፉ ስናስተውል፣የሀገራችንን ፓለቲካ ከሴራ ንድፋ ሐሳብ ነጻ ለማድረግ ገና ብዙ ርቀት መሄድ እንዳለብን ጠቋሚ ሊሆነን ይችላል፡፡

በኪሳቸው ዘውድ ይዘው የሚንቀሳቀሱ፣የአባላቶቻቸው ብዛት ከአንድ ቤተሰብ ቁጥር የማይልቁ ፓርቲዎች በጊዜ ሒደት እየተራገፉ እንደሚሄዱ የሚታወቅ ቢሆንም አስቀድሞ ሌሎች መንገዶችን በመጠቀም የማጥራቱን ሥራ ከወዲሁ መከወን ይኖርበታል፡፡ይህንንም ገቢራዊ ለማድረግ ምርጫ ቦርዱ አንዱ ወሳኝ ተቋም ነው፡፡እነዚህን ሰልፍ የሚያበላሹ መናኛ ፓርቲዎችን ከፓለቲካ ምህዳሩ ላይ ለማጽዳት የዳግም ምዝገባ ቢካሄድ ተገቢ ነው፡፡አዲሱ የለውጥ አስተዳደር ከፓለቲካ ፓርቲዎች ጋር በየጊዜው ለማካሄድ ያሰበውን ወይይት ከሚዲያ ፍጆታ በዘለለ ትርጉም ያለው ውጤት ለማስመዝገብ፤ ጠንካራ እና ሰፊ ድጋፍ ያላቸውን ፓርቲዎች አጥልሎ በማስቀረት በሕዝብ ዘንድ አመኔታ የሚኖረውን የሥርዓት ግንባታ እውን ለማድረግ  መነሳት ይኖርበታል፡፡

በሕወሓት/ኢሕአዴግ ተጠፍጥፈው ያልተሰሩት እውነተኛ የሕዝብ ኃይሎችም ቢሆኑ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት መወጣት አለባቸው፡፡ ከሌሎች፣ ኩታገጠም አቋምን ከሚያራምዱ ፓርቲዎች ጋር ጥምረት በመፍጠር ገዢውን መንግሥት በትክክል ለመፎካከር የሚያስችል ቁመናን በመላበስ አማራጭ የሕዝብ ድምጽ ወካይ ሆነው ብቅ ለማለት የሚኖራቸው ቁርጠኝነት ወሳኝነት አለው፡፡ "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" የሚሉት አቻ እና ተጻራሪ ምርጫዎች ለሀገራችን ፓለቲካ ፓርቲዎች በልክ የተሰፉ ናቸው፡፡ ሦስት እና አራት ትልልቅ ዘውግ ዘለል/meta-ethnic/ ፓርቲዎች የገዢው መንግሥት ተገዳዳሪ ሆነው ቢፈጠሩ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚኖረው ፋይዳ የላቀ ይሆናል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን በሀገር እና በሕዝብ መጻኢ እድል ላይ እንደመቀለድ ይቆጠራል፡፡ ስለዚህ ፈጥኖ ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ በመግባት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመቀለስ የሚፈጀውን የብዙ ሺህ ኪሎሜትር መንገድ ለማገባደድ ቀዳሚው እርምጃ መጀመር ይኖርበታል፡፡


**ግዮን መጽሔት**
**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና**
**ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**
**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ
አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2 የቤት ቁጥር 475

**ማኔጂንግ ኤዲተር**
ደረጀ ይመር

**ተባባሪ ዘጋቢያችን**
ቶማስ አያሌው(**ከአሜሪካ**)

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ብሩክ መኮንን

**አዘጋጅ**
ተስፋዬ ሽብሩ
ሔማስ ታፈረ

**አምደኞች**
ፍቅሩ ኪዳኔ (**ከሲውዘርላንድ**)
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
መስፍን ጌታቸው
አስማማው ኃ/ጊዮርጊስ(**ከአሜሪካ**)
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
ታምራት መርጊያ

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ሀብታሙ መኮንን

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09  የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011mag@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10  የቤ.ቁ. 066/ሀ


በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

# “በትግራይና በአማራ የተፈጠረውን ግጭት የክልሉ አመራሮች ናቸው የወለዱት”

### ኢንጅነር ግደይ ዘረአጽዮን

## “የአንድነትና የዜግነት ፖለቲካ እንዲኖር ነው የምፈልገው”

**የሕወሐት መስራችና የድርጅቱ ም/ሊ/መንበር የነበሩት ኢንጅነር ግደይ ዘርአጺዮን ባለፈው ሳምንት ባስነበብናችሁ ቃለ መጠይቅ ላይ የህወሐትን አጠቃላይ ባህሪና ወቅታዊ ጉዳዮችን በተመለከተ በስፋት ገልጸውልናል፡፡ በዛሬው ቆይታችን የአማራና የትግራይ ህዝብ ግንኙነትና ልዩነት አስመልክቶ ያደረጉትን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡**



**ግዮን፡- በቅርቡ በአቶ ገዱ አንዳርጋቸውና በዶ/ር ደብረጽዮን በኩል የተደረገው የሰላምና የዕርቅ ጉዳይ “ከአንገት በላይ የሆነ ዕርቅ ነው” የሚሉ ሰዎች አሉ:: የአማራና የትግራይ ሕዝብ ደግሞ በባህል፣በሃይማኖት እና በታሪክ እርስ በርሳቸው የተጋመዱ እንደሆነ ይታወቃል::ስለዚህ ክልሎቹን በሚያስተዳድሩት የፖለቲካ ኃይሎች መካከል የሚስተዋለው መቆራቆስ በጊዜ መፍትሄ ካላገኘ የሁለቱ ሕዝቦች ቀጣይ እጣፈንታ ምን ሊሆን ይችላል?**

**ኢ/ር ግደይ፡-** አሁን በትግራይና በአማራ መሀል የተፈጠረውን ያለመግባባት በስልጣን ላይ ያሉት አመራሮች ናቸው የወለዱት:: የሁለቱም ክልል መሪዎች የህዝብን ስሜት በማነሳሳት፣ የህብረተሰብን ድጋፍ ለማግኘት የሚሞክሩበት ሁኔታ አለ:: በርግጥ ሰላምና መግባባትን የሚፈልጉ ቢሆን ኖሮ ይህን ያህል የሚያቃቅራቸው ሁኔታ ባልተፈጠረ ነበር:: ነገሮች መጀመሪያውኑ አቅጣጫቸውን ሲስቱ ቁጭ ብለው ሊፈቱት ይችሉ ነበር::

ህዝብን ማወያየት ይቻላል::ነገሮችን በጥልቀት መመርመር የሚያስችል፣ በህገ ደንቡም የተቀመጠ አካሄድ አለ:: ጉዳዩ ፌዴሬሽን ም/ቤት ደርሶ ምላሽ የሚሰጥበት፣ የአፈጻጸም ሐዲቶች አሉ:: ለምሳሌ ጉራጌ አካባቢ “ስልጤ ነኝ፣ ጉራጌ አይደለሁም” የሚለው ጥያቄ በዚህ መንገድ ተፈትቷል::

ስለዚህ የሚነሱትና አወዛጋቢዎቹ ጥያቄዎች የሚፈቱበት ግልፅ የሆነ የሕግ አግባብ ስላለ ሁለቱን ህዝቦች እርስ በርስ ማጋጨት ለምን ያስፈልጋል፤መጀመሪያውኑም እስከዛ ድረስ መሄድ የለባቸውም :: ይህ ከሆነ ጽንፈኛ ኃይሎች ከጉዳዩ በስተጀርባ እንዳሉ ይገባሃል:: ለምሳሌ በአማራው በኩል እንደ እነ አ.ብ.ን ያለ የፓለቲካ ድርጅት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጤነኛ አይደለም ::ፉከራ ታያለህ፣ ሰላማዊ ሰልፎችና ሽለላ የምታይበት ሁኔታ አለ:: ይሄ ለማንም ስለማይበጅ መቆም አለበት::የአማራው ክልልም እንዲህ ዓይነት ነገር እንዲፈጠር መፍቀድ አልነበረበትም:: በዚህ ዓይነት የተጋጋለ ሁኔታ ሁለቱም ክልሎች የሚያተርፉት ነገር አይኖርምም::

**ግዮን፡- የኢትዮ ኤርትራን የሰላም ስምምነት እንዴት አገኙት፤ ከኤርትራ ጋር ጦርነት የተገባበትና ይህን ያህል ጊዜ ልዩነት ያመጣው የሁለቱን ሀገሮች ግንኙነትና ጥቅም በተመለከተ በህግ የተቀመጠ ነገር ስለሌለ ነው፤ የሚሉ አስተያየት ሰጪዎች አሁንም የችግሩ ምንጭ አልደረቀም ይላሉ::በዚህ ላይ የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው?**

**ኢ/ር ግደይ፡-** ጥሩ ጥያቄ ነው:: እኔ ከመጀመሪያውም ያ ጦርነት መደረግ የለበትም ብዬ ተቃውሜያለሁ:: ከምን ተነስቶ የት እንደደረሰ ሁላችንም በግልፅ አይተነዋል:: በምንም መንገድ መፈጠር ያልነበረበት ጦርነት ነው:: ይህ ከሆነ ከ20 ዓመት በኋላም ቢሆን በዚህ ወቅት ወደ ሰላም መምጣቱ እጅግ በጣም ትልቅ ውጤት ነው:: ደስ ይላል:: የዚህን ስኬት ለጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ነው የምሰጠው፤ እሱ ስልጣን ላይ ባይወጣና ሕወሓቶች ሀገሪቱን በመምራት ላይ ቢቆዩ ከኤርትራ ጋር የነበረው ችግር አይፈታም:: ይህን ያህል ዘመንም አልተፈታም::

ከለውጡ በኋላ ግን ጠ/ሚኒስትሩ በፈጣን ዕርምጃ የሁለቱን ሀገራት ሠላምና ዕርቅ ዕውን የማድረግ ትልቅ ስራ ነው የተሰራው:: በርግጥ በኢትዮጵያ በኩል ብቻ ሳይሆን በኤርትራ በኩል የነበሩ ግላዊ ችግሮች ነበሩበት፤ የኢትዮ ኤርትራ ጉዳይ:: ግን ይሄ ሁሉ አሁን ተፈትቷል:: ችግሮች ተወግደው፣ ህዝቡ እርስ በርሱ መገናኘቱ፣ ምን ያህል ተነፋፍቀው ቆይተው እንደነበር ከእኛ አልፎ ለቀሪው ዓለምም በግልፅ አሳይቷል:: ►

ስምምነቱ ወይም ግንኙነቱ በጣም ጥሩ ነው፣ ቆንጆ ነው:: ግን አስቀድመን እንዳነሳነው እንዲህ ዓይነት የሁለት ሀገር የጋራ ስምምነቶችና ግንኙነቶች ጤናማ በሆነ ፣ በህግና ደንብ በተቀመጠ አሠራርና ህዝብ (የሁለቱም ሀገር) በሚያውቀው መንገድ መሄድ አለበት:: ኢትዮጵያና ኤርትራ ወደ አዲስ ስምምነት ከመጡ ወይም ተቋርጦ የነበረውን ግንኙነት ካደሱ በኂላ ስምምነታቸውን ለህዝብ ግልፅ አለማድረጋቸው፣ እኔ ትልቅ ድክመት ነው ብዬ ነው የማምነው:: መሆን አልነበረበትም::

ሕጋዊ መንገድ መያዝ አለበት፤ ስምምነቱ ወይም ዕርቁ ልል መሆን የለበትም:: በፊትም እነ መለስ ዜናዊም ከኤርትራውያን ጋር የፈጠሩት ግንኙነት የግብር ይውጣ ነበር:: በኂላ ወደ ጦርነት ገቡ:: ስለዚህ የሁለት ሀገሮች ግነኙነት ህግን የተከተለ፣ ለህዝቡ ግልፅ የሆነ፣ ሀሳብ የተንሸራሸረበት መሆን አለበት::

ለምሣሌ በቅርቡ የዛላንበሳን መንገድ ሲዘጉ በሕዝብ መሀል የመጣውና የተፈጠረው ስሜት ሌላ ነገር ነው:: ለምን ተዘጋ? በሚል ሌላ መንፈስ ተፈጠረ፤ በተለይ ትግራይ ውስጥ እንደዚህ መሆን አልነበረበትም:: እዛ እንደዚህ አድርገው በሁመራ ደግሞ ሌላ መንገድ ይከፍታሉ:: ይሄ ምንም እርባና የሌለው ጨዋታ ነው:: መጀመሪያውኑ ሁለቱ ሀገሮች ሲታረቁ፣ ሊያደርጉ ያሰቡትን ነገር ግልፅ ባለ መልኩ ለህዝቡ ማሳወቅ ነበረባቸው::

**ግዮን፡- የዛላንበሳን መንገድ ዘግቶ የሁመራን መክፈቱ ያለው ጠቀሜታና ምክንያት ምንድን ነው?**

**ኢ/ር ግደይ፡-** እኔም አልገባኝም:: ሊገባኝም አይቻልም እንደዚህ ዓይነት ነገር:: ለማንም የሚገባ ነገር አይደለም:: አሁን እያነሳነው ያለው ነገር  የእዚህ ተያያዥ ችግር ነው:: ሕዝቡን አሳማኝ በሆነ ምክንያት ግልጽ ቢያደርጉለት ኖሮ ብዥታውን ማጥራት ይቻል ነበር::

ግን እኛ ከውጭ ሆነን ነገሮችን ብቻ የምንመለከትና ምክንያቱን የማናውቅ ሰዎች ምንድን ነው የምናስበው፣ ከምን መደምደሚያ ላይስ እንድረስ?  ፈፅሞ እንደዚህ ዓይነት ነገር ከዚህ በኂላ መፈጠር የለበትም:: ሁሉ ነገር ሥርዓት የያዘና በህግ የተቀመጠ መሆን ይገባዋል:: የኢትዮ ኤርትራ ግንኙነት ህጋዊ መስመርን የተከተለ  ከሆነ ጥቅሙ ለሁለቱም ሀገራት ነው የሚሆነው::

**ግዮን፡- ትህዴት የእናንተ ፓርቲ ሕወሓት ለፌዴራል መንግስቱ ተገዢና ታዛዥ አልሆንም ባለበት ሰዓት ትግራይ ውስጥ ገብታችሁ በነፃነት ለመንቀሳቀስና ፓርቲያችሁን በክልሉ ህዝብ ዘንድ ተቀባይ እንዲሆን ለማድረግ ከባድ ፈተና አይገጥማችሁም?**

**ኢ/ር ግደይ፡-** እንግዲህ ትግራይ ውስጥ ከሌላው ክልል  የመንቀሳቀስ መብት አንፃር ስናየው እዛ ያለው ሁኔታ ገና ዝግ ነው:: በብዙ ችግር የታጠረ ነው:: እኛ ወደ ሀገር ቤት በለውጡ ማግስት ገብተን ለመታገል ከመወሰናችን በፊት አረና ትግራይ ረዘም ያለ ጊዜ በቦታው ሲሰራ ቆይቷል:: እነሱ ላይ የሚደረገው እንቅስቃሴ ከባድና እንደሆነ እናውቃለን::

ግን ይህ ሁሉ ችግር ቢኖርም የግድ እዛው ትግራይ ገብተን ዓላማችንን ለህዝብ በማስረዳት ትግሉን በድል ለመወጣት እንችላለን ብለን ነው እኛ እንደ ፓርቲ የምናስበው:: በርግጥ ይሄን ነፃ ለማድረግ ከምንሞክርበት ጊዜ አንስቶ ብዙ ፈተናዎች ያጋጥመናል፤ ምናልባት በፌዴራል ደረጃ ያለው የፖለቲካው አዲስ መንፈስ በሂደት ትግራይ ላይም ሊንፀባረቅ ይችላል ብለን እንገምታለን:: ፈተናው ግን በጣም ብዙ ነው::

እኛ ወደ ኢትዮጵያ ገብተን በትግራይ ውስጥ ለመንቀሳቀስ ስናስብ፣ ከመግባታችን በፊት ስማችንን ከማጥፋት ጀምሮ በርካታ ነገሮች በግልፅ ሲደረጉ እናያለን:: በተለይ በሶሻል ሚዲያዎች ላይ የሚያቀርቡትና የትግራይን ህዝብ ለማሳሳት የሚያደርጉ ነገር ብዙ ነው::

**ግዮን፡- በቀጣይ ፓርቲያችሁ በክልሉ ገብቶ ከመስራት ፍላጎት አኳያ ከትግራይ አስተዳዳሪዎችም ሆነ ከፌዴራል መንግስቱ ጋራ እስካሁን የተነጋገራችሁበት ሁኔታ አለ?**

**ኢ/ር ግደይ፡-** ከክልሉ መንግስት ጋር መጀመሪያ ላይ ስንገባ ብቻ ነው የተነጋገርነው:: ከዛ በኂላ በጥልቀት በጉዳዮች ለመነጋገርና በቀጥታ ወደ እንቅስቃሴ ለመግባት፣ በእኛ በኩል ጠንካራ ፍላጎት ስላለ አመራሮቹን ለመገናኘት ሙከራ እየተደረገ ነው:: እስካሁን ድረስ ግን አልተሳካልንም፤ በትግራይ በኩል::

በፌደራል መንግስት በኩል ግን ለመስራትና ለመንቀሳቀስ እንደምንችል ተገልፆልናል:: ይሄ ደግሞ ለሁሉም ፓርቲዎች የተፈቀደ ነው:: ምን ሊረዱን እንደሚችሉ ግን ግና በግልፅ የተቀመጠ ነገር የለም::

**ግዮን፡- በፓርቲ ደረጃስ አብራችሁ ለመስራት የተስማማችሁት ከእነማን ጋር ነው?**

**ኢ/ር ግደይ፡-** በፓርቲ በኩል እኛ ከሁሉም ጋር አብሮ ለመስራት ፍላጎት አለን:: ከአረና ትግራይ ጋር ግን በአንድነት ለመስራት ቅድመ ስምምነት በመድረሳችን መግለጫም አውጥተናል:: አብረን እንሰራለን፤ ከአረና ጋር የተግባባንበት ሂደት ወደ እዛ የሚወስድ ነው::

ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር እንነጋገራለን፤ እንወያለን፣ በተለያዩ መድረኮች ላይም እንሳተፋለን:: በአላማ የበለጠ ከእኛ ጋር የሚስማማው የመድረክ ፕሮግራም ስለሆነ ከእነሱ ጋር አባል ሆነን በስፋት እየሰራን ነው ያለነው::

**ግዮን፡- ለኢትዮጵያ የሚበጀው የብሔር ፖለቲካ ነው የዜግነት ፖለቲካ?**

**ኢ/ር ግደይ፡-** ሒደቱ እየተጠናከረ መጥቶ የፌዴራል የአንድነትና የዜግነት ፖለቲካ እንዲኖር ነው የምፈልገው፤ ግን አሁን ባለው ሁኔታ የነበረው ስርዓት የተለያዩ ብሔረሰቦች ራሳቸውን አጠናክረው በመምጣት የራስ መተማመን እንዲሰማቸው፣ ባህላቸው እንዲታወቅ ማድረጉ ትልቅ ውጤት ነው:: ይሄንን ሒደት ተጠቅመን የአንድነት መንፈስ ላይ ብንመጣ መልካም ነው ብዬ አስባለሁ::

ያለፈው ሁኔታ ምንድነው ችግሩ ብትለኝ፣ ወደ አንድነት የሚያመጣውን ሒደት ከማጠናከር ይልቅ በሥርዓቱ በኩል ልዩነቱን ወደ ማጉላቱ ነበር ትኩረት የተደረገው:: እሱ ነው አሁን ችግር የፈጠረብን፣ ይሄ የብሔር ፖለቲካ የምንለው:: ወደ አንድነት የሚያመጣውን ማጠናከር፣ የዜግነት ፖለቲካ የሚያብብበትን ኢኮኖሚ፣ ሶሻል፣ በተለያዩ ባህል ውስጥ ያሉትን መልካም ነገሮችን ማሰናሰል ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ::

ይሄን ካደረግን ከብሔር ፖለቲካ ወጥተን የዜግነት ፖለቲካን በሀገሪቷ ማስረፅ ይቻላል:: እኛ የምንፈልገው ህብረተሰቡ አንድ ሆኖ የጠነከረ ኃይል እንዲኖረው ነው:: ለሀገር የሚበጀውም የሚጠቅመውም ይሄ ነው:: ግን አሁን ባለው ሁኔታ የዜግነት ፖለቲካ እንጂ የብሔር ፖሊቲካ ፈፅሞ አያስፈልግም ብትል አይሆንም፤ ለዓመታት ሲሰራበት የኖረ ነወና::

**ግዮን፡- ፖለቲካ ጡረታ አለው? የእናንተ ትግልና ጉዞስ የት ድረስ ነው?**

**ኢ/ር ግደይ፡-** ጡረታ መኖር ነበረበት:: እውነቴን ነው:: አሁን ባለንበት ሁኔታ ተመልሰን ወደ ፖለቲካ መግባታችን ራሱ የሚገርም ነው:: ያልተሟሉ ነገሮች አሉ፤ በተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ ላይ የታየውን በጎ መስመር ማገዝ አለብን በሚል ለማስተካከል ካልሆነ በስተቀር እኔ አሁን በፖለቲካ ውስጥ የመሳተፍና ስልጣን የመያዝ ሀሳብና ጉጉት የለኝም::

በዚህ ወቅትም ሆነ ፈጣሪ የፈቀደልኝን ዕድሜ በስራም ከልጆቼ ከቤተሰቦቼ ጋር ባሳልፍ ደስ ይለኛል:: ከዛ ውጭ ግን በታሪካችን ውስጥ ያገኘነውን ጥሩ አጋጣሚ ህዝብና ሀገር እንዲጠቀምበት የተጀመረውን የለውጥ ሒደት ቢያንስ ባለን አቅም የተቻለንን ያህል እናግዝ፤ በተማርነውና በሰራንበት ልክ ዕውቀትና ችሎታችንን እናበርክት በሚል ነው ወደ ሀገራችን ለመግባት የወሰነው:: እንደምታውቁት ለውጡ ሲመጣና ጠ/ሚኒስትሩ በውጭ ያሉ የፖለቲካ ሰዎች እንደገቡ ሲጋብዙ የቀረበውን የቅንነት ግብዣ በመቀበል ለውጡን ለማገዝ ቀድመን የገባነው እኛ ነን::

**ግዮን፡- በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ህልምዎ ምን እንደሆነ ይግለፁልን እና ውይይታችንን እንቋጭ፤**

**ኢ/ር ግደይ፡-** አሁን በኢትዮጵያ የተጀመረው የለውጥ ሂደት ትልቅ ተስፋ ሰጪ ነው:: ይሄ አጋጣሚና ዕድል እንዳያመልጠን ደግሞ ሁላችንም በጥንቃቄ መያዝ አለብን ብዬ አምናለሁ:: የፖለቲካ ድርጅቶችም ይሄንን ኃላፊነት የተቀበሉ ይመስለኛል:: ወደ ፊት ዋና ዓላማ መሆን ያለበት የእኔ ድርጅት ስልጣን ላይ ይወጣል የሚል ሳይሆን በተገኘው የለውጥ አጋጣሚ ተረማምደን ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በመፍጠር ለቀጣይ ትውልድ የተረጋጋችና ፍትሃዊ ሀገር በመመስረት ላይ ብቻ ብናተኩር መልካም ነው እላለሁ::

ምርጫው በተለይ ዴሞክራቲክ ሆኖ ማጭበርበር የሌለበት በትክክል የተካሄደ ምርጫ እንዲሆን እንፈልጋለን:: እንመኛለን:: በፓርላማው ትክክለኛና ህዝባዊ የሆነ አዲስ ፓርላማን፤ትክክለኛ ስርዓትን እንድንፈጥር ነው የምመኘው፤ ይሄን በህይወቴ አይቼ ካለፍኩ ለእኔ ትልቅ ነገር ነው::

**ግዮን፡- እናመሰግናለን::**

# ባንዲራና እንጀራ

ከኢትዮጵያና ከፈጣሪ ማንን ቀድሜ እንዳወቅኩ፣ ማን ቀድሞ በህሊናዬ እንደተሳለ በትክክል ለመናገር ያዳግተኛል፤ ከቤታችን ግድግዳ ላይ የተለጠፈውን የድንግል ማርያም ምስልና ወንድሞቼ ደብተር ሽፋን ላይ ያለውን የኢትዮጵያ ካርታ በተቀራራቢ እድሜ ነው ልብ ያልኳቸው። የማርያምን መቀነት ሰማይ ላይ ከማስተዋሌ አስቀድሞ፣ የመመገቢያ ትሪያችን መሀል ላይ፣ አንበሳ ያነገበው አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ የኢትዮጵያ ባንዲራ ልቤ ገብቷል። ማርያም መቀነቷን ሰማይ ላይ የምታሰጣው ዘንቦ ሲያባራ፣ ፀሐይ ብልጭ ሲል አልፎ አልፎ ነበር። ባለባንዲራው አንበሳ ግን ቢያንስ በቀን አንዴ ከፊቴ ይቀርብ ነበር። ባንዲራ እንኳን ከእንጀራ ጋር ቀርቦ፣ ተሰቅሎ በንፋስ ሲውለበለብ ያጠግባል።

*በድሉ ዋቅጅራ*

# የክፉ ቀን ወዳጅ - ኢሳት

ዓለም ተለዋዋጭ ነው። ከልዋጩም ጋር የሚሄደውና የሚመጣው እልፍ ነው። የካቻምናው፣ አምና አልነበረም፤ የአምናው፣ ዘንድሮ የለም። የዘንድሮ እያለ፣እያለ ይቀጥላል። ቴክኖሎጂውም (የት ለመድረስ እንደሁ እንጃ) ፍጥነቱ አይጣል ነው። ባለፉት ሀምሳ ዓመታት ጉልበተኛና እርጉም መንግሥታትን ለመከስከሻነት የተተገበረው ስልትም ተቀይሯል። ብረት-ነካሹ አመጽ፣ በዘናጩ የቀለም አብዮት ተተክቶ ጫካና ነፍጥ ወደ ውስጥ ተብሏል። ለአረብ ስፕሪንግ ፌስቡክና አልጀዚራ የማይተካ ሚና ነበራቸው። ወያኔን እንዲህ እንደ ዛሬው ተረት በማድረጉ ግብግብስ ማን እንደ ኢሳት! ገፀ-ስውሩ ጌታቸው አሰፋ፣ ኢሳትን ለማፈን ያል'ፈሳበት' ተራራ የለም። እንደው ልፋ ቢለው እንጂ፣ሕዝብን ከቶም ማሸነፍ አይቻልም-ከሚዲያው ጀርባ ነበርና።

"በኢንስ" መሥሪያ ቤት ፊታውራሪነት ማስራጫ ጣቢያው ተደጋጋሚ ጊዜያት ጃም ቢደረግም፣ ኢሳት እንደ በረሃው ዘመን ቆንጥር ለቆንጠር ዘሏል (ከአረብ ሳት ወደ ናየል፤ ከፍሪኪዌንሲ ወደ ፍሪኪዌንሲ፣ ከአየር ወደ አየር...) በርግጥ ዛሬ ጌቾ እድለኛ ነው፤መብቱ ቢረገጥ፣ እስር ቤት (አይቀርለትም ብዬ ነው) ስቃይ ቢደርስበት የሚጮኽለት ኢሳት አለለት። ኢሳት ውሉም ሆነ ውገናው ከሕዝብ ጋር ነው፤ ይህ ትላንት ያየነው ሀቅ ነው (ለዚህ ደግሞ አንደኛ ምስክር እኔው እራሴ ነኝ፤በዝዋይ ማጎሪያ በወንድሜ ላይ ይፈጸም የነበረውን የመብት ጥሰት ከኢሳትና ቪኦኤ በላይ የሞገተ ሚዲያ አላታውስም) በመጨረሻም እንሆ የኢሳት ካፒቴኖች ወደምትወዷት እናት አገራችው በሰላም ትገቡ ዘንድ የዘንባባ ዝንጣፊ ይዤ እመኛለሁ።

*የካቲት ዘጠኝማ ማን ይቀራል?! በሚሊንየም አዳራሽ*

*ታሪኩ ደሳልኝ (ሚኪ)*

# ጉዞ ወያኔ!


እኔ የትግራይ አክቲቪስቶችን ብሆን ኖሮ ጉዞ አድዋን ከመቃወምና ለፌስቡክ ጥላቻ ስነታሪክ ከመዋል ይልቅ ከደደቢት ተነስቶ አራት ኪሎ ቤተ መንግሥት የሚጠናቀቅ "ጉዞ ወያኔ" የሚል የእግር ጉዞ አዘጋጆች የማምንበትን ታሪክ እዘክር ነበር ፤ በዛውም ባለፍኩበት መንገድ ላይ ለማገኘው ሕዝብ ስለትግራይ ሕዝብ እውነተኛ ማንነት ሐሳብና አመለካከት እያሳወኩ ፌስቡክ ላይ የሚዘራውን ጥላቻ እያፈራረስኩ፤አስባችሁታል "የጉዞ ዓድዋ" ሰራዊት ወደትግራይ ተሰልፎ ሲተም ፣ የጉዞ ወያኔ ሰራዊት ወደ አዲስ አበባ ተሰልፎ ሲጓዝ ደሴ ላይ ይገናኛል፤ ሕዝቡ ሁለቱንም በእልልታ ተቀብሎ በደስታ ተገባብዞ ሁለቱም ሰራዊት አብሮ ራት በልቶ ታሪኩን አውርቶ ልዩነቱ ላይ ተከባብሮ የጋራውን ነገር አጥብቆ በጋራ ጀግኖቹን ዘክሮ በፍጹም ሰላም ሲተላለፍ ?!

*አሌክስ አብረሃም*

# I have a dream - ህልም አለኝ !

ትውልደ ኢትዮጵያዊው አሌክስ አሰፋ በአሜሪካ ኔቫዳ ክፍለ ግዛት የምክር ቤት አባል ሆኖ መመረጡን ስንሰማ ሁላችንም ደስ ተሰኝተናል ፡ ቁጭትም ገብቶናል። ዛሬ ኢትዮጵያውያን ከአንድ ክልል ወደ ሌላው ተዟዙረው የፓለቲካ ስልጣን ማግኘት ሳይሆን መኖር እና መነገድ ሁሉ የማይችሉበት ሁነት ውስጥ ገብተናልና ።

ትናንት አድዋ ፣ ካራማራና ባድመ ሄዶ ህይወቱን ለመገበር ብሄሩን ያልተጠየቀው ኢትዮጵያዊ ዛሬ መታወቂያና ስራ ለመያዝም ከየትኛው ወገን ነህ ሲባል ይሞገታል። ከዚህ በመረረ ደግሞ ከክልላችን ውጣ እየተባለ እድሜውን ሙሉ ለፍቶ ያካበተው ይዘረፋል ፣ ይሰደዳል ቀኑ ካልሆነም ክቡር ህይወቱን በግፍ ያጣል ።እኛም የአሌክስን የኔቫዳ ስኬት እያሰብን ልጅ ልጆቻችን ደምና አጥንታቸው ሳይቆጠር በነጻነት የሚኖሩባት አማራ ተወልደው ኦሮሚያ ላይ ስልጣን የሚይዙባት



፣ ኦሮሚያ ተወልደው ትግራይ ላይ ነግደው የሚከብሩባት ፣ ትግራይ ላይ ተወልደው ደቡብ ላይ ተፋቅረው የሚኖሩባት ኢትዮጵያ ትመጣ ዘንድ ህልም አለን We have a dream !

I have a dream ብሩህ ቀን ይመጣ ይሆናል

*ሳምሶን ሚሀሎቪች*

# የሚዲያዎቻችን ዝግመት

በደቡብ ጎንደር ስለደረሰው የመስጂድ ቃጠሎ ሚዲያዎች የዘገቡበት ፍጥነት አጥጋቢ አይደለም የሚል ወቀሳና ግብረ መልስ እየደረሰን ነው። ተገቢ ወቀሳ ነው። እግረመንገድም የጉዳዩን ሱሱነት፣ ጉዳዩ የተፈፀመበት አካባቢ ለመረጃ ተደራሽነት ያለው ቅርበት ግምት ውስጥ ቢገቡ ጥሩ ነው። ሚዲያዎቻችን ያሉበት፣ ያለፉበት የላሸቀ ሙያዊ ደረጃም ይታሰብ። እኔ ከዚህ በተሻለ ፍጥነትና ጥራት መስራት ይችላል ብዬ አስባለሁ። መማሪያ ይሆናል። የሀገራችን የዜና ዑደት በመኮራረጅና በመጠባበቅ ላይ የተመሰረተና ጉዳዩን ከምንጩ ማጣራት የሚችሉና የሚፈልጉ ሚዲያዎች ቁጥር ትንሽ ነው። ስንትና ስንት ትልቅ ዜና ሳይሰማ ሳይታይ ያልፋል። ይህ የአቅም ችግር በቅርቡ የሚፈታ አይመስልም። አክመል ነጋሽ Akemel Negash የሚዲያዎችን የዘገባ ዝግመት ከታች በምታዩት ምስል [አጋርቶናል]




*አርጋው አሽኔ*

## ማሌሊታውያን ግራ ገብቷቸዋል

ማሌሊታውያን ዛሬ ከአዲስ አበባ ስለተባረሩ "ኢትዮጵያ ለኛ አትሆንም፤ ትፍረስ" እያሉ ነው። ነገ ደግሞ ከመቀለ ሲባረሩ "ትግራይ ለኛ አትሆንም፤ ትፍረስ" ማለታቸው አይቀርም። ከፌደራል ስልጣን እንባረራለን ብለው አስበው አያውቁም። ግን ሆነ። ከክልል ስልጣን እንደሚባረሩም ላይገነዘቡ ይችላሉ። ግን ይባረራሉ። የተፈጥሮ ህግ ነውና አይቀርም። እናም ፀረ ኢትዮጵያ የተነሱ ያህል ፀረ ትግራይም ይነሳሉ። ግን እናሸንፋለን! ሀገሬን እወዳለሁ። በዳዮቿን አልታገስም!

*አብርሃ ደስታ*



ተስፋዬ ሽብሩ

# ከግጭቶች ጀርባ ያለው የሃይማኖት አጀንዳ

በአገሪቱ ላለፉት 27 ዓመታት ሲቀነቀን የነበረው የማንነት ፖለቲካ በሕዝቦች መካከል አንድነትን ከመፍጠር ይልቅ ልዩነትን በማጉላት እርስ በርስ ለመናቆርና ለመጋጨት ሰፊ በር ከፍቶ ዛሬ ለደረስንበት የመፈናቀል፣ የሕይወት መጥፋትና፣ የንብረት መውደም ምክንያት ሊሆን በቅቷል:: በብሔርና በጎሳ ላይ ያተኮረው የማንነት ፖለቲካ በጊዜ መፍትሄ ካልተበጀለት መጨረሻው ከዚህ የከፋ የሕዝቦች ዕልቂት ማስከተሉ አይቀርም:: በዚህ መንገድ የተጓዙ አንዳንድ አገራት የደረሰባቸውን ሰቆቃና ጥፋት ማስታወስ በቂ ነው::

ከብሔር ክፍፍሉ ባልተናነሰ ግጭቶችን ሃይማኖታዊ መልክ ለማስያዝ እየተደረገ ያለው ሙከራ በእንጭጩ ካልተቀጨ ማጣፊያው ወደ የሚያጥር የእልቂት መቀመቅ ውስጥ እንዳንገባ የፓለቲካ ታዛቢዎች ከወዲሁ ሥጋታቸውን ያጋራሉ:: እነዚህ ወገኖች ቢሰጉ የሚገርም አይሆንም :: ሕወሓት መራሹ መንግሥት የተከለው ጎሳ እና ማንነት ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ መንገድ ስር ሳይሰድ በጅምሩ እንዲጨነግፍ ቢደረግ ኖሮ ዛሬ ለገጠመን ውርደትና መከራ አንዳረግም ነበር:: የሃይማኖት ኢ-ምክንያታዊነትን እና ተጠያቃዊነትን ገሸሽ ማድረግ፣ የራስን ሃይማኖት በማግነን ጭፍን አስተሳሰብን ለማራመድ መንገድ ሊከፍት ይችላል:: "የእኔ ብቻ" በሚል ሚዛኑን የሳተ አመለካከት እና ፍላጎት የሌለውን መብት በመደፍጠጥ በኃይል ወደ ማስገደድ ሊወስድ ይችላል::

ኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት አጀንዳ አደገኛ አዝማሚያ ሊይዝ የሚችልበት ዕድል በርካታ እንደሆነ ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው አካላት ይናገራሉ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖተኛ ሕዝብ ነው፣ ለሃይማኖቱ ቀናኢ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖቶች መኖራቸው ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ የሃይማኖት ተከታዮች ቁጥር አጨቃጫቂ መሆኑ ሌላው ችግር ነው:: "በቁጥር የኔ ይበልጣል፣ የእከሌ ሃይማኖት ይበልጣል" የሚለው እሰጣ ገባ ጎልቶ ባይወጣም ይዞት የሚመጣው አደጋ ስለመኖሩ ግን መገመት አያስቸግርም::

በአንዳንድ አካባቢዎች ሃይማኖትና ብሔር እርስ በርስ ተቆራኝተው መገኘታቸው ሌላው ችግር ነው:: ለምሳሌ ሶማሌ፣አፋር እና አንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እስልምናና ብሔርን ነጥሎ መመልከት ያስቸግራል:: ብሔርና ሃይማኖቱ በማይነጣጠሉበት አካባቢዎች እምነትን በኃይል የመጫን ዝንባሌ ሊታይ ይችላል::

ሰሞኑን በደቡብ ጎንደር መካነ ኢየሱስ በተባለ ቦታ ሁለት መስጊዶች ተቃጥለዋል:: በመስጊዱ የሚዘጋጅ የሠርግ ሥነ ሥርዓት በመካሄድ ላይ እያለ ሰርጉን የማስጌጫ ወረቀት ውስጥ ተገኘ በተባለ የእመቤታችን ሥነ ስዕል ጋር በተያያዘ በተፈጠረው አለመግባባት ግጭት ተከስቶ ነበር፣አለመግባባቱ ከተፈታ በኋላ መስጊዶች መቃጠላቸው ታውቋል::

የአማራ ክልል እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት በመስጊዱ ላይ የደረሰው ቃጠሎ ኢትዮጵያ ሰላም እንዳትሆን በሚፈልጉ አካላት የተፈፀመ፣ በሙስሊሙና በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ መካከል ሰላምን ለማናጋት የታለመ ጥቃት መሆኑን አስታውቋል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ መግለጫ አውጥቷል:: በማንኛውም የእምነት ተቋማት የሚፈጸም ይህን መሰል ተግባር በሀገራችን ለዘመናት በሰላምና በመከባበር ጠንካራ አብሮነት ገንብተው በሚኖሩ የእስልምና እና የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ላይ የተቃጣ ክፉ ድርጊት በመሆኑ ዜጎች በጽናት ሊቃወሙት እና ለሁሉም የእምነት ቦታዎች ጥበቃ ሊያደርጉ ይገባል፣ በማለት አሳስቧል::

የተፈጸመው ድርጊት በሃይማኖት ኃጢያት ፣በሕግ ደግሞ ወንጀል ስለሆነ አስፈላጊውን የሕግ ማጣራት በማድረግ ድርጊቱ ላይ የተሳተፉ አካላት ለሕግ እንዲቀርቡና ችግሮቹ ዳግም እንዳይከሰቱ መንግሥት ተገቢውን ሃላፊነቱን እንዲወጣ፣ አንዳንድ ኃላፊነት የጎደላቸው ግለሰቦችም በማኅበራዊ ሚዲያ አላስፈላጊ የጥላቻ ቅስቀሳ የሚያደርጉ አካላት ጥፋትን በሌላ ጥፋት ማካካስ እንደማይቻል ተገንዝበው ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ተጠይቋል::

> ከለውጥ ኃይሉ በተቃራኒ የቆሙ አካላት አሁንም ሙሉ በሙሉ አልተሸነፉም:: የሕዝቦችን ሰላም ለማናጋት አቅም ያንሳቸዋል ብሎ መገመት አደገኛ ነው

እንዲህ ዓይነት ከሃይማኖት ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ ጥቃቶች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአገሪቱ አንዳንድ ከተሞች በተደጋጋሚ እየተስተዋሉ ነው:: በቅርቡ ጥር 21 ቀን 2011 ዓ.ም በሶማሌ ክልል በጅግጅጋ ከተማ የሃይማኖት ክብረ በዓልን ተከትሎ በተፈጠረ ግጭት ጅግጅጋን ጨምሮ በክልሉ የተለያዩ ከተሞች 96 ሰዎች መገደላቸው እና ለግድያውም "ሄጎ" ተብሎ የሚጠራው ታጣቂ ቡድን ተጠያቂ እንደሆነ በወቅቱ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን መግለፁ ይታወሳል::

በድሬዳዋም ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ የሚመስል ጥቃት በዜጎች ላይ ለመፈጸም ተሞክሯል:: የእግዚአብሔር አብ ታቦት ሲሸኙ በነበሩ ሕዝበ ክርስቲያን ላይ በተፈጠረ ጥቃት ግጭቱ ለቀናት መዘለቁ ይታወቃል:: በዚሁ መነሻነት በድሬዳዋ የወጣቶች ጥያቄ እየሰፋ መጥቶ የሥራ አጥነት፣ የመልካም አስተዳደር፣ የፍትሕና የእኩልነት ጥያቄዎች ጎልተው በመውጣት ድሬዳዋን ሲንጧት ከርመዋል:: ወጣቶች በጥያቄያቸው "የድሬዳዋን ፍቅር አታደፍርሱ" "በብሔር አትከፋፍሉን" "40/40/20" የተሰኘው የአስተዳደር ቀመር "ይውደም" የሚሉ ተቃውሞዎችን በስፋት ሲያስተጋቡ ከርመዋል::

እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ የብዙ ብሔሮች እና ሃይማኖቶች አገር ነች:: የሃይማኖትም ሆነ የብሔር ማንነት በቀላሉ ተቀጣጣይ እና ስሜት ቀስቃሽ በመሆናቸው ሕዝብን ወደ አልተፈለገ ግጭትና እልቂት ሊያስገቡ የሚችሉበት ዕድል ሠፊ ነው:: የሃይማኖት አክራሪነት የሚፈጠረው ደግሞ አንድን እምነት በኃይል እና በግድ ሌላው ላይ መጫን ሲጀመር ነው:: ይህም ለግጭቶች ሰፊ መንገድ በመክፈት ዜጎችን ከብሔር አልፈው ሌላ ተጨማሪ የመለያያ መንገድ በመክፈት ወደ ዕልቂት ይገባሉ::

ኢትዮጵያ ውስጥ የሃይማኖት ግጭት ከሌሎች አገራት አንፃር ሲታይ ብዙ የጎላ ነው ማለት ባይቻልም፣ ምልክቶች ግን እየታዩ ነው:: ድሬዳዋ፣ ጅግጅጋ እንዲሁም ጎንደር ላይ የተፈፀሙት ድርጊቶች ባብዛኛው ሁኔታዎችን ወደ ሃይማኖት አጀንዳነት ለመለወጥ የታሰቡ ይመስላሉ::

ከለውጥ ኃይሉ በተቃራኒ የቆሙ አካላት አሁንም ሙሉ በሙሉ አልተሸነፉም:: የሕዝቦችን ሰላም ለማናጋት አቅም ያንሳቸዋል ብሎ መገመት አደገኛ ነው:: ለነዚህ አካላት የዜጎችን ሰላም ለማወክ ከሃይማኖት አጀንዳ በላይ የግጭትና የብጥብጥ መፍጠሪያ ስስ ብልት ሊኖር አይችልም::

በቀላሉ ተቀጣጣይ የሆነውን የሃይማኖት ጉዳይ ዜጎችም ሆኑ መንግሥት ትኩረት ሰጥተው ሊሰሩበት ይገባል:: የሃይማኖት አባቶች ፣የአገር ሽማግሌዎች በጋራ ኅብረተሰቡ ከዚህ ዓይነት የአገርና የማኅበረሰብ በታችና ከፋፋይ ዝንባሌ ተላቆ የጋራ አገሩን በጋራ ለማቆምና ለማሳደግ እንዲተጉ ዘወትር ቢያሳስቡ ምንጩን ማድረቅ ይቻላል::

# ዘመናችንን ዘካሪ ጨዋታዎች



በኃይሉ ገ/እግዚአብሔር

ዘመናችንን እንዘክራለን። አዎ! በእለት ተእለት ወጋችን፤ በፍቅር ትርክታችን፤ በእንጉርጉሯችን፣ በሙሿችን፣ በቅብብሎሻችን፣ በተረካችን፣ በተረታችን፣ በአጫጭር ጨዋታዎቻችን፣ በእንካ ሰላንትያችን፣ በበላ ልበልሃችን፣ በዘይቤያዊ አነጋገራችን ሁሉ ዘመናችንን እንዘክራለን።

ከአንድ ሣምንት በፊት ‹‹ዘመንን በቃላዊ ግጥሞች›› በሚል ርዕስ የዘመኑ ስዕል ይሆናሉ ብለን ያሰብናቸውን መንቶ ግጥሞችን ጽፈን ነበር:: ዛሬ ደግሞ ባለታሪኮቻችንን እናቶችን ብቻ አድርገን፣ የዕለት ተዕለት ኑሯችንን የሚያሳዩ አጫጭር ጨዋታዎች እንዲህ መርጠን እነሆ እንላለን፤

**ጨዋታ አንድ፡-**

የወር ደመወዟን በተቀበለች ማግሥት፣ የገዛችውን ልብስ በፌስታል ይዛ ድንገት ቢሮ ገባች። የሥራ ባልደረቦቿ ከበቧት::

‹‹ምን ገዛሽ? ምን ገዛሽ?›› ጉጉት በፈጠረው ጩኸት ጠየቁ::

‹‹እንዴ! ልብስ ነዋ!›› በኩራት መለሰች::

‹‹እስኪ እባክሽ አሳዩን!?›› የደስደስ ሊጋበዙ የፈለጉም ያልፈለጉም አዲሱን ልብስ ለማየት በብርቱ ጓጉ፤ ‹‹እባክሽ አሳዩን!?››

‹‹እኔ አምስት የለኝም! ሙሉ ደመወዜን ልብሱ ላይ ነው ጥዬው የመጣሁት!›› አለች የዋኋ በእፍረት የደበዘዘ ፈገግታ እያሳየች።

በቢሮው ያልተጻፈ ደንብ፣ እንደ ልብስ እና ጫማ ያለ ወረት የሸመተ ሠራተኛ፣ ለሥራ ባልደረቦቹ የሆነ የሚበላ ወይም የሚጠጣ ስጦታ መግዛት አለበት::

‹‹ግዴለም ይሁን፤ ልብሱን እንየው ብቻ!›› ተመልካች አጥብቆ ወተወተ::

‹‹ምን አስቸኮላችሁ! ስለብሰው ታዩኝ የለ!›› ተግደረደረች።

‹‹አሁን ብናየው ምን ችግር አለው!?››

ሴቲቱ ውትወታው ቢበረታባት ፌስታሉን ከፍታ፣ በጋዜጣ ተጠቅልሎ የመጣውን ልብስ አወጣች።

ጋዜጣው ሲፈታ ግን የተገኘው፣ ረዥም ሰዓት ተከራክራ የገዛችው አዲሱን ልብስ ሳይሆን ብጥቅጥቅ ያለ መናኛ ጨርቅ ሆኖ ተገኘ።

በድንጋጤ ክው አለች፤ ድርቅ ብሎ እንደመቅረት ዓይነት። በደመ ነብስ አሮጌውን ጨርቅ አንጠልጥላ ወደገዛችበት ገበያ በፍጥነት በረረች።

ከወዳጆቿ መሃል ገሚሶቹ እየሳቁ ነው፤ ገሚሶቹ ደግሞ እያዘኑ። …የዛሬው የቢሮዋ ሴቶች መዋያ አጀንዳ እሷው ናት።

ያልታደለችው ከሄደችበት አረፋፍዳ መጣች። ቢሮዋ፣ በተሠራችው ጉድ ባዘኑና ይህን፣ ‹‹አዝናኝ›› ዜና ከቁስለኛዋ አፍ መስማት በፈለጉ ሰዎች ተሞልቷል።

‹‹እህስ?›› አሉ ባልደረቦቿ፣ ያዘነው በማዘን፤ ለመዝናናት ያሰበው ፈገግ ለማለት እየተሰናዳ፤ ‹‹እህስ? አጭበርባሪውን አገኘሽው!?››

‹‹አላገኘሁትም!›› አለች ያልታደለችው እንባ እያነቃት።

‹‹እና ዝም ብለሽ መጣሽ!?››

ፀጥ አለች አንገቷን እንደሰበረች።

‹‹ዝም ብለሽ መጣሽ ወይ?›› ወተወቷት የሥራ ባልደረቦቿ።

‹‹ለነገሩስ…›› አለች ያልታደለችው እያቅማማች፤ ‹‹ለነገሩስ ዝም ብዬ አልመጣሁም!››

‹‹እና ምን አደረግሽ!?››

‹‹’ወየው! ወየው! ወየው! ወየው ገንዘቤ!’ ብዬ ጮኼ መጣሁ!››

‹‹ምን አልሽ?›› አባባሏን ለጨዋታ ማሳመሪያ የፈለገው ሁሉ ጠየቀ::

‹‹’ወየው! ወየው! ወየው! ወየው ገንዘቤ!’ ብዬ ጮኼ መጣሁ!››

(አንድምታ፡- ለደረሰብህ በደል፣ ለደረሰብህ መገፋት፣ ከመጮኽ ውጪ መፍትሔ አልባ መሆንህ ሕመም ነው። መፍትሔ የለውም ብሎ አለመጮኽም የበረታ ሕመም ነው። ከሁሉም የሚፀናው ደግሞ ለተዋለብህ ግፍ ሁሉ እንዳትጮኽ መከልከልህ ነው። እርር አድርገው ቆንጥጠውት፤ ‹‹ዝም በል ዝም፤ አፍህን ያዝ!›› ብለው እንደሚቆጡት ህፃን ዓይነት።)

**ጨዋታ ሁለት፡-**

ልጂቱ፣ ‹‹ስንደመር ያምርብናል፤ ጠጋ ጠጋ በሉ!›› የሚል ጥቅስ የተለጠፈበት ታክሲ ፊቷ ቆሞ እየለመናት ነው::

‹‹እናቱ! ግቢ፤ የሞላ ታክሲ ነው!››

‹‹ከሞላማ አልገባም!››

‹‹ተይ እህት፤ ‹ስንደመር ያምርብናል› ግቢማ ዝም ብለሽ፤ ፍቅር ያሸንፋል!›› አጓጉል ወተወታት::

ልጂት አቅማማች:: የረዳቱ ፍቅር አዘል ልመናው ልቦናዋን ገዛው፤ ሰተት ወደ ውስጥ:: መቀመጫ በሌለው ታክሲ ውስጥ መቀመጫ ተጋራች:: …‹‹ስንደመር ያምርብናል!››

ልጂት በትርፍ ገብታ ከተቀመጠችበት ታክሲ ስትወጣ በድንጋጤ ቦርሳዋን በረበረች፤ ሰሞኑን የተቀበለችው ደመወዝም ሆነ ተንቀሳቃሽ ስልኳ በቦታው የለም:: ድርቅ፤ ፍዝዝ፤ ግትር:: የጨው ሐውልት የመሆን ዓይነት:: ‹‹ወይኔ ሞባይሌ! ኡ! ኡ!›› …ጩኸት ብቻ::

(አንደምታ፡- አንቺ ታክሲዋ አገሬ ሆይ፤ ወዴት እየሄድሽ ነው!?)

**ጨዋታ ሦስት፡-**

የመብራት አገልግሎት ሊከፍሉ ወደ መክፈያ ጣቢያ የሄዱ አንዲት አቅመ ደካማ እናት ናቸው:: መብራት ከሚመጣበት የሚቀርበት ጊዜ ቢበልጥም ላገኟት ትንሽዬ አገልግሎትም ቢሆን መክፈል አለባቸውና ወደ መክፈያው ቢሮ እየተጎተቱ ሄዱ::

‹‹እማማ መቶ ሃምሣ ብር!›› አለች ገንዘብ ተቀባይዋ የከፈሉበትን ኩፖን ተቀብላ ስማቸውን ኮምፒውተር ውስጥ ከፈለገች በኋላ::

‹‹ም… ም… ምን ልጄ?›› አሉ እናት ድምፃቸው በድንጋጤ ድንቅፍቅፍ እያለ::

‹‹አንድ መቶ ሃምሳ ብር!›› መለሰች ገንዘብ ተቀባይዋ እየተሳቀቀች::

‹‹ልጄ!››

‹‹አቤት እማማ!››

‹‹ከዚህ ቀደም፣ ከስድሳ ባውንድ በላይ ተጠይቄም አላውቅ እኮ!?›› አሉ ሐዘን በተጫነው አሳዛኝ ዜማ:: (ከስልሳ ብር በላይ ከፍዬ አላውቅም ማለታቸው ነው::)

‹‹እናቴ አሁን ጨምሯል!››

‹‹ማነሽ ልጄ!?›› እናት ተጣሩ በዝግታ::

‹‹አቤት እማማ!›› አለች ገንዘብ ተቀባይዋ ጆሮዋን ወደ ባልቴቷ እያስጠጋች::

‹‹ለጨለማም ማስከፈል ጀመራችሁ እንዴ!?››

‹‹ምን አሉ እማማ!?››

‹‹ለጨለማም ማስከፈል ጀመራችሁ ወይ!? …የተጠየቅኩት ከተጠቀምኩበት ከበለጠ፣ የምከፍለው ለጨለማው ነው ማለት ነው!››

(አንድምታ፡- ለአንባቢ የተተወ)

**ጨዋታ አራት፡-**

አንዲት እናት አለች:: ነፍሰ ጡር ናት:: ሁሌ ማንኛውም ወረፋ ላይ፣ ‹‹እባካችሁ አስቀድሙኝ፤ ነፍሰ ጡር ነኝ!?›› እያለች ቅድሚያ ማግኘት ልማዷ ነው:: እንደለመደችው ዘይት ልትገዛ ሸማቾች ማኅበር ሔደች:: የሸማቾች ማኅበር ደጃፍ በወረፋ ተጨናንቋል::

‹‹እባካችሁ አስቀድሙኝ!?›› አለች ሴቲቱ እንደለመደችው::

‹‹ለምን?›› ስትል ጠየቀች አንዲት የሰፈሯ ሴት በመታከት::

‹‹ነፍሰ ጡር ነኝ!››

‹‹ወይ ጉድ!›› አለች ልጂቱ በብስጭት፤ ‹‹ወይ ጉድ! ይህቺ ሴትዮ ማርገዝን የፓርቲ መታወቂያ አደረገችው እኮ!››

(አንድምታ፡- ‹‹የሹም ዶሮ ነኝ፤ እሽ አትበሉኝ›› ባይ በዛብን እንደማለት::)

**ጨዋታ አምስት፡-**

ትምህርት ቤታቸው የብሔር ብሔርሰቦችን ቀን እንዲያከብሩ ያዘዛቸው የቅጠል ሰፈር ተማሪዎች ከወገባቸው በላይ ራቁታቸውን ሆነው፣ ሰውነታቸውን አፈር እና ኖራ ቀብተው ወደ ትምህርት ቤት ሲሔዱ አንዲት እናት መንገድ ላይ አገኟቸው።

‹‹ልጆቼ!››

‹‹አቤት እማማ!››

‹‹እንዲህ ፀበልተኛ መስላችሁ ወዴት እየሔዳችሁ ነው?››

‹‹ትምህርት ቤት!››

‹‹ለምን ልጆቼ?››

‹‹የብሔር ብሔረሰቦችን በዓል ልናከብር!››

እናት እዝን አሉና እንዲህ አሉ፤ ‹‹አይ አንተ መንግሥት! ትንሽ ትልቁን ጨርቅ አስጥለኸው ቀረህ ማለት ነው!?››

(አንድምታ፡- ለአንባቢ የተተወ)

# “የኢትዮጵያ ፖለቲካ የዝንጀሮ ፖለቲካ ነው”

## “ኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠሏን አምኜ አላውቅም”

## ፕ/ር ፍስሃጽዮን መንግሥቱ

*አንጋፋው ፕሮፌሰር ፍስሃጽዮን መንግስቱ ከወጣትነታቸው ጊዜ አንስቶ በሀገር ውስጥና በውጭው ዓለም ለበርካታ ዓመታት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ከፍተኛ እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡ ከኮ/ል ጎሹ ወልዴ ጋር በመሆንም መድህን ፓርቲን በአሜሪካና አውሮፓ መስርተዋል፡፡*

*ወደ ሀገር ቤት ከገቡ በኋላ በተማሩበት የትምህርት ዘርፍ ሕዝብና ሀገራቸውን ማገልገል በመምረጣቸው ለዓመታት አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን ጨምሮ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች በመምህርነት አገልግለዋል፡፡ ለመሆኑ ፕሮፌሰር ፍስሃጽዮን መንግስቱ ከምን ተነስተው የት ደረሱ የሚለውን የግዮን ጋዜጠኛ ፍቃዱማ/ወርቅ እንዲህ ባለመልኩ ያስቃኘናል፡፡ መልካም ቆይታ፡፡*

**ግዮን፡- ፕ/ር ፍስሃጽዮን መንግስቱ ማን ናቸው ለሚሉ አንባቢያን በቂ መረጃ ያገኙ ዘንድ፤ የት እንደተወለዱ፣ ዕድገትና ትምህርትዎ ምን እንደሚመስል ቢገልፁልን?**

**ፕ/ር ፍስሃጽዮን፡-** መልካም::አሁን ኤርትራ በምትባለው ሰሜን አካባቢ በስራዬ አውራጃ አዲ መንጎቲ የምትባል የመኳንንት መንደር ተብላ ትጠራ በነበረው አካባቢ በጥር 19 1947 እ.ኤ.አ ነው የተወለድኩት:: እኔ በፊትም፣ አሁንም ኤርትራ ከኢትዮጵያ መገንጠሏን አምኜ አላውቅም:: ሕዝቡ አንድ ቤተሰብ ነው፤ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል አስመራ ነው የተማርኩት:: ከኢሳይያስ አፈወርቂ ጋር አንድ ት/ቤት ነው የተማርነው፤ እኔ ልዑል መኮንን ት/ቤት (አስመራ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት) ነው የተማርኩት::

ከድሮ ጀምሮ በት/ቤት ውስጥ የዲሲፕሊን ሰው፣ የተማሪዎችም አለቃ ነበርኩኝ:: አንድ ዩኒቨርስቲ ብቻ ስለነበር በእኛ ጊዜ፣ በዛ ዕድል ለመጠቀም ስድስት ወር ያህል ት/ቤት እያደርን፣ እያጠናን በጣም ታግለን ነው ዩኒቨርስቲ ለመግባት የቻልነው:: አስራ ሁለተኛ ክፍል 27 ተማሪዎች ብቻ ያለንበት አንድ ክላስ ብቻ ነበር፤ ዘጠነኛና አስረኛ ግን አምስትና አራት ክፍል ያለው የተማሪዎች ብዛት እንደነበር አስታውሳለሁ::

**ግዮን፡- እርስዎ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውጤት ሲያመጡ አስመራ ዩኒቨርስቲ ተቋቁሞ ነበር? ቀጣይ ትምህርትዎንስ የት ነበር የተከታተሉት?**

**ፕ/ር ፍስሃጽዮን፡-** አስራ ሁለተኛ ክፍል ስጨርስ አስመራ ዩኒቨርስቲ አልነበረም:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ነው የተመደብኩት:: በዛ ጊዜ ምንም እንኳን በሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጥሩ ማርክ ብታገኝም፣ በአማርኛ ሲ ካላመጣህ ዩኒቨርስቲ አትገባም :: ስለዚህ ሁላችንም (ብዙ ያለፈ ሰው አላስታውስም) የክረምት ኮርስ ገብተን፣ ለምሳሌ እኔ ዲ የነበረውን ማርክ ወደ ቢ አሻሽዬ ነው ዩኒቨርስቲ የገባሁት::

በዛን ጊዜ ነው ትግሪኛ ተናጋሪው “ለምን በአማርኛ ብቻ ይሆናል” የሚል ቅሬታ ማንሳት የጀመረው:: እኔ ለነገሩ ምንም ግድ አልነበረኝም፤ ግዕዝ መሰረቱ ነው፤ ስለዚህ አማርኛና ትግርኛ መነጋገር ወይም ደግሞ አማርኛ የኢትዮጵያዊነት ቋንቋ ስለነበረ ምንም አልተሰማኝም:: ሌሎች ጓደኞቼ ግን ቁጭት ነበራቸው ማለት እችላለሁ::

የትግራይ ነፃ አውጪም ሆነ የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባርን አንዳንድ ሰዎች ሊቀላቀሉ የቻሉት እንደዚህ ዓይነት ሀሳብ ስለነበራቸው ይመስለኛል:: በአማርኛ መናገር የአማራን የበላይነት ያሳያል የሚል ግንዛቤ አሳድረው ነበር:: እኔ ግን እንደዛ ዓይነት ሀሳብ አልነበረኝም:: ምክንያቱም አንድን ቋንቋ ብንወደውም፣ ባንወደውም ሁላችንንም የሚያገናኘን ቋንቋ የግድ ያስፈልጋል ብዬ ስለማምን:: አንድ ሀገር አለን ካልን፣ ስለ አንድነት ካወራንና ካመንን ሁላችንም የምንገናኝበት አንድ ቋንቋ ያስፈልጋል:: እንደ አጋጣሚና የታሪክ ጉዳይ ሆኖ አማርኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሆነ:: አማርኛ የአማራ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ቋንቋ ነው ብሎ ማመን ተገቢ ይመስለኛል:: በዚህ የተነሳ እንደውም አንዳንድ ጊዜ ጓደኞቼ ‹‹አማራህይዝድ ነህ›› ይሉኛል::

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከገባሁ በኋላ ህክምና ለማጥናት ፈልጌ ነበር፤ ግን ትንሽ በሰው ስጋ ላይ መመራመሩ ስጋት ስለነበረኝ ለምን ሕግ አላጠናም በሚል ወደ ህግ ትምህርት ሄድኩኝ:: ከክፍልህ ምርጥ አስር ተማሪዎች መሀል አንዱ ካልሆንክ የህግ ትምህርት ዘርፍ መግባት አትችልም፤ ይሄ ችግር እንዳይገጥመኝ አስራ ስድስት ሰዐት በቀን እያጠናን ነው ብዙዎቻችን ህልማችንን ዕውን ያደረግነው::

**ግዮን፡- መቼ ነበር ከዩኒቨርስቲ ተመርቀው የወጡት? ከዛ በኋላስ ወዴት ሄዱ?**

**ፕ/ር ፍስሃጽዮን፡-** እ.ኤ.አ 1973 ነው ከዩኒቨርስቲ ተመርቄ የወጣሁት:: ወደ ሥራ ዓለም የገባሁት ገና ሳልመረቅ ነው፤ ገንዘብ ሚኒስቴር ተቀጥሬ ነበር:: ብዙ ጊዜ እሰራ የነበረው በታክስና ኢንቨስትመንት ፋይናንስና የዓለም አቀፍ ሕግ ላይ ነው:: ስለዚህ ሕግ የሚያውቅ ሰው ይፈልጉ ስለነበር ከገንዘብ ሚኒስትር ቀጥሎ ሀገር ውስጥ ገቢ ገባሁ::

ከዩኒቨርስቲ ተመርቄ ከወጣሁ በኋላ ደግሞ በኤክሳይስ ታክስ ዲፓርትመንት የሕግ አማካሪ፣ የሚኒስትሩም አማካሪ ነበርኩ:: ፐብሊክ ፖሊሲ ታክሴሽን ኢንቨስትመንት ፋይናንስ በሚመለከት ማለት ነው:: ►



**ግዮን፦- በአፄ ኃይለ ሥላሴ ጊዜ የነበርዎት ትልቅ ኃላፊነት ምን ነበር?**

**ፕ/ር ፍስሃጽዮን፦-** አማካሪነት ነው ትልቁ ሥልጣኔ፤ በዕድሜ ወጣት ነበርኩኝ:: ከዩኒቨርስቲ ስመረቅ 400 ብር በገንዘብ ሚኒስቴር እየተከፈለኝ፣ 50 ብር በስኮላርሽፕ እየተሰጠኝ ልክ እንደ ንጉሥ ነበር የምኖረው:: በጊዜው እኮ "መሬት ላራሹ" ስንል የእኛ ጥያቄ አልነበረም፤ እኛ በጣም ሀብታሞች የነበርን፣ ማጥናትና መማር ብቻ ነበር ፍላጎታችን::

እኛ ሞቾት ላይ ብንሆንም ጥያቄው የብዙዎች ስለነበር ሀሳቡን ተቀብለን አስተጋብተናል:: በመሬት ላራሹ ላይ ቀዳሚ የመሪነት ሚና እንዳላቸው ሰዎች ሳይሆን በውይይትና በሀሳብ ነፃነት እንደሚያምን ሰው ሆኜ ታግያለሁ:: በዛ መንገድ ስኬታማ ሆኛለሁ አለሆኑኩም የሚለው ሌላ ጉዳይ ነው::

በኤርትራ ጉዳይ ላይ ከኢህአፓ መሪዎች ጋር የነበረኝ ግንኙነት እኔ በመገንጠሉ ሀሳብ ፍፁም ስለማልስማማ ፣ሲዋዥቁ ሳይ ለእነሱ ሀሳብ ምንም ፍላጎት አልነበረብኝም:: ግን ለውጡን እደግፋለሁ:: ስለዚህ እነሱን በመደገፍ እንደማንኛውም አባል ሆኜ አገልግያለሁ:: ሙሉ ለሙሉ የኢሕአፓ አባል ባልሆንም መሪዎቹ ጓደኞቼ ስለነበሩ እንደ እነሱ ሆኜ በተቻለኝ መጠን ለለውጡ ሠርቻለሁ:: በኤርትራ ጉዳይ ግን አልስማማም ብያለሁ::

**ግዮን፦- ከኢሳያስ ጋር በት/ቤት ደረጃ አብራችሁ አንድ ትምህርት ቤት የተማራችሁ እንደመሆናችሁ መጠን እሳቸውን እንዴት ይገልጿቸዋል?**

**ፕ/ር ፍስሃጽዮን፦-** አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከመጣን በኋላ እሱ ኢንጂነሪንግ መሰለኝ የገባው፤ እኔ ደግሞ ሕግ ክፍል:: ለምሳሌ በት/ቤት ሕይወት እኔ የሚረብሹ ሰዎች ካሉ አለቃ ሆኜ አሸዋ ላይ አንበረክካቸው ነበር:: የሚገርመኝ ኢሳይያስ በዛ ጊዜ በጣም ጨዋ፣ ረባሽ ያልነበረ ሰው ነው:: ግን የእሱ ጓደኞች እሱ ትግል ሲወጣ፣ እሱን አምነውና ተከትለው ጫካ ገብተዋል:: ለትግል የወጡ ሰዎች በብዛት በሕይወት የሉም::

ከማስታውሰው ጎይቶም በርሔ የሚባል ልጅ ዩኒቨርስቲ ህግ ፋክልቲ እያለሁ "ለምን ከእኛ ጋር ትግል አትሄድም?" ሲለኝ ፤ "አንደኛ ነገር የኤርትራን መገንጠል እቃወማለሁ፣ ሁለተኛ የምትገቡበት የማታውቁት ድርጅት ውስጥ ስለሆነ አልሄድም፣ ውጤቱን ታገኙታላችሁ" ብያቸው ነበር፤ እውነትም ጎይቶም በርሔን ጨምሮ የኢሳይያስ ብዙ ጓደኞች ጫካ ከገቡ በኋላ ተገድለዋል:: እኔም እስካሁን በህይወት የቆየሁት በእግዚአብሔር ፍቃድ እንጂ በጣም ብዙ ፈተናዎች ደርሰውብኛል::

ሻዕቢያ ከገባ በኋላም ቢሆን ብዙ ልጆች ተገድለዋል:: ይሄ ነገር በጣም ያሳዝነኛል፤ እንቅልፍም ይነሳኛል:: የሃሳብ ልዩነት ሊኖር ይችላል፣ ግን ሁላችንም የምንለፋው ለሀገርና ለወገን ከሆነ ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ መፍታት አይቻልም ወይ? የሚል አስተሳሰብ ነው ያለኝ::

**ግዮን፦- ሁለተኛ ዲግሪዎን መቼና የት ነበር የያዙት?**

ፕ/ር ፍስሃጽዮን፦- አብዮቱ እንደፈነዳ እንዳልካቸው መኮንን ጠ/ሚኒስትር ሲሆኑና አክሊሉ ሀብተወልድን ሲተኩ እኛ "ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥ" የሚል መስመር ያዝን፣ የሚሊተሪው የመምጣት እንቅስቃሴም ዓላማው ምን እንደሆነ አልገባንም ነበር:: ስለዚህ እኛ ገንዘብ ሚኒስትር የነበርን ሰባት ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ የገንዘብ ሚኒስትር ሠራተኞች አድማ ለማካሄድ ፈለግን::

በዛን ጊዜ ወታደሮችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው በጣም ፈሩና 4ኛ ክ/ጦር ጠርተው አነጋገሩን:: እኛ እኮ አላማችን እንዲህ ነው በሚል አስረዱን፤ እነሱም እኛም ወጣቶች ስለነበርን፤ እንደ እኔ የመሳሰሉ ሰዎች "ሀገር ማስተዳደር ማለት ቀላል አይደለም፣ ብቻችሁን አትችሉትም:: ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎችን ማሳተፍ ተገቢ ነው" የሚል ጥያቄ አነሳንላቸው:: እነሱ ይሄ ሀሳብ አልጣማቸውም:: "የእኛን ነገር የማትከተሉ ከሆነና አድማ ከተነሳ ወዮውላችሁ" አሉን::

እኔ በዛን ጊዜ ሁለት ስኮላርሽፕ ነበረኝ:: ኒውዮርክ ኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ ቢቀበለኝም ትራንስፖርት ራስዎ ይክፈሉ ተባልኩኝ:: እንግሊዝ ሀገር ግን ሙሉ ስኮላርሺፕ ሰጡኝ:: እነዛ ወታደሮች ባያስጠነቅቁኝና እግዜር ባያድነኝ ኖሮ መጀመሪያ መስራት የፈልግሁት ሀገሬ ነበር:: እሱ ባለመሆኑ እንግሊዝ ሊድስ ዩኒቨርስቲ በማቅናት በዚህ አጋጣሚ ነው ሁለተኛ ዲግሪዬን የያዝኩት::

ደርግን ከጅምር እንቅስቃሴው እዚህ ተቃውመነው ነበር፤ አውሮፓ ስደርስ ደግሞ እዛ ከነበሩ ኢትዮጵያውያን ጋር በመቀላቀል የበለጠ ተቃውሟችንን አጠናከርነው:: እዛ ዶ/ር ካሱ ኢላላ፣ ዶ/ር አብዱልመጅድ ሁሴን ፣ ፕ/ር ባህሩ ዘውዴን ከመሳሰሉ ሰዎች ጋር ደርግን በመቃወም ትልቅ እንቅስቃሴ እናደርግ ነበር:: ትንሽ የተማርን ስለነበርን ብዙዎቻችንን እንተዋወቃለን:: አስቀድሞ ወደ ሀገር ቤት የመጣው ፕ/ር ባህሩ ነው "አንተ ችግር ከገጠመህ እኛም እንጠነቀቃለን" በሚል እኛ እዛው ቀረን፤ በመጨረሻ ደርግ ሲወድቅ አብረውን ከነበሩት መሀል የተወሰኑት ኢህአዴግን ተቀላቅለው ኢትዮጵያ ሲመጡ እኔና አንድ ጓደኛዬ ግን በእንዲህ ዓይነቱ የብሔር ፖለቲካ ውስጥ አንገባም በሚል በራሳችን

መንገድ ቆየን:: ውጭ እያለሁ እየተማሩኩም፣ እየሰራሁም በሀገሬ ጉዳይ ላይ ግን ንቁ ተሳታፊ ነበሩኩ::

**ግዮን፡- ከእንግሊዝ በኋላ ወዴት ተጓዙ?**

**ፐ/ር ፍስሃጽዮን፡-** እዛ ሶስት ዓመት ከቆየሁ በኋላ ወደ ሆላንድ ነው የተጓዝኩት:: ሰላሳ ሶስት ዓመት ያህል ሆላንድ ኖሬያለሁ:: ትዳር የመሰረትኩትም በዚህ አጋጣሚ ነው:: ባለቤቴ በጣም የተማረች፣ እጅግ በጣም ጎበዝና የማከብራት ሴት ነች:: በትምህርት ላይ እያለን እንግሊዝ ነው የተገናኘነው:: እ.ኤ.አ በ1980 ሆላንድ ነው የተጋባነው:: ሶስት መጻሕፍት ጽፋለች:: ወ/ሮ አለም ደስታ ትባላለች፤ ስለ ሴቶች ጥያቄ የተለያዩ ርዕሶችን የሚያነሱ በጥናት ላይ የተመረኮዙ ሁለት የእንግሊዘኛና አንድ የአማርኛ መጽሓፍትን ለህትመት አብቅታለች::

እሷና እኔ የተለያየነው ልዩነት ስለነበረን አይደለም:: “አንተ የትዳር ሰው አይደለህም፣ ለሀገርና ለወገን ነው የምታስበው:: እኔ ግን የበለጠ ለትዳራችን ነው ትኩረት የምሰጠው” ትለኛለች:: በሀገሬ ጉዳይ መጠመዴ ቤተሰቤን የጎዳው ይመስለኛል:: የፖለቲካ ሕይወት ቀላል አይደለም፣ ብዙ መስዋዕት እንድትከፍል ያስገድደሃል፤ አጠገብህ ያሉ ሰዎች ይጎዳሉ:: “ያንን ሁሉ ጊዜ ተምረህ፣ ለሀገር ለወገን ስትል እኛን ወደ ኋላ አስቀረኸን” የሚሉ ሰዎች አይጠፉም::

የሚገርምህ ይሄን ሁሉ ጊዜ ተምሬ፣ ሠርቼ የምኖረው በኪራይ ቤት ነው፤ የማከራየው ነገርም የለኝም:: ለሀገርህ መስዋዕት ሆኖ መኖር ነው ውስጥህን የሚያረካው::

**ግዮን፡ስንት ልጆች አሏችሁ?**

**ፐ/ር ፍስሃጽዮን፡-** ሁለት ልጆች ወልደናል:: አሁን ለትምህርት ውጭ የሄደች አደይ ፍስሃጽዮን የምትባል ልጅ አለችኝ፣ እሷን እጅግ በጣም አደንቃታለሁ:: እንደሌሎች ሊፒስቲክ፣ መኳኳል ምናምን የለባትም፣ በተፈጥሮ ውበት የምታምን ናት:: ውጭ ነው የተወለደችው፣ ያደገችው፤ ግን ጥሩና ንፁህ ሀበሻ ናት:: አማርኛ በጥቂቱ ያስቸግራታል እንጂ:: እኛ ሀገር ያሉ የሀይስኩል ተማሪዎች ሴቶች ላይ የምታየውን አርቴፊሻል ነገር እንኳን አታይባትም:: የመጀመሪያ ዲግሪዋን በኢኮኖሚክስና ማርኬቲንግ፣ሁለተኛ ዲግሪዋን በኢንተርናሽናል ሎው ይዛለች::

ወንድ ልጄ ደግሞ ያሬድ ፍሰሃጽዮን ይባላል:: እርሱም በጣም ጥሩና የዋህ ልጅ ነው:: ግን ኢንጆይመንት (መዝናናት) ይወዳል:: “አባባ አንተ እንደ እስር ቤት ነው የምትኖረው፣ መጽሐፍ ማንበብ ብቻ ነው የሚያዝናናህ” ይለኛል፤ ከባለቤቴ ጋር ከተፋታን በኋላ ወደ እኔ ሲመጡ የሚያዩትም፣ የሚያገኙትም ወረቀትና መጽሐፍ ብቻ ስለሆነ፣ ልክ እንደ እስር ቤት ነው የሚሰማው:: እኔ የቀለም ሰው እንጂ የገንዘብ ሰው አለመሆኔ እርሱን ብቻ ሳይሆን ብዙ ሰዎችን ይገርማቸዋል::

**ግዮን፡- በሆላንድ ቆይታዎ የነበረዎ ሀገራዊ ተሳትፎ እንዴት ይገለፃል?**

**ፐ/ር ፍስሃጽዮን፡-** ሆላንድ እያለሁ ታመምኩ:: ለአንድ አመት ያህል እየታከምኩ ከቆየሁ በኋላ የምወደው ሀገር ሄጄ ሕዝቤ ፊት ብሞት ይሻለኛል በሚል እ.ኤ.አ በ2008 ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት ተነሳሁ:: ሆላንድ እያለሁ ከሰላሳ ዓመት በላይ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ላይ ብዙ ነገሮችን ሰርቻለሁ:: በሆላንድ የኢትዮጵያውያን ማህበርን ከጓደኞቼ ጋር ሆኜ ያቋቋምኩት እኔ ነኝ:: በየጊዜው አሜሪካ የተለያዩ ድርጅቶች ሀገራዊ ፕሮግራም እያዘጋጁ ይጠሩኛል፤ እነ ፐ/ር ብርሃኑ ነጋንም ያኔ ነው ያገኘኋቸው:: በሰዐቱ በሻዕቢያ በወያኔና ደርግ መሀል የነበረውን ድርድር ሁሉ እንከታተል ነበረ::

የኢትዮጵያም ሆነ የኤርትራ ጉዳይ ላይ በጣም ተሳታፊ ስለነበርኩ እስከ ሞስኮ ድረስ ተጠርቼ የሚመስለኝና የማምንበትን ዕውቀት አካፍያለሁ:: አሜሪካን ሀገር ግን በፖለቲካው በጣም ይንቀሳቀሱ ስለነበር የበለጠ ወደ እዛ ተንቀሳቅሼ ብዙ ሰርቻለሁ:: በአጋጣሚ ኮ/ል ጎሹ ወልዴ ከእኔ ጋር አብረን የተማርንና የተመረቅን በጋራ የሰራን ሰዎች ስለነበርንና በጣም ስለምንቀራረብ መድህን የተሰኘውን ፓርቲ በውጭ ሀገር መሰረትን:: የድርጅቱም ምክትል ፕሬዝዳንት ከመሆን ባሻገር የአውሮፓ ዋና ተጠሪና ኃላፊ ነበርኩኝ::

**ግዮን፡-ከኮ/ል ጎሹ ጋር ቅርበት ቢኖራችሁም በሁለታችሁ ፀብ መድህን እንደፈራረሰ በስፋት ይነገራል፤**

**ፐ/ር ፍስሃጽዮን፡-** በጣም የሚገርመው ኮ/ል ጎሹ ብዙ ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም፣ አንዳንድ ደካማ ጎኖችም ነበሩት:: የመንግስቱ ኃ/ማርያም አይነት አምባገነንነትን ማካሄድ ይፈልጋል በዛን ጊዜ፤ ምናልባት እርሱ ይሄን ሊክድ ይችላል:: በራሱ ውሳኔ፣ እኔን ሳያማክር ብዙ ነገር መስራት ጀመረ፤ ማናችንንም ሳያማክር:: እኔ ደግሞ ሌላ አምባገነን መንግስቱን አልፈልግም:: “ዋሽንግተን መሆናችን ለሰላዮች የሚያመች ስለሆነ፣ ከዲሲ የእኛን ሄድ ኳርተር እናውጣት፤ ሱዳን፣ ናይሮቢ ወይም የመን እንሂድ:: እዚህ ለስለላ ድርጅቶች አመቺ ነው የምንሆነው፣ ኪራይም እየተከፈለ ነውና” ብለን ስንነግረው “ልታስገድሉኝ ነው ወይ?” የሚል ምላሽ ነው የሰጠኝ::

እጅግ በጣም የማከብረው ሰው እንደዛ ሲለኝ በጣም ተሰማኝ:: በዚህ የተነሳ እኔና አውሮፓ የነበሩ ጓደኞቼ ሆነን እሱን ሳላማክር አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ጀመርኩኝ:: የስዊድንም፣ የእንግሊዝም፣ የሆላንድም፣ የጀርመን ፣ፈረንሳይም፣ ቤልጄየም የነበሩ ኤግዚክቲብ ኮሚቴ ሰብስቤ፣ “እኛ ያለንበት ድርጅት ሰው እንደሚፈልገው አልሆነም፤ ኮ/ል ጎሹ ደግሞ እንደዚህ ብሎኛል “ብዬ ያለኝን ነገርኳቸው:: ከእነሱ ጋር ተመካክረን፣ ሀገር ውስጥ ሰው በመላክ ብዙ ነገር እንዲሰራ ተደረገ:: እጅግ በጣም የሚያሳዝነኝ ለካ ኮ/ል ጎሹ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የሚሰራ የነበረ አንድ እሱን የሚያውቀው ሰው እንደ ሰላይ አድርጎ በእኛ ላይ አስቀምጦብናል::

ሪፖርት እኛ ጋር ሲመጣ ለእሱ መረጃዎችን ያቀርባል:: በኋላ “ፍስሃጽዮን የራሱን ድርጅት አቋቋመ” ብለው ከሰሱኝ:: እኔ በእግዚአብሔር ፊት ነው የምናገረው፣ ሌላ ድርጅት የማቋቋም ምንም ሀሳብ አልነበረኝም፤ አልሞከርኩምም:: እኛ ያሰብነው ለማጠናከር ነው:: ኮ/ል ጎሹም ደካማ ጎን ካለው እሱን ለመሸፈንና ጠንካራ ፓርቲ ለማቋቋም፣ ከዘር ፖለቲካ የፀዳ ሀገራዊ ድርጅት ለመመስረት ነበር ጥረታችን:: ሌላ ፓርቲ ለማቋቋም ምንም ፍላጎት እንደሌለኝ እያወቀ፣ ለ25 ዓመታት አውሮፓና አሜሪካ ላይ “ጠንቅቄ የማውቀው ወዳጄ ነው” እያለ ሲናገር የነበረ ሰውዬ፣ እንቅስቃሴያችንን ገልብጦ “ፍስሃጽዮን ከወያኔ ጋር ተነካክቷል፤ ከሻዕቢያ ጋር ይሰራል” በሚል ስም ማጥፋት ጀመረ:: ግን ማንም የሚያውቀው ሀቅ እኔ ፀረ ሻዕቢያ መሆኔን ነው::

**ግዮን፡- በጊዜው መድህን ፓርቲ ውስጥ ይሄ ችግር ሲፈጠር፣ በእናንተ በኩል ከኮ/ል ጎሹ ጋር በድጋሚ ውይይት ለማድረግና ልዩነቶቻችሁን ለማጥበብ ያልሞከራችሁት ለምንድን ነው?**

**ፐ/ር ፍስሃጽዮን፡-** ኮ/ል ጎሹ ወልዴን ለንደን ድረስ አስመጥተን “ኢሕአፓና መኢሶን ውስጥ የተደረገውን ነገር ታውቃለህ:: ስለዚህ እኛ ከእነሱ ስህተት ተምረን እውነቱና ወሳኙ ነጥብ ታውቆ እንደራደር” ብለን ጠየቅነው፤ ግን በዚህም መንገድ ከእኛም ሆነ ከሌሎች ሰዎች ጋር ስላልተስማማና ውዝግብ ውስጥ ስለገባ፣ መድህን ፓርቲ በዚህ ምክንያት ለሁለት ተከፈለ::

ለነገሩ ለሁለት ተከፈለም አይባልም፤ ጎሹ መድኅንን ይዞ ትንሽ ቀጠለ፣ ግን በዕምነት ደረጃ ፕሮቴስታንት ስለሆነ ፖለቲካውን ተወው:: በሁለቱም ወገን በኩል መድህን ኮላፕስ አደረገ ማለት ነው:: በነገራችን ላይ ከትምህርት ቤት ህይወት አንስቶ ጎሹ ወልዴን አወቀዋለሁ ብያለሁ፤ እሱ ከዜሮ አንስቶ፣ ድርጅት ከስር የመመስረት ችሎታ የለውም፤ በተቋቋመ ድርጅት ግን ማዘዝ ይችላል:: የእሱ ጥንካሬ ይሄ ነው::

መድህንን ለማጠናከርና ለመግባባት የተደረገው ጥረት ስላልተሳካ እሱ ጋር የተወሰኑ፣ እኔም ጋር የተወሰኑ ሆነው ተጉዘን ነበር:: ግን መድህን ሲዳከምና ሲፈርስ አብዛኞቹ መላው አማራ ድርጅት ውስጥ ገቡ:: የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከዚህ የምንማረው ነገር አለ፤ አንዳንድ ስልጣን የጠማቸው ግለሰቦች ፓርቲያቸውን በመበተን የሌላውን እንቅስቃሴ ያዳክማሉ:: እነ ፐ/ር በየነ ጴጥሮስን በደንብ አውቃቸዋለሁ:: መራራ ጉዲናን በ1995 (እ.አ.አ) ይመስለኛል፣ ኮንፍረስ ኦርጋናይዝ በሚል ወደ ሆላንድ አስመጥቼው በእዛ አካባቢ እሱም ተጠቅሞ ዶክትሬት ዲግሪውን የሰራው በእኔ ነው:: አንጋፋው ጋዜጠኛ ሙልጌታ ሉሌን (የጦቢያ መጽሔትና ጋዜጣ አሳታሚና አዘጋጅ) ያመጣሁት እኔ ነኝ፤ እኔ ጋር ለሶስት ወር ተቀምጧል:: ጋዜጠኛ ተፈራ አስማረንም እኔ ነኝ ከሀገር ያስወጣሁት:: ዳዊ ኢብራሒምንም እኔ ነኝ ያስመጣሁት::

**ግዮን፡- መድህን ሙሉ በሙሉ ከፈራረሰ በኋላ ነው ወደ ሀገር ቤት የመጡት?**

**ፐ/ር ፍስሃጽዮን፡-** በቆይታዬ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ብዙ መሰረታዊ ችግሮች እንዳሉት ተገነዘብኩ ማለት ነው:: እኔ ወደ ፖለቲካው መጀመሪያ የገባሁት ባለኝ ዕውቀት ሀገሬን ለመርዳት በሚል ሀሳብ ነው:: ስትገባበት ግን በችግር የተተበተበ ነው:: ከእኔ ፀባይም ጋር አይሄድም፣ ግልፅ ሰው ስለሆንኩ የሚሰማኝን ፊት ለፊት ነው የምናገረው:: ይቅርታ ደይረግልኝና የኢትዮጵያ ፖለቲካ የዝንጀሮ ፖለቲካ ነው ፤የሚል አቋም ላይ ደረስኩ:: የዝንጀሮ ፖለቲካ ስል መሰረታዊ የሆኑ ችግሮችን

ቀሪውን ቃለ ምልልስ በገጽ 18 ይመልከቱ

# አንደበት



"የምርጫ ቦርድ ገለልተኛነትና ተቋማዊ ብቃት ብቻ በቂ ነው ማለት የሚቻል አይመስለኝም። ከእኛ ተቋም ውጪ ሌሎች ተቋማት በምርጫው የሚኖራቸው አስተዋፅኦ አስፈላጊ ነው፤ ሌሎች የመንግሥት ተቋማት የሚሳተፉበት ስለሆነ ማለት ነው። ለምሳሌ በምርጫው ክርክር ቢነሳ ፍርድ ቤት ምን ዓይነት ውሳኔ ይሰጣል፤ ከፍርድ ቤት ውሳኔ በፊት ያሉ የክርክር ሒደት፣ አድሏዊ ያልሆነ የቅሬታዎች አፈታት፣ ተወዳዳሪዎቹ የመወዳደሪያውን መርህ እና ሕግ በምን ሁኔታ ያከብራሉ፣ ተከታዮቻቸውን በዛ መስመር እንዴት ያስኬዳሉ፣ የፀጥታም ሁኔታ በጣም ወሳኝና ሌላ አስፈላጊ ነገር ነው።"

*ብርቱካን ሚዴቅሳ*

*አዲስ ማለዳ ጋዜጣ ጥር 25 ቀን 2011 ዓ.ም*

---



"አንድ መታወቅ ያለበት ነገር፣ መንግስት፣ የግሉን ዘርፍ ‹‹በፍትሐዊነት ተወዳደር›› ሲል፣ ቀድሞውኑ ራሱ በውድድር ያምናልና ወይ የፍትሐዊ ውድድር እውነተኛ ትርጉሙ የገባው ነው ወይ ብለን መጠየቅ አለብን። እዚህ አገር ‹‹የግሉ ዘርፍ የኢኮኖሚው አንቀሳቃሽ ሞተር ነው›› የሚባለው ከንግግር ያልዘለለ የይስሙላ አባባል ነው።

*እየሱስወርቅ ዛፉ*

*ኢትዮጲስ ጋዜጣ ጥር 27 ቀን 2011ዓ.ም*

---



"ሶሻል ዴሞክራሲ ርዕዮተ ዓለምን ነው የምንከተለው:: ለኢትዮጵያ ሕዝብ በጣም አስፈላጊ ነው ብለን የምናምንበት ርዕዮተ ዓለም ነው:: ተሳክቶልን ይሄን ርዕዮተ ዓለም ወደ ኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥልጣን ካመጣነው ትምህርት በነፃ፣ ህክምና በነፃ፣ በዋናነት የማህበራዊ ዋስትና ጉዳይ ላይ ብዙ እንሰራበታለን:: የታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ታሣቢ ያደረገ ርዕዮተ ዓለም ነው::"

*አቶ መርሻ ዮሴፍ የኢሕአፓ አመራር*

*አዲስ አድማስ ጋዜጣ ጥር 25 ቀን 2011 ዓ.ም*

---



"የጋዜጠኝነት ስህተት ዋጋው እጅግ ውድ ነው! የህክምና ስህተት ጥቂት ሰዎችን ይገድላል:: በፋብሪካ ውስጥ የሚፈጠር ስህተት የምርትን መጓደል ወይም መጥፋትና ብልሽትን ያስከትል ይሆናል:: ስለዚህ ከላይ ያልኩት በህክምና ስህተት የሚሞቱት አንድም ይሁን ሁለት ቢያሳዝንም በቀጣይ ግን ሊታረም ይችላል:: ሌላውም እንዲሁ፤ የጋዜጠኝነት ስህተት ግን በአንድ ጊዜ በጣም ሰፊ ቦታ ነው የሚደርሰው፤ ስለዚህ ለሌላ ስህተት ወዲያው በር ይከፍታል"

*የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን መምህር ዶ/ር ጌታቸው ድንቁ*

*አዲስ ልሳን ጋዜጣ ጥር 23 ቀን 2011 ዓ.ም*

## ጠቃሚ እውነታዎች

- አንድ ሰው በቀን 4 ጊዜ፣ በዓመት ደግሞ 1460 ጊዜ …. በአጠቃላይ 60 ዓመት እስኪሞላው ድረስም 88 000 ጊዜ ይዋሻል። ከዚህ ውስጥም በጣም የተለመደው ውሸት "ደህና ነኝ" የሚል ነው።
- ለሌሎች ለተቸገሩ ወገኖች እጅህን ስትዘረጋ፣ አምላክ ደግሞ ከሰጠኸው አንድ ሺ እጥፍ አብዝቶ ይሰጥሃል።
- አግኝተህ የማታውቀውን አዲስ ነገር ከፈለግክ አድርገኸው የማታውቀውን አዲስ ነገር አድርግ።
- መዋሸት እውነታው እንዳይታወቅ ሳይሆን እንዲዘገይ ብቻ ነው የሚያደርገው።
- አንዳንድ ጊዜ መቀየር የማንችላቸው ነገሮች በምትኩ እኛኑ ቀይረውን ቁጭ ይላሉ።
- ደስታ ማለት የምናስበው፣ የምንናገረውና የምናደርገው ነገር ተጣጥመው ሲጓዙ ነው።
- በህይወትህ ሁሉ ቀኑን አትርገም። ምክንያቱም ጥሩ ቀን ደስታን ሲለግሰን፣ መጥፎ ቀን ደግሞ ልምድ (experience) ይሰጠናል::
- እውነተኛ ጓደኛ አንተ በራስህ ላይ እምነት ባጣህ ሰዓት ባንተ ላይ እምነት የሚጥል ነው።

## ባጃጅ

እስከ መቼ ይሆን ባጃጅ፤
በየቀኑ ተበላሽተሽ በየቀኑ የምትበጅ
እስከመቼ ይሆን ባጃጅ
እድሜሽን የምትጨርሸው ተፈንጥብሽ ወጪ ወራጅ
እስከመቼ ይሆን ባጃጅ
ቀልብሽን የማትቋጥሪው ርጋታሽ የማይታወጅ
እስከመቼ ይሆን ባጃጅ
    የቸኮለ እየወጣብሽ
    የደረሰ ሚወርድብሽ
እስከ መቼ ነው ቦጅ ቦጅ
እስከመቼ ይሆን ባጃጅ
ቡለን ካስማሽ እየላላ በየጉራንጉሩ ጋራጅ
በየቀኑ ተበላሽተሽ በየቀኑ የምትበጅ
እስከመቼ ይሆን ባጃጅ
ጀምበርሽ የሚጠልቀው ተፈንጥብሽ ወጪ ወራጅ
እስከመቼ ይሆን ባጃጅ
በደቂቃ እየፀነሽ በደቂቃ ምታስወርጅ
ምነው ለሩቁ ሚመኝሽ ጠፋ
ወራጅ አለ ባይሽ በዛ ተሳፋሪሽ በወረፋ።
ማነው ለሩቁ ሚነኝሽ
ማነው አጭቶ ሚያገባሽ
    የትኛው ነው ያንቺ ተስፋ

*የቀንድ አውጣ ኑሮ በይስማዕከ ወርቁ*

## ለጠቅላላ እውቀት

- ኤምፐረር ፔንጉዊን የተባለው ለየት ያለ የፔንጉዊን ወገን እና የዋልታ ወፍ ዝርያ በውቅያኖስ ውስጥ እስከ 200 ሜትር ጥልቀት መድፈቅ ይችላል:: እንዲሁም ለ18 ደቂቃ ያህል ትንፋሹን አፍኖ በውኃ አካላት ውስጥ ለውስጥ እየዋኘ የመቆየት ብቃት አለው::
- በዓለማችን ላይ ምርጥ ፈረስ ጋላቢዎች በመባል የሚደነቁት ህዝቦች ኢራናዊያን ናቸው::
- "ሲሆርስ" የተባሉት የዓሣ ዝርያዎች የፈረስ ጭንቅላት እና የዓሣ ሰውነት አላቸው::
- የዋልታ ድብ ለምሳው ወይም ለቁርሱ ብቻ 86 ፔንጉዊንስ ይመገባል::
- ቢራቢሮን አባሮ የመያዝ መዝናኛ ወይም ሆቢ ሊፖዲፕቴራ ይባላል::
- ጉጉት በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ጥርት አድርጋ ማየት ትችላለች::
- ጥንቸል መሮጥ እና መዝለል እንጂ መራመድ አትችልም::
- ድመት በሕይወት ዘመንዋ እስከ 100 ግልገሎችን ትወልዳለች::

"በህይወቴ ብዙ ማዕበሎችን ለመመልከት በቅቻለሁ፤ አብዛኞቹ ማዕበሎች ግርምታን አጭሮብኛል:: የተፈጥሮ የአየር ጠባይ የምቆጣጠርበት አቅሙ ስለሌለኝ ማድረግ ያለብኝ ጥሞናን በአንክሮ በመለማመድ የተፈጥሮ ተግሳፅ ማክበር ነው::"
ፓውሎ ኮል-

## መጽሐፍ

| ፀሐፊ ተውኔት ዮፍታሔ ንጉሤ /1835 - 1938/ | | |
|---|---|---|
| ጥቅም ያለበት ጨዋታ | ተውኔት | 1930 ዓ.ም |
| የሆድ አምላኩ ቅጣት | | 1924 ዓ.ም |
| ሙሽሪት ሙሽራ | | - |
| ጠረፉ ይጠበቅ | | - |
| አፋጀሽኝ | | 1958 ዓ.ም |
| እልቂጥሩ /ጎበዝ አየን/ | ግጥምና ስድ ንባብ | 1928 ዓ.ም |
| መሰንበት በጎ | | - |



> **በሕወሓት መሪዎች በኩል ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ ስቃወማቸው ብኖርም “ይሄ ሰውዬ ክፋት የለውም፣ የእኛን ዓላማ ቢቃወምም ሀገር ወዳድ ነው፣ ብናስረው ወይም የሆነ ነገር ብናደርገው ምንም ጥቅም የለውም” ብለው ስራዬን እንድሰራ ፈቅደውልኛል**

# የኢትዮጵያ ፖለቲካ...

*ከገጽ 16 የዞረ*

እንደመፍታት ሽሚያውና ሩጫው ስልጣን ተኮር ሆነብኝ ለማለት ነው::

ስልጣን ተኮር ከሆነ ደግሞ ዋጋ የለውም:: በእኔ እምነት ስልጣን እንደ አሺሽ ሱስ ነው:: ስልጣን ላይ ገንዘብ ስትጨምርበት ደግሞ ሱፐር አሺሽ ነው የሚሆነው:: ስለዚህ እዚህ ውስጥ መግባት የለብኝም አልኩኝ::

ባለችኝ ፕሮፌሽን ለሃምሳ ዓመታት በማውቀው፣ ስማር ሳስስተምር የነበርኩበትን ጉዳይ ወደ ተግባር በመቀየር፣ ሀገሬን ልርዳ ብዬ ነው ወደ ኢትዮጵያ የመጣሁበት ዋና ጉዳይ:: ከመጣሁ በኋላ የስልጣን ኢንተረስትም የለኝም፤ ወደ ፖለቲካ ፓርቲ የመግባት ፍላጎትም የለኝም:: የገንዘብም ፍላጎትም የለኝም፤ ስለገንዘብ ጥቅም የማውቀው ሳጣ ብቻ ነው:: አመጣጤ ቀደም ሲል ከላይ እንደገለፅኩት ታምሜ ስለነበር በሀገሬ ለመሞት ነበር:: በጊዜው መአት መድኃኒት ይገኝ ነበር::

እዚህ እንደደረስኩ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በጣም ብዙ ፕሮሰስ ስለነበር፣ መቀሌ ዩኒቨርስቲ ወዲያው ተቀበሉኝ:: ከስምንት ወር በኋላ ሙሉ ለሙሉ ከህመሜ ዳንኩኝ::በዚህ አጋጣሚ አንድ ነገር ልናገር፤ የትግራይ ህዝብ እጅግ በጣም የሚከበር ነው::ፕሮፌሰር ፍስሃጽዮን መጥቷል የሚባለው ዜና ሲሰማ፣ ከተለያዩ የትግራይ አካባቢዎች ብዙ ሰዎች “ለህመምህ ይረዳሃል” በሚል ማር ይዘው መጥተው ይጠይቁኝ ነበር::ይሄንን የሚያደርጉት የማያውቁኝ ሰዎች ናቸው:: በዚህ ሂደትና ርብርብ ላይ የእግዚአብሔር ፍቃድ ተጨምሮበት ነው የዳንኩት:: ፈጣሪ ነው ኤክስትራ ላይፍ (ተጨማሪ ህይወት) የሰጠኝ::

***ግዮን፡- መቀሌ ዩኒቨርስቲ የመደበዎት ማነው?***

**ፕ/ር ፍስሃጽዮን፡-** እኔ ስመጣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬዝዳንት የነበረው ፕ/ር እንድሪያስ እሸቴ ነበር:: መቀሌ ደግሞ ፕ/ር ምትኩ ነበሩ:: አሁን ያለው ፕሬዝዳንት ደግሞ ምክትል ፕሬዝዳንት ነበር:: መቀሌ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ በታክስና ኢንቨስትመንት ለመጀመሪያ ጊዜ ያስጀመርኩት እኔ ነኝ:: ፕሮሰስ ሳያበዙ በፍጥነት የተቀበሉኝ እነሱ ናቸው::

ከመቀሌ ከወጣሁ በኋላ ደግሞ፣ ሲቪል ሰርቪስ ማስተማር ጀመርኩኝ፤ የኢንተርናሽናል ሊደርስሺፕ ኢንስቲትዩት በሊደር ሺፕ አካባቢ ምክትል ፕሬዝዳንት ሆኜ ለሁለት ዓመታት ሠርቻለሁ:: ዲላ ዩኒቨርስቲ ፣ ጎንደር ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም አስተምሬያለሁ:: አዳማም ሌክቸር ሰጥቻለሁ:: በአጠቃላይ ከአንድ ሺህ በላይ በማስተርስ ዲግሪ ወይም ደግሞ ኤምቢኤ፣ ከሰላሳ የማያንሱ ደግሞ በዶክትሬት ዲግሪ አስተምሬያለሁ፤ ዕውቀቴንም አካፍያለሁ::

***ግዮን፡- ውጭ እያሉ ደርግን በኋላ ደግሞ ስልጣን ላይ ያለውን ኢህአዴግን ይቃወሙ ስለነበር እንዴት ወደ ሀገር መግባት ቻሉ?***

**ፕ/ር ፍስሃጽዮን፡-** ፖለቲካውን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እርግፍ አድርጌ ተውኩት:: አስታውሳለሁ “እኔ ታምሜያለሁ፣ ሀገሬን ማየትም እፈልጋለሁ” ብዬ ብራስልስ ያሉትን የኢትዮጵያ አምባሳደር ነገርኳቸው:: በተጨማሪ መቀሌ ዩኒቨርስቲዎች እንድረዳቸው፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲም እንድተባበረው ጠይቀኛልና ሀገሬ መግባት አለብኝ አልኳቸው:: “ልዩነቶቻችን እንደተጠበቀ ሆኖ መሄድ ትችላለህ” የሚል ምላሽ ሰጡኝ::

በዚህ መልክ ወደ ሀገር ቤት ከገባሁ በኋላ፣ የእኔ ሞባይል በደህንነት እየተጠለፈ ከፍተኛ ክትትል ይደረግብኝ ነበር:: ለአቶ ስዩም መስፍንም ሄጄ በአካል ነግሪያቸዋለሁ:: “ይሄ ነገር እንዴት ነው፣ በየሄድኩበት ሴኩሪቲዎች ይከታተሉኛል” ብዬ ምክንያቱ እንዲገለፅልኝ ጠይቄዋለሁ:: በጊዜው የየትኛውም ድርጅት አባል አልነበርኩም፤ ከሕወሓትና ኢሕአዴግ ጋርም ለመሞዳሞድ የምፈልግ ሰው አልነበርኩም::

በኋላ ይሄ ሰውዬ ከእኛ ጋር ልዩነት ሊኖረው ይችላል፣ በሙያው ግን ሀገር ሊጠቅም የሚችል ነው በሚል ተወት ያደረጉኝ ይመስለኛል:: የእኔ ሁኔታ ለእነሱ ስልጣን አደገኛ እንዳልሆነ በደንብ ተረድተውታልና:: እውነት ለመናገር የኢሕአፓ መሪዎች የነበሩትና የሕወሓት መሪዎችን በአንድ ጉዳይ ማመስገን እፈልጋለሁ:: ኢሕአፓዎች በኤርትራ ጉዳይ እየተቃወምኳቸው፣ አክብረው ነበር የያዙኝ:: ለእኔም በጣም ይገርመኛል:: በዚህ የተነሳ እስካሁን ድረስ አመሰግናቸዋለሁ:: በሕወሓት መሪዎች በኩል ምንም እንኳን ብዙ ጊዜ ስቃወማቸው ብኖርም “ይሄ ሰውዬ ክፋት የለውም፣ የእኛን ዓላማ ቢቃወምም ሀገር ወዳድ ነው፣ ብናስረው ወይም የሆነ ነገር ብናደርገው ምንም ጥቅም የለውም” ብለው ስራዬን እንድሰራ ፈቅደውልኛል::

ወያኔዎች ባለፉት 27 ዓመት ሥልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ፣ ሁሉም ምሁርና ፕሮፌሰር አፉን ዘግቶ ነበር፤ እኔ ነኝ በድፍረት በየውይይት መድረኩ ላይ ስናገር የነበረው:: “ይሄ ሞኝ ፕሮፌሰር ዝም ብሎ እንደፈለገ ይናገራል” ይሉኛል፤ “ለምንድን ነው ነጭ በሬ የምትሆነው “ ሲሉኝ ነበር:: ግን እኔ አሁንም ሆነ ድሮ ለራሴ ሳይሆን ለሀገሬና ለሕዝቦቿ ጥቅም መሆን ያለበትን ፊት ለፊት እናገራለሁ:: በዛ መልኩ ስለተረዱኝ ወደ ሀገሬ ከገባሁ በኋላ ብዙም ችግር አልገጠመኝም::

***እንጋፋው ፕሮፌሰር ፍስሃጽዮን መንግስቱ ወደ ሀገር ከገቡ በኋላ ያከናውኗቸው በርካታ ጉዳዮችን በተመለከተና የሀገራችንን ወቅታዊ ጉዳዮችና ቀጣይ ተግዳሮቶች ዙሪያ ያደረግነውን ቃለምልልስ በቀጣይ ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን::***



መሐመድ ማምዳኒ

# ከዘውግ ፌዴራሊዝም ጋር ያለው ግብግብ

በ ታዋቂው የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ላይ የኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲው ልኂቅ መሐመድ ማምዳኒ የኢትዮጵያን ወቅታዊ የፓለቲካ ምስቅልቅል ገጽታን አስመልክተው ያሰፈሩትን ጽሑፍ የግዮን ጋዜጠኛው ደረጀ ይመር በሚከተለው መልኩ ወደ አማርኛ መልሶታል::

የ42 ዓመቱ ጎልማሳ ዐቢይ አሕመድ በዓለ ሲመታቸው በሚያዚያ 2010 ዓ.ም ከተፈፀመ በኂላ ባካሄዱት የፖለቲካ ለውጥ የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ የትኩረት ማዕከል ሆነው ቆይተዋል:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከጎረቤት ኤርትራ ጋር የነበረውን የሃያ ዓመት ቁርሾ መቋጫ አበጅተውለታል፤ የፖለቲካ እስረኞችን ነጻ ለቀዋል፤ መቀመጫቸውን ከሀገር ወጪ ያደረጉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ኃይሎች የተጣላባቸው እገዳ ተነስቶላቸው ወደ ሀገር ቤት መግባት ችለዋል፤ የመገናኛ ብዙኃን ነጻነት እውን ሆኗል፤ በሰላም ማዕቀፍ ውስጥ ያለ የትኛውም የፖለቲካ ኃይል ያመነበትን አጀንዳ የሚያራምድበት ሰፊ ምህዳር ተከፍቶለታል::

> በዘውግ ድርጅቶቹ አማካኝነት የሚሰነዘረው ዘር ተኮር ትችት ሚዛን እንዳይደፋ ከሚያደርጉት ነባራዊ እውነታዎች መካከል ጠቅላይ ሚኒስትር በእምነታቸውም ሆነ በትውልድ የዘር ሐረጋቸው ጉራማይሌ ማንነትን መለበሳቸው ነው

ምንም እንኳን ዐቢይ አሕመድ የለውጥ መሐንዲስ ተብለው ቢሞካሹም፣ ሀገሪቱ ላለፉት ሁለት ዐሥርተ ዓመታት የምትተዳደርበት ሕገመንግሥት ከወለደው የዘውግ ፌዴራሊዝም ጋር ፊት ለፊት የሚያላትም እርምጃዎቹን ነው የወሰዱት:: የጠቅላይ ሚኒስትሩ አዎንታዊ የፓለቲካ ውሳኔዎች ከጎንዮሽ ጉዳት ነጻ ናቸው ብሎ አፍን ሞልቶ ማውራት አይቻልም :: አዲሱ የለውጥ አስተዳደር ቁመና በመርህም ሆነ በተግባር ደረጃ ከሕገመንግሥቱ አኳያ ሲመዘን ማዶ ለማዶ ነው::ይህም ውሎ አድሮ ሀገሪቱን ዘርን መሠረት ወዳደረገ የእርስ በርስ ግጭት ውስጥ እንዳይጨምራት የፓለቲካ ታዘቢዎች ሥጋታቸውን ያጋራሉ::

የ1987 ዓ.ም ሕገመንግሥት በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ፊታውራሪነት ሲዘወር በነበረው የአራቱ የዘውግ ድርጅቶች ጥምረት ኢሕአዴግ አማካኝነት ነው የተተከለው:: በዚህም ምክንያት በዘር ማንነት ላይ ተንጠላጥለው ወሰን የተበጀላቸው ዘጠኝ ክልሎች እና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች እውን ሊሆኑ ችለዋል::

ሀገሪቱ በንጉሡም ሆነ በወታደራዊው ደርግ ዘመነ መንግሥት የነበራት የአስተዳደር አወቃቀር አሃዳዊ እንደሆነ ይታወቃል:: የኢሕአዴጉ የዘውግ ፌዴራሊዝም በአካባቢም እና በፌዴራል የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ንቁ ተዋናይ ለመሆን የቀድሚያ መመዘኛው አጥንት ቆጠራ እንጂ በዜግነት የሚገኝ ማንነት አይደለም::

የዘውግ ፌዴራሊዝሙ በውስጡ ብዙ የተዛነፉ መርህዎችን ታቅፏል:: በዚህም በተግባር የተሳከሩ ነባራዊ ሁኔታዎችን ለመወለድ በቅቷል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ አካባቢ እንደኩሬ ተከትሮ አይደለም የኖረው::ለዘመናት በጋብቻ፣በንግድ እና በሥራ ምክንያት በየቅጣጫው የትውልድ ቀዬውን ጥሎ ሲፈልስ እንደኖረ የአደባባይ እውነታ ነው:: በአራቱም የሀገሪቱ ጫፎች ያልተበተነ የዘውግ ማኅበረሰብን ማግኘት የሚታሰብ አይደለም::ሕገመንግሥቱ ግን ለእነዚህ ዜጎች ምንም አይነት ከለላ አይሰጥም:: ሰነዱ አንዱን ባለቤት ሌላውን ደባል አድርጎ የልዩነት ግምብ ይፈጥራል:: የግዛት ባለቤት ያደረጋቸው የዘውግ ማኅበረሰቦች ቀዬቸውን ጥለው ወደ ሌላ ክልል ሲያመሩ የባዕድነት ወይም የባይተዋርነት ስሜት ይሰማቸዋል::በሌላ አነጋገር ሰነዱ አንደኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ ብሎ ብይን ይሰጣል::

ኢትዮጵያ የብዙ ዘውግ ማኅበረሰቦች ሀገር ናት:: እስካሁን ያሉት መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነ የዘውግ ማኅበረሰቦች ብዛት ከ90 በላይ ይሆናል:: ከእነዚህ ሁሉ የዘውግ ማኅበረሰቦች የራስን ዕድል በራስ ማስተዳደር ወይም የክልል ባለቤት የሆኑት ዘጠኙ ብቻ ናቸው:: በእነዚህ ክልሎች ውስጥ የሚኖሩት ሌሎች ሕዳጣን ማኅበረሰቦች ውክልና የላቸውም::በእነዚህ ሀገር አልባ ወገኖች ላይ የአካባቢ ሹማምንቶች የሚያደርሱት የሰብኣዊ መብት ጥስት ከፍተኛ ነው::

የዘውግ ፌዴራሊዝሙ በትግራይ፣ በአማራ እና በኦሮሞ ዘውጌዎች መካከል የሥልጣን ሽኩቻ ከፍቷል:: ምንም እንኳን ኢሕአዴግ የአራት ፓርቲዎች ጥምረት እንደሆነ ቢታወቅም ባለፉት ዘመናት የኃይል ሚዛኑ ወደ ሕዳጣኑ ሕወሓት ያደል ነበር:: ከደርግ ውድቀት ማግሥት በኢኮኖሚያዊም ሆነ በፓለቲካዊ መስክ ሁለንተናዊ የበላይነት የነበረው ይኸው ፓርቲ ነው::ከ1983 ዓ.ም የመንግሥት ለውጥ ቀደም ብሎ የአገዛዝ ዘመን የአማራ ተፅዕኖ ከፍተኛ ነበር ብለው የሚያምኑ ዘውግ ተኮር የፓለቲካ ኃይሎች ቁጥራቸው ቀላል የሚባል አይደለም::ኦሮሞ ደግሞ ከማዕከሉ ወደ ዳር ተገፍቶ የበይ ተመልካች እንዲሆን ተደርጓል የሚል ቅሬታ ከኦሮሞ የፓለቲካ ልኂቃን አንደበት በአብዛኛው ጊዜ የሚደመጥ ነው::

ሕወሓት በበላይነት በሚመራው ኢሕአዴግ ላይ ተቃውሞ መፋፋም የጀመረው በ 2007 ዓ.ም ነበር:: ይህን አመጽ እንደ ክብሪት ሆኖ ያቀጣጠለው ደግሞ በአዲስ አበባ ዙሪያ በሰፈሩት የኦሮሞ አርሶአደሮች ላይ በገዢው መንግሥት ይደርስ የነበረው ሁለንተናዊ ጭቆና ነው::የፌዴራሉ መንግሥት መቀመጫ የሆነቸውን አዲስ አበባን ወሰን በማስፋት ሂደቱ ወስጥ ኩታገጠም የሆኑት የኦሮሞ ገበሬዎች ሰለባ ሆኑ::በዚህም ምክንያት ጭቆናው ከአንገቱ የደረሰው ሰፊው ሕዝብ ወደ ጎዳና ወጥቶ በጀግንነት መፋለም ጀመረ::በዚህ ጊዜ ሌላው የሀገሪቱ ትልቅ የዘውግ ማኅበረሰብ አማራ በኦሮሚያ ክልል ከሚካሄደው የሰላማዊ ትግል ጋር ግንባር በመፍጠር  የትግሉን ሒደት ከተጠበቀው በላይ ለገዢው መንግሥት አከበደበት::

በዚህ ጊዜ ከቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሥልጣን የተረከቡት ኃይለማሪያም ደሳለኝ  ሰላማዊ ቅዋሜውን በኃይል ለመቀልበስ ቀጭን ትዕዛዝ ነበር ያስተላለፉት:: በዚያው ዓመት ከ500 እስከ 1500 የሚጠጉ ንፁሐን ሰልፈኞች ጭዳ ሆነዋል::

ይህንን የግጭት ማዕበል ተከትሎ ነው የኦሮሞ ፓርቲ ተወካዩ፣ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሥልጣን እርካቡን ለመቆናጠጥ የበቁት:: በተመረጡ አጭር ጊዜ ውስጥም ማንም ባልጠበቀው ደረጃ ተአምራዊ የሆኑ ለውጦችን ማስመዝገብ ችለዋል::

የጠቅላይ ሚኒስትሩ ለውጥ በብዙ መልኩ የሚወደስ ነው:: ነገር ግን ለውጡ ያለንዳች ተዛማጅ ጉዳት ተፈጻሚ እየሆነ አይደለም:: የእርሳቸውን በሁሉም መስክ እየተደረገ ያለውን ተከታታይ  ቀዶ ጥገናዊ ለውጥ ለመገዳደር፣ ሚናቸውን የተነጠቁት የዘውጌ የፓለቲካ ኃይሎች የመጨረሻ ምላጫቸውን መሳባቸው አይቀርም:: የዘር ማንነትን እንደ መደላደል በመጠቀም  ኃይላቸውን ለማጠናከር በብርቱ እንደሚዋትቱ እሙን ነው::በዘውግ ድርጅቶቹ አማካኝነት የሚሰነዘረው ዘር ተኮር ትችት ሚዛን እንዳይደፋ ከሚያደርጉት ነባራዊ እውነታዎች መካከል ጠቅላይ ሚኒስትር በእምነታቸውም ሆነ በትውልድ የዘር ሐረጋቸው ጉራማይሌ ማንነትን መላበሳቸው ነው::

የዐቢይ አሕመድ ውህድ ማንነት ለሀገሪቱ እንደትልቅ የምስራች ነው የሚቆጠረው:: አባታቸው የእስልምና እምነት ተከታይ ኦሮሞ ሲሆኑ፣ እናታቸው ደግሞ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን እምነታ ተከታይ አማራ ናቸው:: እርሳቸውም በግላቸው የፕሮቴስታንት ዕምነትን ይከተላሉ:: ይህም ውህድ ማንነታቸው ለሀገራዊ አርበኝነት ትልቅ ብስራት እንደሆነ ገሀድ ማሳያዎችን መጥቀስ ይቻላል:: በዘመነ ሕወሓት/ኢሕዴግ ከል ለብሶ የነበረው ሀገራዊ አርበኝነት አፈር ልሶ የተነሳው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ጥቂት የአመራር ዘመን ነው::

ዐቢይ አሕመድ አሁንም ከፈተና ነጻ የሆነችን ሀገር እያስተዳደሩ አይደለም::በየአቅጣጫው በሚለኮሰው ሰደድ እሳት ሀገሪቱ እየተለበለበች ነው::

በየክልሉ የታጠቁት ሚሊሻዎች  ለሀገር አንድነት ብርቱ ሥጋት ሆነዋል:: በተለይ የልዩ ኃይል ተብሎ የተቋቋመው የፀጥታ ተቋም ኩታገጠም በሆኑ የዘውግ ማኅበረሰቦች መካከል በሚነሳ ግጭት ውስጥ በቀጥታ እጁን ማስገባቱ ነገሩን የበለጠ ውሉን የሳተ አድርጎታል:: እዚህ ጋር እንደ አብነት የምንወስደው በሶማሌ እና በኦሮሚያ ክልል ከእርስ በርስ  ግጭት በስተጀርባ የሶማሌ ልዩ ኃይል የነበረውን ከፍተኛ ተሳትፎ ነው:: ይህ ግጭት የክልል ባለቤት በሆኑት ሶማሌዎች እና መጤ ተብለው በተፈረጁት ኦሮሞዎች መካከል የተፈጠረ የተካረረ ግጭት ነበር::

የኢትዮጵያን የሰብኣዊ መብት ኮሚሽንን በሚመሩት አዲሱ ገብረእግዚአብሔር አማካኝነት በወጣው ሪፖርት መሠረት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኂላ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ክልላችሁ አይደለም፣ ውጡ ተብለው፣ በግፍ ሊፈናቀሉ ችለዋል:: እነዚህን ተባራሪ ዜጎች የሚጠብቅ ምንም ዓይነት ተቋም የለም:: ኢትዮጵያ ቀጣያዋ የአፍሪቃ የእልቂት አውድ እንዳትሆን ያሰጋል::

አንዳንድ የፓለቲካ ታዛቢዎች የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሹመት ሃይማኖታዊ አንደምታ አለው ብለው ሽንጣቸውን ገትረው ይከራከራሉ:: ለዚህም እንደማሳያ የሚወስዱት ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኂላ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ከፍተኛውን የመንግሥት ሥልጣን መቆናጠጥ መጀመራቸው ነው::

ኢትዮጵያ በየትኛውም የአውሮፓ ወራሪ ኃይል ቀኝ ያልተገዛች ሀገር እንደሆነች ይታወቃል :: ይህ ነጻነቷ ግን በሌሎች የአፍሪቃ ሀገራት ዘንድ ከሚስተዋለው ጎሳ መር ፓለቲካ አላዳናትም:: በአብዛኛው የአፍሪቃ ሀገራት ላይ የሚንጸባረቀው ፓለቲካዊ ሥርዓት በዘር ተቧድኖ ለመንግሥት ሥልጣን መሻኮት ነው:: በአፍሪቃ ምድር የዘር ማንነትን መሰረት ያደረገ ፖለቲካ መናኝት አህዱ ያለው ቀኝ ገገርዋ እንግሊዝ የነበራትን ተፅዕኖ በተዘዋዋሪ መንገድ (Indirect rule) ለማንበር የቀየሰችው ሴራ ፍሬ ማፍራት እንደጀመረ ነበር::

የእንግሊዝ ቅኝ ተገዢ ግዛቶች ሥልጣን ተሰፍሮ የሚሰጠው ለአካባቢው ቀደምት ነዋሪዎች ነበር:: ሌሎች ማኅበረሰቦች ከፖለቲካ ሥልጣን ተገፍተው የበይ ተመልካች እንዲሆኑ ተፈርዶባቸዋል::

ይህም በአብዛኛው ብዙኃኑን ጥቁር ያገለለ እና ጥቂት ነጮችን ከፍ ላደረገው የፖለቲካ ሥርዓት የተሰጠ ማለዘቢያ ምላሽ ነበር:: በዚህም መሠረት የሀገር ባለቤቶች እና ደባሎች በሚል የልዩነት አጥር እርስ በርስ  የተጋመዱትን ሕዝቦች የጎሪጥ ለመተያየት ተገደው ነበር :: ከነጻነት በኂላም የዘር ማንነት በግዛት ማዋቀር ውስጥ ገዢ ሆኖ ቀጥሏል::

አብዛኞዎቹ የፖለቲካ ተንታኞች እንደሚሉት ከሆነ ሕዳጣኑ ሕወሓት ያለውን ልዕልና ያለተቀናቃኝ ለማንበር በኢትዮጵያዊ ማንነት ኪሳራ ሀገሪቱን በዘር መስመር ሊከፋፍል ችሏል:: ይህም ተግባሩ ከቀኝ ገዢዋ እንግሊዝ የተዘዋዋሪ አገዛዝ (Indirect rule) ሙሉ ለሙሉ የተኮረጀ (Plagiarize) ነው::

በመለስ ዜናዊ ሲመራ የነበረው ሕወሓት፣ የቀድሞዋ የሶቪየት ኅብረት ዘርን መሠረት ያደረገ የግዛት አወቃቀር ግልባጭ እንደሆነ ብዙ ማሳያዎቹን ዋቢ ማድረግ ይቻላል::

የ1987 ዓ.ም  ሕገመንግሥት የስታሊንን የብሔርብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ትንታኔን የሙጥኝ ብሎ የያዘ ነው:: ከዚህም በተጨማሪ ብሔሮች ለሚያነሱት የመብት ጥያቄ የሶቪየትን የመፍትሔ አማራጭን እንዳለ ይቀበላል::


ልክ እንደሶቪየት ኅብረት በእያንዳንዷ  የሀገሪቱ ቁራጭ መሬት ላይ የሰፈሩ ሕዝቦች በባለቤት እና በደባልነት  ሕገመንግሥቱ ፈርጆ አስቀምጧል :: የመለስ ዜናዊ ፓርቲ ሶቪየታዊ እና አፍሪቃዊ ባሕሪያትን በአንድነት ቀይጦ የያዘ  ነው::

እንደ አብዛኛው የአፍሪቃ ሀገራት ኢትዮጵያ በመስቀለኛ መንገድ ላይ ቆማለች:: ሀገሪቱን ለአስራ ሰባት ዓመታት አሀዳዊ በሆነ የግዛት አወቃቀር ሲያስተዳድራት የነበረው የወታደራዊው ጁንታ ደርግም ሆነ በፌዴራል ሥርዓቱ ስም በከፋፍለህ ግዛ ሕዝቦችን ሲያሸብር የነበረው ሕወሐት /ኢህአዴግ ሀገሪቱን አንዲት ጋት ወደ ፊት ፈቀቅ ማድረግ አልቻሉም:: አዲሱ የለውጡ አስተዳደር ከባለፉት ሥርዓቶች ውድቀት መማር ይኖርበታል::

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በጉልህ የሚታይ ሁለንተናዊ እድገትን ማስመዝገብ የሚችሉት የፌደራላዊ ሥርዓቱን መከለስ የሚያስችል ማእቀፍ ሲያዘጋጁ ብቻ ነው:: ይህ ፌዴራላዊ ሥርዓት ከዘውግ ማንነት ይልቅ የመልካምድራዊ አወቃቀርን መከተል ይኖርበታል::

አዲስ ፌዴራላዊ ሥርዓት ነጻነት፣ መብት እና የራስን እድል በራስ የመወሰን ሥልጣንን የሚለግሰው በዘር መነጽር ሳይሆን በአካባቢ ነዋሪነት ይሆናል:: ይህ ፌዴራላዊ ሥርዓት  ኢትዮጵያን በአምባገነናዊ አገዛዝ መዳፍ ሥር ዳግም እንዳትወድቅ መጠባበቂያ ግምብ ሆኖ ያገለግላል::

***ማስታወሻ፡ መህመድ ማምዳኒ የታዋቂው ማካረሬ ዩኒቨርስቲ የማኅበራዊ የምርምር ጥናት ዳይሬክተር ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ የኮሎምቢያ ዩኒቨርስቲ የሥነ መንግሥት ፕሮፌሰር ሲሆኑ “citzen and subject contemporary Afirca and the legacy of late colonialism ”የሚል ድርሳን ፀሐፊ ናቸው::***



ተመስገን ዘገየ

# ከመንገዱም እንዳያስወጡን

ሐዋሳ በልማት ጎዳና ላይ የምትገኝ ከተማ ናት::የሐይቁ መኖር፤የኢንዱስትሪው መንደር መስፋፋት ፤የታላላቅ ሆቴሎች መገንባት፤ ብዙ የውጭ ሀገራት ዜጎች ወደ ከተማዋ እንዲገቡ ምክንያት የሆነ ይመስለኛል::ገና ወደ ሐዋሳ ብቅ ሲል አንድ መንገደኛ የሐዋሳ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንን በልዩ ግርማ ሞገስ ማየት ይጀምራል::ብዙ የውጭ ሀገራት ዜጎች ወደ ከተማዋ ይጎርፋሉ::ከተማዋ አንዱ የምትታወቅበት እንግዳ መቀበል ነው::ይሁን እንጂ የውጭ ሀገራት ዜጎች ወደ ከተማዋ መግባታቸው ጥቅሙን ብቻ እንጂ እያስከተለ ያለውን ጉዳት በንጽጽር በጥንቃቄ የተመለከትነው አይመስለኝም ::ይህን ያልኩበት ያለ በቂ ምክንያት አይደለም::በሦስት ቀናት ቆይታዬ ያጋጠመኝን ነገር ትልቅ ጉዳይ ሆነብኝ እና ለእናንተም ላካፍላችሁ ስለወደዱኩ ነው፤ እናንተም በጉዟችሁ ከታዘባችሁት ገጠመኝ ጋር እያገናዘባችሁ ተከተሉኝ::

የጉዞዬ መዳረሻ ወደ ሆነችው የደቡቧ ኢትዮጵያ ውቢቷ ሐዋሳ ከተማ በሰላም ደርሻላሁ፤በአራቱም የሐዋሳ አቅጣጫ ለሥራ ስንቀሳቀስ ከዋልኩ በኂላ ከተከራየሁበት አልጋ ቤት ከድካሜ አረፍ አሉክ::የሀገርና የወገን ፍቅር የማያውቅ አንድ ኢትዮጵያዊ ወጣት እንደ እብድ ውሻ እየተክለፈለፈ ወደ አልጋ ቤቴ ድንገት መጣና “ግቢውን በሙሉ የቻይ ዜጎች ለሦስት ወራት ተከራይተውታልና ውጣ” የሚል ቀጭን ትእዛዝ አስተላለፈልኝ ::ሰዐቱ እኩለ ሌሊት ነው::በዚህ ሰዐት ወዴት ይደረሳል?

ይህ ትእዛዝ ለመንገደኛው በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ነበር::ውጣ ያለኝን ወጣት ከአንደበቴ ክፉ ነገር ወጥቶ እንዳላስቀይመውና ከፈጣሪ ጋርም እንዳልጣላ፣ ስሜቴን ለመቆጣጠር ተውተረተሩክ::ከተወሰኑ ደቂቃዎች በኂላ የሆቴሉን ባለቤቶች “ለምን እንዲህ አይነት የማይጠቅም ሥራ ትሠራላችሁ ?ፈጣሪያችሁን አትፈሩም ?” በማለት ሳናግራቸው በቂ የሆነ መልስ ሊሰጡኝ አልቻሉም::ብቻ ከእንግዳ ተቀባይነትና ኢትዮጵያዊ ስሜት ይልቅ የቻይና ረበጣ ገንዘብ የልብ ልብ ሰጥቷቸዋል::

ይህ ሁኔታ ለመንገደኛው የከበደው አዲስ ክስተት ስለሆነ አይደለም::ይልቁንም አልጋ ቤቱን ለማስለቀቅ ከፍተኛ ትግል የሚያደርጉት ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸውና ከሰው ይልቅ ገንዘብን ያስቀደሙ ደላሎች መሆናቸው ነው:: እኔም እልህ ያዘኝና ገብቼ ለመተኛት ሞከሩክ::ዕንቅልፍ ግን ጠፋ:: የቻይና ዜጎችም በቋንቋቸው በመነጋገር ግቢውን እንደ ነጋሪት በሚጮኸው ድምፃቸው መረበሽ ጀመሩ፡ ፡ለደከመው መንገደኛ ዕረፍት ነሱኝ:: ሁሉም በየተራ እየመጡ የመንገደኛውን አልጋ ቤት ያንኳኳሉ::ግቢው የጦርነት ቀጠና መስሏል::

በመጨረሻም መንገደኛውና ቻይናዎቹ በእንግሊዘኛ ቋንቋ መግባባት ጀመርን:: የአልጋ ቤቱ ባለቤትም ምንም ሰው የለም ብሎ እንዳከራያቸው ነገሩኝ::በኂላም ከቻይናዎች ጋር መከራከር ከነፋስ ጋር እንደ ማውራት ቆጠርኩትና በመንፈቀ ሌሊት ያረፍኩበትን የመኝታ ክፍል ለቅቄላቸው ወጣሁ:: ስወጣ በሐዋሳ ከተማ የተመለከትኩት ነገር ደግሞ ከተማዋን ትንሿ ባቢሎን እንድላት አስገደደኝ::ድብልቅልቅ ያለ ነገር በመሀል አስፋልት ገጠመኝ:: ነፍሴም በዚህ ወቅት በእጅጉ ተጨነቀች::

በሐዋሳ ከተማ ለሕሊና የሚከብዱ፤ፈጣሪን የሚያሳዝኑና ዕድሜን የሚያሳጥሩ ሥራዎች ጨለማን ተገን በማድረግ እየተሠሩ መሆኑ ዐይኔ ተመለከተ:: ሰው ያየኛል ማለት እየቀረ መሆኑን ተረዳሁ፡ምነው ሐዋሳን የሚያስተምር ፤የሚገሥፅ ሙሴ እንዴት ጠፋ ብዙ ቤተ እምነቶች አሉ እያልኩ ከራሴ አእምሮ ጋር ሙግት ጀመርኩ፡ምክንያቱም ድርጊቱ ከሃይማኖት አንጻር ብቻ ሳይሆን ከባሕላችን አንጻርም ከፍተኛ ጥንቃቂ ውስጥ የሚያስገባ ድርጊት ነውና ::

እኅቶቻችን የተቀደሰውን ገላቸውን ገልጠው፣ በአደባበይ ዝሙትን ሲጠሩ፣ ወንዶቹ ደግሞ ሴተኛ አዳሪዎችን ፍለጋ በመንፈቀ ሌሊት ሲንቀሳቀሱ፣ ዝሙት በገንዘብ ሲቸበቸብ፣ መንገደኛው ወዳጃችሁ ይህን ድርጊት ስመለከት እንደ ሰዶምና እንደ ገሞራ እንዳንጠፋ ፈራሁ ::ምክንያቱም ክቡር የሆነው የሰው ልጅ አውሬ እየሆነ ነውና::በእኔ ትዝበት ሐዋሳ ከተማ በዝሙት ከፈጣሪ ጋር እየተጣለች ያለች “ደንበኛ ንጉሥ ነው “የሚለው አባባል ትርጉም ያጣባት ከተማ እየሆነች መምጣቷን መገመት ችያለሁ፤ አንድ ወቅት አንድ ወንድሜ እንዲህ ጽፎ ነበር ”እስከ አሁን ደንበኛ ንጉሥ ሁኖ በትክክል ያየሁበት ቀብር አስፈጻሚዎች ጋር ነው በክብር ይሸከሟችኂል “ብሎ ነበር:

አንዳንድ ባለሀብቶች የሀገራቸውን ተወላጅና ደንበኛቸውን መንከባከብ ራሳቸውን መንከባከብ እንደሆነ አያውቁም::እኔ አልጋ ተከራይቼበት የነበረበት ቦታ ደንበኛ ንጉሥ ነው ለመባል የግድ የቻይና ዜጋ መሆን ይጠበቅበታል::፡

ወደፊት ቅድስት ሀገራችን እንደ አልጋና ሆቴሎች ሀገሪቱንም ተከራይተናታል ውጡ ሳይሉን አይቀሩም::በርግጥ ምን ቀረን ብላችሁ ነው? መልካም ባህላችን እንደ ክፉ ልማድ የሚቆጥሩ የውጭ ሀገራት ዜጎች ተብራክተዋል::የዚህ ውጤት ይመስለኛል በሀገራችን እንዳንከባበር ፤በከተሞቻችን ዝሙት እንዲስፋፋ የሆነው::

አንድ ወቅት ሊቁ አለቃ ገብረ ሐናን ባለቤታቸው ወ/ሮ ማዘንጊያ ቁርስ በተልባ ጭቃ ትሰጣቸዋለች:: ምሳቸውንም ለአለቃ ገብረ ሐና የተልባ ጭቃ በድጋሚ ታቀርብላቸዋለች::በእራት ሰዐትም በተልባ ጭቃ ሲመገቡ አለቃ ገብረ ሐና የሚመገቡት ነገር ሲያንቃቸው፣ ባለቤታቻው ወ/ሮ ማዘንጊያ ጠጋ ብላ “አለቃ ተልባ አጭልቄ ልስጠዎት” ስትላቸው አለቃ አይ ማዘንጊያ የቀረሽ መዝራት ነው ዝሪብኝ አሏት:: እኛስ ምን ቀረን? ሰው እንዴት መከባበሩን ፤መዋደዱን ያጣል? በኢትዮጵያ ዝሙት እንዴት ገቢያ ይሆናል? ወዳጆቼ እናንተን ባለውቅም ለእኔ ግን ይህ ትልቅ ሥጋት ሁኖብኛል::በዚህ አካሄዳችን የምንቀጥል ከሆነ መጠፋፋታችን አይቀርም::በሐዋሳ ከተማ በጣም ቅን የሆኑ ሰዎችንም የያዘች የልማት ኮሪደር ናት፤ ጠንክረው የሚሰሩ በአርአያነት የሚጠቀሱ ሰዎችንም ዐይቻለሁ::፡ግን ምን ዋጋ አለው በጥባጭ ካላ ማን ጥሩ ይጠጣል ::አሉ አንዳንድ የሀገር ስም እንዲጠፋ የሚያድርጉ ቦዘኔዎች ከስንዴው ማሳ ጋር እንክርዳድ ሁነው ተቀላቅለዋል::በሚመለከታቸው አካላት ክትትል ከስንዴው ጋር ያሉት እንክርዳዶች መለቀም ይኖርባቸዋል::ይህ ካልሆነ ለከተማ ስምና ዝና ዕንቅፋት ይሆናሉ::ስለዚህ ችግሮችን ገና በዕንቁላሉ መቅጨት ይገባል::

በሐዋሳ ቆይታዬ አስነዋሪው የዝሙት ገቢያ በዐይኔ በብረቱ ለመመልከት ተገድጃለሁ ፤ኢትዮጲያዊ ከመሆን የቻይና ዜጋ መሆን ሲያስከብርም በተግባር ተመልክቻለሁ ::እንጨት”የፈጀን የእኛው ጠማማ ነው ”እንዳለው ታሪካችን እየተበላሸ ያለው የሀገር ፍቅር በሌላቸው ትውልድ ኢትዮጵያዊ በሆኑ ግለሰቦች ነውና ሳይቃጠል በቅጠል፤ሳይርቅ በቅርቡ መፍትሔ ቢፈለግለት መልካም ነው::

በከተማዋ ሰላማዊ የጉብኝት ሥርዓትን ማስፈን፣ የጎብኝዎችን እርካታን መጨመር፣የቱሪስቶችን ቁጥር በመጨመር፣ ዘላቂና ቀጣይነት ላለው የቱሪዝም ገቢ መኖር የሚያበረክተው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው:: በጉብኝት ሒደት ላይ መጥፎ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ችግሮችን በመለየትና በመተንተን መፍትሔ ማስቀመጥ ይገባል፡

*መንገደኛው ነኝ*



# ባህማን

ኢራናውያን የሚያከብሩት በዓል ባህማን ወይንም በያዝነው ፌብርዋሪ ለአስር ቀናት የሚያከብሩት በዓል ነው:: ይህ በዓል በኢራናውያን ዘንድ በልዩ ሁኔታ የሚከበር ነው:: በዓላማችን ላይ ከተካሄዱ እልህ አስጨራሽ አብዮቶች መካከልም የፈረንሳይ፣ የአሜሪካ የቻይና፣ የሩሲያ፣ አብዮቶች ተጠቃሾች ናቸው:: ከ1950 በኋላ ከተደረጉት ህዝባዊ አብዮቶች መካከልም የ1979 የኢራን አብዮት አንዱና ዋነኛው ነው::ምክንያቱም የኢራን አብዮት ላለፉት 2500 አመታት በሃገሪቱ ላይ የነበረውን የዘውዳዊ ስርኣት የገረሰሱበት በመሆኑ ጭምር ንው፤፤ ይህ አብዮት በወቅቱ ሀገሪቱን ይመሩ የነበሩትን ሬዛ ሻህ በውጭ መንግስታት ጣልቃ ገብነት እንዲሁም የውጭ መንግስታት ተላላኪ አስፈፃሚነት እንዲሁም ስርዓቱ የኢራናውያን ባህል በውጪ ባህል ለመተካት የተንቀሳቀሰ በመሆኑና በሙስና የተጨማለቀ በስርዓቱ ላይ የሚነሱ ተቃውሞዎችን ከውጭ በሚያገኘው ረብጣ ሀብትና አቅም የሚደመስስ እንዲሁም ከሀይል ይልቅ በአፈሙዝ የሚያስወግድና የሚመራውን ሕዝብ ባለማድመጡ ደካማ የመንግስት አመራር (የመልካም አስተዳደር እጦት) የተፈጠረ የመንግስት ላይ አመፅ በመነሳቱ የተካሄደ አብዮት ነው::

የሻህ አመራር የሀገሪቱን ሀይማኖት ወደ ጎን የገፋ ዜጎች ሰፊ በሆነ ድህነት አረንቋ ውስጥ እንዲወድቁ ያደረገ፣ ሰፊ የሆነ ስራ አጥነት የተፈጠረበት ወቅት ነበር፡፤ ከዚህ አብዮት በኋላ ሻህ አገራቱን ለቆ ፈርጥጧል::

ይህንንም ተከትሎ የአብዮቱ መሪ የነበሩት አያቶላ ኮሚኒ በስደት ከቆዩበት ሀገረ ፈረንሳይ ወደ ሀገር ቤት ተመልሰው አብዮቱን ለማፅናት ለአስር ቀናት ያደረጉትን እልህ አስጨራሽ የአብዮት ሂደት ለማስታወስ ሲባል ከፌብርዋሪ አንድ እስከ ፌብርዋሪ አስር ዘንድ ለ40ኛ ጊዜ ዘንድሮ ህዝባዊ በዓሉ ይከበራል፡፤ አብዮቱ ከጅማሬው ኢራንን ለዘመናት ሲበዘብዙ የነበሩ ግለሰቦች በህዝባዊ ማዕበሉ ዝንዲወገዱ ያደረገ ነበር:: የአገሪቱ ባህልን ከማሳደግ ይልቅ በውጪ ባህል እንድትጥለቀለቅ ያደረገው የሬዛ ሻህ ስርዓት መወገድ ኢራናውያን ሀገርኛ በሆነ ባህሎች እድገት ላይ እንዲያተኩሩ አድርጓል::

ይህ በዓል ለ40ኛ ጊዜ ሲከበር ኢራናውያ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ዘርፍ ያስመዘገቡትን ውጤት በማስታወስ ጭምር ነው:: በዘንድሮው በዓል ኢራናውያን በጋራ የሚያከብሩትና አንድነታቸውን የሚያስጠብቁበት ዓመት እንደሆነ በተለያየ ሂደት እየገለፁ ይገኛሉ:: ህፃን፣ ወንድ፣ ሴት አዛውንት በአንድነት በመሆን ባማረና በደመቀ ሁኔታ የባህልን ትዕይንት ህዝብን በማሳተፍ አብዮቱ ያስገኘላቸወን ነፃነት፣ እራስን በራስ ማስተዳደር፣ የውጭ ጣልቃ ገብነትን ለመከላከል ኢራን የሰራችውን እንቅስቃሴ በመግለፅ ይከበራል::

የኢራን አብዮት በቀጠናው ጠንካራና የተረጋጋ መንግስት እንዲፈጠር አድርጋል:: ይህም ውጤት በህዝባዊ ደጀንነት የተመዘገበ ነው::

አብዮቱ በሀገር ውስጥ የፍትሃዊ ማህበራዊ ኢኮኖሚ ተጠቃሚነት እየፈጠረ ይገኛል:: በትምህርት ዘርፍ በተደረገ ጥረት ከፍተኛ የሆነ የማህይምነት የመቀነስ ስራ በመስራቱ በተለያዩ የሳይንስ ዘርፎች ኢራን ተወዳዳሪ እንድትሆን አስችሏል::

በአብዮቱም ኢራን ዛሬ ያስመዘገበችው የጤና ለውጥን ጭምር በማሰብ ነው:: ኢራናውያን ከአብዮቱ በፊት ከነበራቸው የጤና ህክምና እጦት በመውጣት በአለማችን ላይ በህክምናው ዘርፍ ተመራጭ የሆኑ የህክምና መዳረሻ ለመሆን ትችል ዘንድ ኢራን እየሰራች ትገኛለች::

በአዕምሮ ቀዶ ጥገና በኩላሊት ንቅለ ተከላ፣ በአይን ህክምና፣ የህፃናት እንክብካቤ ተመራጭ የህክምናው ኢንዱስትሪ መዳረሻ ሆናለች::

በቴክኖሎጂ እድገትም ቢሆን እራሷን በአገር ቤት ቴክኖሎጂ በአገር ልጆች አዘምናለች:: የተለያዩ የህዋ ላይ ሳተላይቶች የተለያዩ የናኖ ቴክኖሎጂ ውጤቶች አስመዝግባለች::

ኢራን አመታዊ ጂዲፒዋ 430.7 ቢሊዮን ሲሆን ለእያንዳንዱ ሰው የነፍስ ወከፍ ገቢም 5415.21 የአሜሪካን ዶላር እንዲሆን አስችሎታል:: በውጭ ንግድ ግንኙነትም ከቻይና፣ ህንድ፣ ደቡብ ኮርያ፣ ቱርክ ጣሊያንና ጃፓን ጋር ከፍተኛ ግንኙነት መስርታ እየሰራች ትገኛለች:: በውጪ ንግድም ኢራን 101.4 ቢሊዮን በሚጠጋ ገቢ ከዓለማችን 23ተኛ ደረጃ እንድትገኝ አብዮቱ አስችሏል::

በአካባቢያዊ መረጋጋትም ኢራን በፀረ ሽብር ስራ ውስጥ በመካከለኛው ምስራቅና በፓርሺያ ገልፋ ሰላም ከማስከበር አንፃር በኢራቅና በሶርያ የዳኢሽን (አይኤስ አይኤስ)፣ አልቃኢዳን በተጠናከረ ሀይል በመዋጋት ና ከሌሎች ሀገራት ጋር ግንባር በመፍጠር ቀጠናውን ከሽብር የማፅዳት ስራ አከናውናለች:: የኢራቅ የፖለቲካ አመራርም በአካባቢው የሚስተዋለውን አለመረጋጋትና የፖለቲካ ኪሳራ በውይይት እንዲፈታ ትልቁን ኃላፊነት ወስደው እየሰሩ ባሉበት በዚ ጊዜ ይህ ህዝባዊ በዓል መከበር መቻሉ የኢራናውያንን ደስታ እጥፍ ድርብ ያደርገዋል::

# ታላቋ ኢራን ና የ1979 አብዮት

ታላቋ ኢራን የተመሠረተችው ከብዙ ሺ ዓመታት በፊት መነሻቸው የህንድና የአውሮፓ የዘር ሀረግ እንዳላቸው የሚነገርላቸውና አርያንስ ተብለው በሚጠሩ እውነተኞችና ቀናዎች እንደሆነ የታሪክ ምሁራን ይመሰክራሉ:: መኖሪያቸውንም የእውነተኞች ሀገር ኢራን ሲሉ ሰይመዋታል:: አርያንሶች ሀገራቸውን ከመሠረቱበት ጊዜ አንስተው ኢራን ብለው የሚጠሯት ቢሆንመ በአውሮፓውያን ጫና ለብዙ ዘመናት ፋርስ በመባል ስትጠራ ቆይታለች::

ይሁን እንጂ ከ 1928 ጀምሮ ፋርስ የሚለው ስሟ ቀርቶ ኢራን በሚለው የቀድሞ ስሟ መጠራት ጀመረች:: ኢራን በረጅም ታሪኳ 38 ስረወ መንግስታትና 446 ነገሥታት በመፈራረቅ መርተዋታል:: እኚህ ነገሥታት ራሳቸውን ስዩመ እግዚአብሔር አድርገው ስለሚቆጥሩ የሀይል በትራቸውንና ክንዳቸውን በህዝባቸው ላይ ያለ ከልካይ ሲያነሱ ቆይተዋል::

በመጨረሻም በኢራን ታሪክ የመጨረሻው ንጉሥ ወደ ሆኑት መሐመድ ሪዛ ሻህ ላይ ደረሰ:: መሐመድ ሪዛ ሻህ ወደ ንግሥናው መንበር የመጡት በ1941 ነበር:: ነገር ግን የሻህ አገዛዝ ፍፁም አምባገን እና በሙስና የተጨማለቀ በመሆኑ

በነባሩና በአይነኬው የንጉሡ ሥርዓት ላይ የተለያዩ ጥያቄዎች መነሳት ጀመሩ:: በሌላ በኩል ደግሞ የንጉሡን ክብር ከፍ በማድረግ ተዝቆ የማያልቀውን የኢራንን የነዳጅ ሀብት ወደ ሀገራቸው በማጋዝ የሚታወቁት ምዕራባዊያን በተለይም ስለ ህዝቡ ነፃነትና ፍትህ የሚታገሉ ታጋዮች መነሳታቸውን ሲያውቁ ከንጉሱ ጋር በመተባበር አብዮቱን ለማክሰም ሞክረዋል የሆነ ሆኖ የተዳፈነ እሳት አንድ ቀን መንደዱ አይቀርምና አያቶላህ ሩሐላህ ኾሜይኒ ለብዙ ዘመናት ያልተመለሰውን የህዝቡን ጥያቄ በማንሳት የኢራናውያንን ልብና ቀልብ በመሳብ አይነኬውን የሻህን ስረወ መንግስት ገርስሶ በመጣል የኢራንን እስላማዊ መንግስትን በ1979 አቋቋሙ::

በ1960ዎቹ የተቀጣጠለው የእስልምና አብዮት ኢማም ኾሜይኒ በፌብሩዋሪ 1, 1979 ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ በድል ተጠናቋል። በአስር ቀናት ውስጥ ብቻ (ማለትም በፌብሩዋሪ 11 ,1979) አብዮቱ ተጠናቀቀ። በኤፕሪል 1, 1979 በተደረገው ሪፈረንደም መሰረት 98.2 በመቶ የሚሆነው ህዝብ ደግፎትና መርጦት የኢራን እስላማዊ ሪፐብሊክ ተቋቋመ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በዚች ጥንታዊ ምድር በኢማም ኾሜይኒ መሪነትና በአያቶላህ አሊ ኻሜኒይ ተተኪነት አዲስ ዘመን ተበሰረ። የገገርዎቹ ተቀዳሚ አላማዎች የሚባሉት ገለልተኛነት፣ ነፃነት፣ የወሰን መከበር እና የኢራንን እስላማዊነት መጠበቅ ናቸው። ለ8 አመታት በዘለቀው በኢራቅ የጦርነት ጊዜያት እንኳን የህዝቡ ቀናኤነት ለአፍታ እንኳ አልተፈታም



ነበር። በአሁኑ ወቅትም ቢሆን ኢራን ጥሩ ደረጃዎችን በማለፍ ብሩህ ተስፋ ወዳለው ጊዜ በመገስገስ ላይ ትገኛለች።

አያቶላህ ሩሖላህ ኾሜይኒየኢራን እስላማዊ መንግስትን በ1979 ካቋቋመ በኋላ ኢራን የራሷን ውብ ባህልና ታሪክ ጠብቃ ያለ ማንም የውጭ ሀይል መሰልጠን እንደምትችል በማስገንዘብ የወጣቱን ቀልብ ለምዕራባዊያን ከመገዛት ነፃ ያወጡና ሀገራቸውንም እንዲወዱ፤ለሀገራቸው ሁለንተናዊ ዕድገት እንዲተጉ ያደረጉ ታላቅ መሪ ናችው:: ለዚህ ነው ዛሬ ኢራን የምዕራባዊያንን ዛቻና ማስፈራራት ሳይበግራት የራሷን ባህልና ቋንቋ እንዲሁም ታሪክ ጠብቃ አሁን ለደረሰችበት የእድገት ደረጃ ላይ የደረሰችው እነዚህም የ1979 አብዮት ፍሬዎች መሆናቸውን ታሪክ የማይዘነጋው ነገር ነው::

# ጫንቃዬ ሕወሓትን . . .

ከገጽ 2 የዞረ

አካሄድ ትክክለኛነት እና ፍትሃዊነትን ተረድተው “አይዞህ” ብለው የሞራል ብርታት የሰጡኝ ከፍ ሲልም ከጎኔ ቆመው የታገሉ ጥቂቶች አልነበሩም። ነገር ግን ወደ ላይ በወጣሁ ቁጥር የተበጀልኝ ሴራ ይበልጥ እየተወሳበሰበ መጣ። በተለይም የጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዴሊቨሪ ሚኒስትር ሆኜ በተሾምኩ ማግስት ጀምሮ ጥቃቱ ተቋማዊ መልክ እየያዘና ትልልቅ ቱባ የህወሃት ባለስልጣናትም ጭምር የሚሳተፉበት ወደመሆን ተሸጋገረ። የፖለቲካ እስረኞችን ሙሉ በሙሉ ለመፍታትና የሰቆቃ ማእከል ሆኖ ሲያገለግል የነበረው ማእከላዊ ተዘግቶ ወደ ሙዝየምነት እንዲቀየር ተወሰኖ ለመላው ህዝባችን ይፋ እንዲሆን ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በግለሰብ ደረጃ ይህ ነው የማይባል ጥቃትና ዛቻ እንዲሁም ማስፈራሪያ ደርሶብኛል።

የአገሪቱ ቁንጮ የህወሓት ባለስልጣናት የተሳተፉበት ይኸው ጥቃት “ለምን የፖለቲካ እስረኛ አለ ብለህ ይፋ አወጣህ፣ ውሳኔው በቀጥታ twitter እና Facebook ለአለም በማሰራጨት የጠቅላይ ሚንስትሩን ውሳኔ የማስቀየር እድላችንን ዝግ እንዲሆን አድርጋሀል ፣ በአጠቃላይ ከጠቅላይ ሚንስትር ሃይለማርያም፣ ከምክትል ጠቅላይ ምንስትር ከአቶ ደመቀ መኮንን፣ ከኦህዴድ አመራሮችና ከፈረንጆች ጋር ወግነህ የስርአት ለውጥ ለማምጣት የምትንቀሳቀስ የቀለም አብዮተኛ ነህ፣ ከዚህ በኋላ ከአንተ ጋር የምንነጋገረው በጥይት ነው!” በማለት ውሳኔው ከተላለፈባት ከዚያች ምሽት ጀምሮ ከፍተኛ ዛቻና የስነ-ልቦና ጫና ከትላልቅ የህወሓት ባለስልጣናት በተደጋጋሚ በተለያዩ ወቅቶች ደርሶብኛል።

እዚህ ላይ ግልፅ የሆነልኝ ነገር የድርጅቱ አመራሮች ምን ያክል እንደተበላሹና በታሰሩ ዜጎች መፈታት ምን ያክል እንደሚያማቸው ነው። ጫናው ሲያይልና ይፋ የተደረገበት ምክንያት ግቡን ሲመታ በፌስቡክ ገፅ የተፃፈንውን ነገር ትንሽ ቆየት ብለንና በነጋታው ደግሞ በተለይም የውጭ ሚዲያ ወኪሎች የቀድሞውን ዘገባ እንዲያስተካክሉ አድርገናል። ነገር ግን መረጃው አስቀድሞ በበቂ መጠን ስለተሰራጨ ግቡን ሊመታ ችሏል።

ከዛ በኋላም ቢሆን በነበሩት ተደጋጋሚ የህወሓት ስብሰባዎች ተመሳሳይ ስሞታና ዛቻ ደርሶብኛል። በእርግጥ አገራችንን ወደ ትልቅ እስር ቤት እየቀየራት የነበረው የጥቂት አምባገነኖች እርምጃ መቆም እንዳለበትና የነሱ ሰለባ የሆኑት የህሊና እስረኞች ከገቡባቸው ነጻ መውጣት እንዳለባቸው ካመንኩኝ ውየ አድሬያለሁ።

ከሁሉም በላይ ደግሞ የታገልኩት የሰብአዊ መብት ለማክበር ነው፣ እስረኞች በህግ ጥላ ስር ሊመቱ አይገባም እያለ በአደባባይ ላይ ያለአንዳች ሃፍረት የሚለፍፍ ስርአት ራሱን ፉርሽ በሚያደርግ ሁኔታ ደብዳቢ እና ተጋራፊ ሆኖ መገኘቱ አንድ በቅርብ በማውቀው ወዳጄ ላይ ተከስቶ ካገኘሁት ጊዜ ጀምሮ የህሊና እረፍት ሊሰጠኝ ባለመቻሉ ይህ ሁኔታ መለወጥ እንዳለበት ካመንኩኝ ሰናባብቻለሁ።

እናም መልካም እድልና ምቹ ሁኔታ ሲፈጠር መጠቀም ይገባ የነበረ በመሆኑ የህሊና እስረኞችን ለመታደግና ማዕከላዊን ወደ ሙዝየም ለመቀየር በተደረገው ጥረት ግንባር ቀደም ሚና ከተጫወቱ መሪዎች ጋር ሆኜ የድርሻዬን ተወጥቻለሁ። በዚህ ውሳኔ ሂደት ውስጥ የበኩሌን የጠብታ ታክል ድርሻ ተወጥቼ ከሆነ በህይወቴ የምኮራበት ትልቅ ተግባር እንጂ በምንም መልኩ አላፍርበትም። ሆኖም የአምባገነንነት እርካቡ እየተናደበት እንደነበር የገባው ህወሓት ውስጥ የመሸገው ቡድን በርግጎና በአልሞት ባይ ተጋዳይነት ተነሳስቶ ለዚህ ውሳኔ ድርሻ ነበራቸው በሚላቸው ሃይሎች ያነጣጠረ እርምጃ መውሰድ መቼ ይቀርና!!

በተለይም ደግሞ አክራሪው ቡድን በህወሓት ውስጥ መሽጎ እንደሚገኝ የውስጥ አርበኛ ወስዶኝ ነበረና አንገቴን እንድደፋና ሽሽቼ እንድጠፋ ለማድረግ የተቀነባበረ የስም ማጥፋትና የጥቃት ውርጅብኝ ተካሂዶብኛል። ይህ ሁሉ ሁኔታ እየተካሄደ በነበረበት ሁኔታ እንኳን ምርጫየ ትግል እንጅ መፈርጠጥ አልነበረም።

“ሳይደግስ አይጣላም!” እንዲሉ አበው . . . ከዛ በኋላ በፍጥነት በተቀያየረው ሃገራዊ ሁኔታ ትኩረታቸውን ስቦት እና አዛብቶት እንጅ የታሰበልኝን እና የተደገሰልኝማ ነገር አሳምሬ አውቃለሁ። ይህ ሁሉ እየሆነም ቢሆን ምርጫዬ መሸሽና አንገት መድፋት ሳይሆን አንገትን ቀና አድርጎ መታገል ነበር። ምክንያቱም ጥቃቱ በእኔ በግለሰብ ደረጃ ላይ ያነጣጠረ የነበረ በመሆኑ ነው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የራያ ህዝብ ያለ ምርጫውና ያለውዴታው ገና ከማለዳው “ሆ. . .!” ብሎ የተቃመው አከላለል ከተወሰነበት ጊዜ ጀምሮ መግደልና ማሳደድን መቀጠላቸው ህዝቡም በተደራጀ መልኩም ባይሆን ትግሉ አላቆመም ነበር። የራያ ህዝብ ትግል ፍሬ እንዳያፈራ ካደረጉት መሰረታዊ ምክንያቶች/ጉዳዮች አንዱ ትግሉ በተደራጀ መንገድ አለመከናወኑ መሆኑን አውቆ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በተደራጀ መንገድ ወደ ትግል ገብቷል። ወንድሜ ከሆነውና በጠንካራ ማህበረሰባዊና ስነልቦናዊ ገመድ ከተሳሰርኩት የአማራ ህዝብ ጋር አብሬ ልኑር ብሎም እየተዋደቀ ይገኛል።

ይህ ሲሆን ታዲያ የኢትዮጵያ የናሽናል ጥያቄ (የብሄረሰቦች ጥያቄ) ብዝሃነትን የማስተናገድ ችሎታ እጦት ነውና “ኢትዮጵያ ብዝሃነትን ልታከብር ይገባታል!” ብሎ በፕሮግራሙ ላይ በነጭና በጥቁር በደማቁ የጻፈው እንዲሁም በዛ ላይ ተመስርቶም ላለፉት 45 አመታት የፖለቲካ ሞብላይዜሽን ያደረገው ህወሓት ምላሽ ጥይት፣ ግድያ፣ ማፈናቀልና እንግልት ሆኗል።

ነገሩ “ሆድ ሲያውቅ ደሮ ማታ ነው!” እና ድርጅቱ ለፕሮግራሙና ለዚያም ሲባል መስዋእት ለሆኑት ታጋዮቹ ክብር እንደሌለው በአደባባይ አስመስክሯል። የማንነት ጥያቄን ያነሱ እምቦቃቅላ ህጻናትን እስከ አፍንጫው በታጠቀው የክልሉ ልዩ ሃይል አናት አናታቸው እየተመቱ በእንጭጩ ተቀጭተዋል።

በአጠቃላይ የራያ ህዝብ የተደራጀ እንቅስቃሴ ማድረግ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የስንቱ ህይወት እንደተቀጠፈ፣ ለእስር እንደተዳረገና እንደተፈናቀለ ቤቱ ይቁጠረው። አካባቢው በዚህ ምክንያት ለከፋ ማህበራዊ መስቅልቅልና ቀውስ እንዲሁም ለጸጥታ ቀውስና ፖለቲካዊ አለመረጋጋት ተዳርጓል። በራያ ህዝብ ላይ ይህን የመሰለ ግፍና መከራ እየፈጸመ ካለ ድርጅት ጋር አብሬ እንድቀጥል ህሊናዬ አልፈቀደልኝም።

በእርግጥ ገና ከገባሁ በጥቂት አመታት ውስጥ ልቤ ሸፍቶ በመንፈስ የራቅኩት ድርጅት ዛሬ ቀኑ ደርሶ በወጉ የአባልነት ግንኙነታችን ያበቃ ዘንድ የራያው ጉዳይ አንዱ ምክንያት ሆኗል።

ከሁሉም በላይ ደግሞ በጠቅላይ ሚንስትር ዶ/ር አብይ አህመድ እና በምክትል ጠቅላይ ሚንስትር ደመቀ መኮንን የሚመራ የለውጥ እንቅስቃሴ መጀመሩ ይታወቃል። በእርግጥ የአገራችን ችግር መሰረታዊ ለውጥ የሚሻና ውስብስብ ቢሆንም ችግሩን የሚመጥን መሰረታዊ የለውጥ ፕሮግራም ተነድፎ ተግባራዊ እየተደረገ እንደሆነ መናገር ይቻላል።

ህወሓት በጥቂት ጠባብ ጸረ ለውጥ ቡድን ተጠልፎ ከሃገራዊ ለውጥ ጎን መቆም ሳይሆን ፀረ- አቋምን ምርጫው አድርጎ ለውጡ የትግራይን ህዝብ ጨምሮ መላው የአገሪቱ ህዝብ የሚጠቅም ቢሆንም ቅሉ፣ የውስን ሰዎች ጥቅም የሚያስቀር ሆኖ በመገኘቱ ብቻ ድርጅቱ ሊታገልለት የሚገባውን የትግራይ ህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ሳይሆን የጥቂት የህወሐት ባለስልጣናት ጥቅም ለማስከበር ሲል ለውጡን ተቃርኖ ብቻ ሳይሆን አፍራሽ በሆነ የሰላ ጥግ ላይ ቆሟል።

በመሰረቱ ዲሞክራሲም ሆነ እኩልነት የትግራይ ህዝብ ለዘመናት የታገለላቸው እና ውድ ልጆቹን የገበረላቸው የህልውና ጥያቄዎች እንጂ ባለጋራዎቹ አይደሉም። አዲሱ የለውጥ ፕሮግራምም ተንጋዶ የበቀለውንና የማቃናትና አሜኬላውን የመንቀል እንጅ ከትግራይ ህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ተቃርኖ የመጣ አይደለም። ህወሓት በዚህ ታሪካዊ ወቅት እየተወሰደ ያለውን ትክክለኛ እርምጃ የመቃወም ግዙፍ ስህተት ከድርጅቱ ጋር አብሬ እንዳልቀጥል ካደረጉኝ መሰረታዊ ምክንያቶች ሁለተኛው ነው።

ከዛሬ ነገ ችግሮች ተቀርፈውና ተሻሽለው ከመስመር የወጡ አካሄዶችም ፈር ይዘው ይራመዳሉ በሚል ትዕግስትና ተስፋ፣ ብዙ ነገሮችን በራሴ ይገፎ እየታገልኩ ቆይቻለሁ። በግሌም ሆነ በተገኘሁበት ማህበረሰብ ላይ እጅግ መራር ውርጅብኝ እየወረደ፣ ይባስ ብሎም በአገር ደረጃ ነገሮች እየተበለሻሹ እየሄዱ እንኳ ነገሮችን ለማቃናትና ለማሻሻል የበኩሌን እልህ አስጨራሽ ትንቅንቅ አካሂጃለሁ። የሆነ ሆኖ ከግትር አቋማቸው ፈቀቅ የማይሉ ተቸካዮች በህዝብና በአገር ላይ የሚያደርሱት ግፍ አልበቃ ብሏቸው፣ በተገኘችው ጭላንጭል ዕድል ይህን መከራ ለማስቆም የሞከርኩትን ግለሰብ ስም ለማጥፋት በየመንደሩ ሲባዝኑ ይውላሉ።

ከጥንት ጀምሮ ለነፃነት ከኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ጋር አብሮ የተዋደቀውን የትግራይ ህዝብ፣ ዛሬ እንደሰብዓዊ ምሽግ ተጠቅመው ሊለያዩት ቢሞክሩም፣ ይህ የአክራሪ ወንጀለኞች የቀን ቅዠት እንደጉም መብነኑ እና መክሸፉም የማይቀር ነው! ኢትዮጵያዊነትን ከትግራይ ህዝብ ልብ ላይ መፋቅ ከቶም የማይቻልና ዛሬም ቢሆን እላዩ ላይ ተጋድመው የተጫኑትን የቀንበር እንጨቶች ሰብሮ ዳግም ለእኩልነትና ነፃነት እንደሚበቃ ቅንጣት ጥርጥር የለኝም!

በመጨረሻም ፀረ-ለውጥ እና ፀረ-ዴሞክራሲ ከሆነው ድርጅት ጋር ለመቀጠል ህሊናዬ ባለመፍቀዱ በገዛ ፍቃዴ ከድርጅት አባልነት የለቀቅኩኝ መሆኑን እያሳወቅኩ በቅርቡ ያታግለኛል ከምለው ድርጅት ጋር ተደራጅቼ የራያና መላ የአገራችን ህዝብ ጥያቄ ይበልጥ መልስ እንዲያገኝና ለውጡ ተጠናክሮ እንዲቀጥል እየተደረገ ያለውን ርብርብ አቅም በፈቀደው ሁሉ ለማገዝና ለመታገል እንደምሰራ ከወዲሁ ለማሳወቅ እወዳለሁ። የራያ ህዝብ በተድላና በፍቅር ከወሎ አማራና ከመላው የአማራ ህዝብ ጋር ለዘላለሙ ይኖራል። ምክንያቶቹ በትንሹ እነዚህ ሲሆኑ በማወቅም ይሁን ባለማቅ በእስካሁኑ የፖለቲካ ህይወቴ ያስቀየምኳችሁ ካላችሁ ከልብ የመነጨ ይቅርታን እጠይቃችኋለው።

ዛዲግ አብርሀ
ድልና ነፃነት ለራያ ህዝብ!

ዴሞክራሲና ሰላም ለመላ የአገራችን ህዝብ!



ተስፋ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ

# የጠቅላይ ሚኒስትሩ
## አስደንጋጩ የፓርላማ ሪፖርት

በዓለም ላይ እየታየ ያለው የሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ንግድ እና ዝውውር ለአፍሪቃ ቀንድ ሀገራት ሰላም እና ምጣኔ ሀብት እድገት መሰናክል ሆኗል እየተባለ ነው። በዚሁ አካባቢ ሕገ ወጡ የጦር መሳሪያ ንግድ በተለይ በሀገራችን እየተስፋፋ እንደሆነ በገልጽ እየታዘብን ነው።



የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቅርቡ 4ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 2ኛ ልዩ ስብሰባ አካሂዷል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ የምክር ቤት አባላቱ ላቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሰጡት መልስ ላይ እንደተናገሩት ”የሕገ-ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር ከመበራከቱ የተነሳ ኢትዮጵያ ካላት የሕዝብ ቁጥር የሚበልጥ የጦር መሳሪያ ያላት ሀገር ሆናለች” ብለዋል፡፡ ሪፖርቱ እውነት ቢሆንም ለመስማት ግን በጣም አስደንጋጭና የሚሰቀጥጥ ነበር። ይህ ቁጥር የሚያመለክተው ሁሉም ሰው ራሱንና ሌላውን የሚያጠፋበት መሳሪያ እንደታጠቀ ነው የሚያሰየው። ይህን የጦር መሳሪያ ብዛቱን ማንም ሰው ሲሰማው እንደ ቀላል ነገር አድርጎ ሊመለከተው ይችላል። ነገር ግን ቁጥሩ ለሀገርና ለሕዝብ ትልቅ አደጋ ይዞ እንደመጣና፤ሕዝብ በቀላሉ ወደ ግጭት በሚገባበት ጊዜ ለፀጥታ ኃይሎችም ፈተና ይሆናል።ማሳያችን በኦሮሚያ እና በኢትዮጵያ ሶማሌ የነበረውን ግጭት ነው። ከፖሊስ እና ከክልሎች ልዩ ኃይሎች በላይ ሆኖ ለመከላከያ ሰራዊታችን ጭምር ፈተና ሆኖ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው።

በአሁኑ ሰዐት በዓለም ላይ በጦር መሣሪያ ሽያጭ ከ60 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ የሚንቀሳቀስበት ሕገ ወጥ የንግድ ዘርፍ ነው። በዚህ የሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ንግድ እና ዝውውር ሽያጭ ከፍተኛውን ደረጃ የያዘችው ዩናይትድ ስቴትስ ከገበያው 40 በመቶውን ትሸፍናለች።ከሷ ቀጥሎ ብሪታንያ፤ ቻይና፤ ፈረንሳይ፤ ጀርመንና ሩሲያ እንደ አጠራራቸው ይከተላሉ። በየዓመቱ የጦር መሣሪያ ዝውውርና ሽያጭ በተመለከተ እነዚህ አገሮች ሕገ ወጥ ንግዱን ለማቆም ድርድርና ውይይት ቢያደርጉም፤ በእውነተኛነት ድርድሩን ተቀብለው የጦር መሣሪያ በሕገ ወጥ መልክ ላለመሸጥ ስምምነታቸውን ሲያከብሩ እስካሁን ድረስ አልተመለከትንም። እናም እነዚህ ዋነኛ የጦር መሣሪያ አቅራቢ ሀገሮች የትኛውንም የሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር የቁጥጥር ውል በቀጣይም ቢሆን በቀላሉ የሚቀበሉት አይመስልም። በየዓመቱ ስድስት ቢሊዮን ጥይት የምታመርተው አሜሪካ የጥይት ሽያጭ ነገር ከውይይቱ እንዲካተትባት እንኳን አትፈልግም። ቻይና በበኩሏ በማደግ ላይ ላሉት ሀገሮች በገፍ የምትሸጠው የአነስተኛ የጦር መሳሪያ ሽያጭ በውል ውስጥ እንዲታሰርባት አልፈቀደችም።

የዩናይትድ ስቴትሱ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ የጦር መሣሪያ ሕግን በተመለከተ በየጊዜው በጦር መሳሪያ የሚፈፀመው አስከፊ የጭካኔ ድርጊት እንደ ሀገር ቆም ብለን ልናስብ ይገባል ሲሉ አበክረው በተደጋጋሚ ይገልፁ ነበር። በቅርቡ በካሊፎርኒያዋ ሳንበርናርዲኖ፣ 14 ንጹሓን እንደተገደሉበት ዓይነቱ አሰቃቂ ድርጊት የጦር መሳሪያ በግለሰቦች እጅ መያዝ እንደሌለበት አንዱ ማሳያ ነው ብለው ተናግረው ነበር፣ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ ሕጉን ለመቀየር ያስገደዳቸው ዋነኛ ምክንያት በወቅቱ እንዳሉት "እንደ ማኅበረሰብ እራሳችንን መመርመር ይኖርብናል" በማለት ነበር የጦር መሳሪያ ንግድ እንዲቀር ያሳሰቡት፤ በተጨማሪም የጦር መሣሪያ ግለሰቦች እጅ በቀላሉ የሚገባበትን ሁኔታ ለማክበድ፣ መሠረታዊ እርምጃዎችን መውሰድ ወሳኝ ነው ብለው ነበር። ዛሬም የኛው የሀገራችን መሪ ዶ/ር ዐቢይ አሕመድም በቅርቡ ለፓርላማው አስደንጋጭ ሪፖርት አቅርበዋል፤ ይህም የሕገ-ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር ከመበራከቱ የተነሳ ኢትዮጵያ ካላት የሕዝብ ቁጥር የሚበልጥ የጦር መሳሪያ ያላት ሃገር ሆናለች” ብለዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ መደንገጥ ካለበት ከሌላው ጊዜ ይህን ሪፖርት ባዳመጠ እለት ሊሆን ይገባል። ምክንያቱም መልእክቱ ኢትዮጵያ አገራችን ሰላማችንን አንድነታችንን የሚያደፈርስ የጦር መሳሪያ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር በላይ ነው ማለት ነው።

ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ለፓርላማ ሲያቀርቡ “የሕገ ወጥም ሆነ ሕጋዊ መሣሪያ ዝውውር አደገኛ ነው። ስለ መሣሪያ ጉዳት ከአሜሪካ መማር አለብን፤ በዚያ ጥቂት የታጠቁ ግለሰቦች ተማሪዎችን ሲገድሉ ዐይተናል” ብለዋል። የአሜሪካን በሕጋዊም ሆነ በሕገ ወጥ መልክ የጠፋው የዜጎች ሕይወት የሁለት ዓመት ዳታ ብቻ ብንመለከተው ደግሞ የጉዳዩን አሳሳቢነቱ በደንብ መገንዘብ እንችላለን፤በፈረንጆቹ አቆጣጠር 2015 ▶

ብቻ በአሜሪካ 372 ጅምላ የጦር መሣሪያ ጥቃቶች የደረሱ ሲሆን፤ 475 ሰዎች ሕይወታቸውን ሲያጡ 1800 የሚደርሱት ቆስለዋል። በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2016 ብቻ አሜሪካ ውስጥ 11004 ሰዎች በጦር መሣሪያ ተግደለዋል። 5500 ደግሞ በራሳቸው መሳሪያ ራሳቸውን አጥፍተዋል። ከዚህ በተጨማሪ በጅምላ ጭፍጨፋ 71 ሰዎች ሕይወታቸውን አጥተዋል። (ምንጭ FBI Las vegas Police )

ሁለተኛው የአሜሪካ ሕገ-መንግሥት ማሻሻያ፣አባማ እና ሪፐብሊካን ፓርቲ የአሜሪካ ሕገ-መንግሥት ለሃያ ሰባት ጊዜያት የተለያዩ ማሻሻያዎች ተደርገውለታል። ከነዚህም መካከል የጦር መሳሪያ የማስቀመጥ እና የመታጠቅ መብትን ዕውቅና የሰጠው ሁለተኛው የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ነው። በዚህ መብታቸው በመጠቀም ወደ 270 (ሁለት መቶ ሰባ) ሚሊዮን የሚገመቱ አሜሪካውያን እራሳቸውን እንዳስታጠቁ የጀኔቫው ቀላል መሳሪያዎች አጥኚ ድርጅት ጥናቱን አቅርቧል። ከእነዚህ ታጣቂዎች መካከል ግን መሣሪያቸውን ያስመዘገቡት 3.1 ሚሊዮኑ (ሶስት ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ ) ብቻ ናቸው። ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያትም የመሳሪያ ታጣቂዎች መሳሪያቸውን እንዲያስመዘገቡ የሚያስገድድ ሕግ ባለመኖሩ ምክንያት ነው ብሏል።

በሀገራችን በተለይ በአንዳንድ ክልሎች የጦር መሳሪያን መታጠቅ የሚችለው ማን ነው በሚለው ላይ ወጥ የሆነ ህጋዊ አሰራር የለም። የጦር መሳሪያዎች የአእምሮ ህሙማን እና አንዳንዴም የወንጀል ሪከርድ ያለባቸው ሰዎች እጅ በመግባቱ የጉዳዩን አሳሳቢነት በእጅጉ ያከፋዋል።ለምሳሌ በሀገራችን በግልፅ የሚታወቅ ሕጋዊ የጦር መሳሪያ ነጋዴ እስከሌለ ድረስ ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ይዞ ለሚመጣ ግለሰብ ሕጋዊ እውቅና መስጠት የወንጀል ተባባሪ ከመሆን የሚተናነስ አይደለም። በቅርቡ በአማራ ክልል እየሆነ ያለው ይህ ነው። የቀነ ገደብ ተሰጥቶ መሳሪያቸውን እንዲስመዘግቡ ፍቃድ ሲሰጥ ፤በርካታ የኅብረተሰብ ክፍል መሳሪያ በሕገ ወጥ መልክ ለመግዛት ሲራወጥ እንደነበር ምስክር መሆን እችላለሁ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፓርላማ እንደተናገሩት "አርሶ አደሩ የጦር መሳሪያ ካልያዝኩ ራሴን መከላከል አልችልም ብሎ ስለሚያምን፤መሬት ሸጦ መሳሪያ ይገዛል።" በተለይ አሁን ላይ የጦር መሳሪያን ሸጦ ገንዘብ ማትረፍን እንደሥራ የወሰደ ኃይል አለ፤ ለዚህም ሲባል መሬት ተሸጦና ከባንክ ብድር ተወስዶ የሚሰራ ንግድ እንደሆነ ለፓርላማ አባላት ተናግረዋል። እንዲህ አይነት ሕገ ወጥ ሥራዎች እንዲስፋፋ ምክንያት የሆነው በክልሎች ያለው የተዘረከረከ አሠራር ፈር መያዝ ባለመቻሉ ነው። ለማሳያነት የሀገርን ሰላም ይጠብቃል፤ ሕዝብን ከወንጀል ይከላከላል የተባለው የመንግሥት አካል፤ በሕገ ወጥ የመሳሪያ ዝውውር ወይም ሽያጭ ላይ ከተሰማራ ሁኔታዎቹ ብዙ ነገር ያሳየናል ፤ ለዚህ አብነት የሚሆነው የባህርዳሩ የፖሊስ አዛዥ ነው። ይህ የጸጥታ ክፍል ኃላፊ በቤቱ ከ450 በላይ ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ አስቀምጦ እንደተገኘ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። የኃላፊው ተግባር ሕገወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር በክልሎች ሥር እየሰደደ እንደመጣ ማሳያ ነው።

ለዚህም ይመስላል የአማራ ክልል ሚሊሻ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ለአማራ ቴሌቪዥን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደጠቀሱት፤ ማንኛውም ሰው በመንግሥት ካልተፈቀደ በስተቀር ሕዝብ በሚበዛባቸው የአገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ሕዝባዊ ስብሰባዎች እና ሰላማዊ ሰልፎች የጦር መሳሪያዎችን ይዞ መንቀሳቀስ እንደማይቻል መመሪያ ያስተላለፉት፤ይሁን እንጅ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በክልሉ ትልልቅ ከተሞችን ጨምሮ አንዳንድ አካባቢዎች የጥይት ተኩሶች ይደመጣሉ። ዝርፊያ እና አግባብ ያልሆኑ እንቅስቃሴዎችም እንደሚታዩ ጠቅሰው የነበረው። የዚህ አይነት ልቅ ህገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር የማህበረሰቡን ሰላማዊ እንቅስቃሴ የሚያውክ ከመሆኑ ባሻገር ንፁሃን ዜጎችን ለህልፈት ሊዳርግ የሚችል አደገኛ አካሄድ ነው።

በአንዳንድ የሀገሪቱ ክልሎች የሚኖሩ ሕዝቦች መንግሥት የፀጥታ ኃይል ላይ አመኔታ ሲያጣ ቤተሰቡን ለመጠበቅ ወደ ጦር መሳሪያ ግዢ እያመራ እንደሆነ በዐይን ለመታዘብ ችለናል። በተለይ በአማራ ክልልና በትግራይ፣ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልል፣ በደቡብ አካባቢም ያሉ የወሰንና የግዛትና የድንበር ይገባኛል ጥያቄዎች የሚነሱበት አካባቢ ሕዝቡ አሁን ካለው የመፈናቀል እና ሕገ ወጥ ዝርፊያ ለመከላከል ከመንግሥት የፀጥታ ኃይል በላይ ሕገ ወጥ መሳሪያን በመግዛት እራሱን ለመከላከል ዋነኛ መከታ አድርጓል፣ በተጨማሪም የፌዴራል መንግሥቱ ውስጣዊ ችግር ባለባቸው ክልሎች የችግር አፈታት መንገድ ደካማ በመሆኑ የተነሳ ነው የሚሉ ወገኖችም አሉ። በአሁኑ ወቅት ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውርና በየክልል የታጠቀ ኃይል የሚሰራው የዘውግ አድሎ ታክሎበት በክልሎች ያለው ሁኔታ እጅግ አስፈሪ ደረጃ ላይ ደርሷል።

> **በአሁኑ ወቅት ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውርና በየክልል የታጠቀ ኃይል የሚሰራው የዘውግ አድሎ ታክሎበት በክልሎች ያለው ሁኔታ እጅግ አስፈሪ ደረጃ ላይ ደርሷል**

የሕገ ወጥ የጦር የመሳሪያ ዝውውሩ እልባት ካላገኘ አሁን ያለውን የሀገሪቱ አንፃራዊ ሰላም ወደ ኋላ የሚመልስና የሚፈጠረውን ግጭትም የሀገሪቱ የፀጥታ ኃይል ሊያስቆመው የማይችል ከባድ ይሆናል። በዚህም በክልሎች እና በፌደራል ሥርዓቱ በቀጥታ ችግር ውስጥ ይገባሉ። ሕገ ወጥ የጦር መሳሪያን ዝውውር አለመከላከልና ከሕዝቡ ቁጥር እስኪበልጥ ድረስ ቁጭ ብሎ መመልከት ዞሮ ዞሮ ዳፋውና ችግሩ ለመንግስት፤ለሀገርና ለሕዝብ የሚተርፍ ነው።

ስለዚህ የክልልና የፌደራል መንግሥት የፀጥታ አካለት፣ የጉምሩክ ሠራተኞች እና ሕዝቡ በአጠቃላይ ከስር ከስር እየተከታተሉ እንዲህ ያሉ ችግሮችን በአጭሩ መቅጨት ይኖርባቸዋል። ችግሩ በዚህ ከቀጠለና በቶሎ መቋጫ የማያገኝ ከሆነ፣ ሀገሪቷ ወደ መበታተን አቅጣጫ ልትሄድም ትችላለች።

ታድያ ከቁጥራችን በላይ የሆነውን አጥፊ የጦር መሳሪያ ብዛቱ እንደተገለፀው እንዳለ ይቀመጥና አሁን እንደ አገር ምን እናድርግ? በኔ እምነት ከቁጥራችን በላይ የሆውን የጦር መሳሪያ ከስራ ውጪ ማድረግ የሚቻለው እያንዳንዳችን የጥላቻ ስሜት እንዳይኖረን፤ፍቅርና አስተውሎት ከግል እስከ ከቤተሰባችንና ጎረቤቶቻችን ድረስ እንዲኖር ማድረግ፤በቋንቋችን ልንግባባ እንጂ በቋንቋችን የምንጣላ ወይም የምንለያይ እንዳልሆነ በመገንዘብ መተባበራችንና መደጋገፋችን ለአገር ጠቃሚ መሆኑን መገንዘብ መቀራራብ እንደሚገባ ማስተማር። በሀገራችን ባሉ ዘውጎች መካከል ያለውን የደንበር የወሰን ጥያቄዎች በፀጋ ተቀብሎ ጠቃሚ ውይይትና መተማመን በመፍጠር በጨዋነት ደንብ እንደ አንድ ቤተሰብ አባል ቁጭ ብሎ ፖለቲከኞች ሳይሆኑ ህዝቡ በራሱ ባህላዊ መንገድ እንዲወያይና እንዲፈታው ማድረግ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በመላው ኢትዮጵያ የመኖርና የመስራት መብት እንዳለው ማስገንዘብ።

በዜጎች መካከል ወንድማማችነት/እህትማማችነት ጠንካራ እንዲሆን በየትምህርት ቤቱ ፤በሥነ ጥበብ ፤በስእል፤በሙዚቃዎች እንዲተላለፉና ለሕዝቡ እንዲደርሱ የማድረግ ኃላፊነት መንግሥትና የሚመለከታቸው ሁሉ እንዲሆን ማድረግ፤ ከፖለቲከኞች በላይ የሕዝብ ለሕዝብ ውይይት በየክሎቹ በተከታታይ እንዲካሄድ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። በመቀጠል በፖለቲከኞች እና በሕዝቦች መካከል ያለውን የቂም በቀል አዙሪት በጣጥሶ እኩልነትና ፍትህ የሰፈነባት፣ የሀገሪቱን ዳር ድንበር የሚጠብቀው የፀጥታ ሀይል ያለ አድሎ ሁሉንም በእኩልነት ካገለገለ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በኩራት የሚኖርባትና የሚሰራባት ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ከተቻለ የጦር መሳሪያው የጥፋት ሳይሆን የብዛት ብቻ ማድረግ የሚቻልበት መንገድ አስቀድሞ ማሰብም ጠቃሚ ነው።

ኢትዮጵያ ለዘላለም በክብር ትኑር

# የዘመናዊ ፖለቲካችን. . .

ከገጽ 7 የዞረ

እነዚህን ተቋማት መገንባት እስካልቻልን ድረስ ነገራችን ሁሉ የእንቧይ ካብ መሆኑ ይቀጥላል::

## 6ኛ. እስከሞት ድረስ የምንፀናለቸው መርሆዎች ባለቤት መሆን

ከአያሌ የፖለቲካ ችግሮቻችን በተጓዳኝ ይኸን ያህል ዘመን አገዛዝ ይሰለጥንብን ዘንድ ግድ ያሉን አያሌ ሁኔታዎችን ማንሳት ይቻላል:: ከእነርሱ ውስጥ አሸርጋጅነት ጎላ ብሎ የሚታይ ይመስለኛል:: በየዘመኑ ግፍን የሚቃወሙ የአይበገሬነት ተምሳሌት የሆኑ ጀግኖች ሀገራችን አጥታ ባታውቅም የሰንበሌጥ ፖለቲካ የሚጫወቱ አያሌ ወገኖች በየዘመኑ እንደ እንጉዳይ ፈልተው ሲያድሩ ይስተዋላል:: መርህ አልባነት የአድርባዮች መርህ ነው:: ከግፍ ከውሸት ከሕገወጥነትና ከግብረ ገብነት አፈንግጠና በፍርሃት ቆፈን ተቀይዶ ለግፈኞች ውዳሴ ማህሌት መቆም:: የመከራውን ሌሊት ያስረዘመው ይኸን የግፍ ቋት የሆነ አካሄድ በግል በማኅበረሰባችንም ሆነ በሀገር ደረጃ ከስሩ ተመንግሎ ሊጣል ይገባዋል:: እውነት፣ ነጻነትና ሰብኣዊ ልዕልና አቋራጭ መንገድ የላቸውም በመርህ በእውነትና በፍቅር ላይ ቆመን ህልማችንን ለመጨበጥ መትጋት ይገባናል::

## 7ኛ. ዘመኑን የሚመጥኑ አስተሳሰቦችን መታጠቅ

ስለ ኢትዮጵያን ጥንታዊ ገናና ሥልጣኔ ብዙ እናወሳለን:: የሚጎድለው እንዳች አገር የሌለ እስኪመስል ድረስ አብዝተን እናቆለጳጵሰዋለን:: የሚጎድለው ኖረም አልኖረ በሩቁ ዘመን አባቶቻችን የሠሯቸውን ነገሮች የሚጠጋ ነገር በዚህ ዘመናዊ ዓለም መሥራት አልቻልንም:: ሁኔታው በምን ዓይነት የአስተሳሰብ ድርቅ እንደተመታን ያሳያል:: ከቆዩ ክፉ አስተሳሰቦች መላቀቅ ደግሞ የሞት ያህል ያስጨንቃል:: ሰዎችን የሐሳብ መስመራቸውን ተከትሎ ከመከራከር ይልቅ በዘር ወይንም በጥቅም መነፅር ብቻ የማየት ሀሳብ ተፀናውቶናል:: ይህን መሰሉ የፖለቲካ እይታ ደግሞ እጅግ ኋላቀርና በማኅበረሰብ እድገትም በስረኛውና በመጨረሻው ንጣፍ ላይ የሚገኝ ነው:: ወደ ኋላ ዕያየን ወደ ፊት እንሮጣለን:: ዘመኑን የሚመጥን አስተሳሰብ ባለቤቶች መሆን ይገባናል:: የመፍታት ችግር በስፋት ይታይብናል:: ተግባቦታችን እርስ በእርሳችንም ሆነ ከሌሎች ጋር ደካማ ነው:: በአመዛኙ ዝግ ነን ቢባል ማጋነን አይሆንም:: በዜግነታችን ላይ አለመተማመን ሲታከል ደግሞ ዳፋው ፈርጀ ብዙ ነው:: ስለዚህ ሁልጊዜም ለአዲስና ከእኛ ለተለዩ አስተሳሰቦች መዘጋጀት ያሻናል:: በሰብኣዊና ሥነ ልቦናዊ ብቃታችንም ሙሉ መተማመን ሊኖረን ይገባል::

## 8ኛ. ቁርጠኝነት

የምንቆምለትን ዓላማ ካልተገባ ጥቅም ከከንቱ ውዳሴም ሆነ ከአቋራጭ መንገድ በፀዳ መልኩ በእውነትና በምንሰራው ነገር ትክክለኛነት በፍፁም በማመን መጀመር ተገቢ ነው:: ለተሰጠንለት ዓላማ ለውጤት መብቃት የምንችለውን ሁሉ ለመክፈል ቁርጠኝነቱ ያስፈልጋል:: ብዙ ጊዜ የኋላ ታሪካችንን መለስ ብለን ስናይ ወይንም በትውልድ የኋልዮሽ ስንታይ ከሚያኮሩ ነገሮች መካከል በጉዳዮች ላይ የያዝነው አቋም ብቻ ሳይሆን አቋማችን ወደ ተግባር ለመለወጥ በወሳኝ ወቅት የምናሳየው ቁርጠኝነት ትልቁ መገለጫችን ይመስለኛል:: ይህን የመሰለውን ሰብዓዊ ጥራት ማዳበር ለግላዊ እድገትም ሆነ ለማኅበረሰብ እድገት የሚኖረው አስተዋፅኦ ከፍ ያለ ነው::

## 9ኛ. የታዛቢነት ፖለቲካ ይምከን

በተለይ ከ1960ዎቹ መሠረት ያደረገ እልቂት በኋላ ምሁራን ወደ ትግሉ መመለስ ቀጥ ያለ ተራራን የመቧጠጥ ያህል ከብዶን ቆይቷል:: አሁንም ቢሆን ትልቅ ሥራ የሚጠይቅ ጉዳይ ሆኗል:: የኢትዮጵያችን ምሁራን መናኸሪያ የውጭ ሀገር ታዛ ከሆኑ ከራርሟል:: በርግጥ ከእነርሱ ውስጥ ጥቂቶቹም በተለያዩ መንገዶች ታግለዋል:: አብዛኛው ግን በአርምሞ መታዘብን መርጠዋል:: አርምሞው ምን ዓይነት መንፈሳዊ ልዕልና እንዳጎናፀፋቸው የሚያቁት እነርሱ ብቻ ናቸው:: ያም ሆኖ በተለያየ መልኩ ሲደመጡ ስለኢትዮጵያ ፖለቲካና ፖለቲከኞች አያሌ ህፀፆችን ያነሳሉ:: የኢትዮጵያን ፖለቲከኛ ፖለቲከኞች ችግሮች ማውሳት ምንም ዓይነት ምሁራዊ ትንታኔ የሚያሻው አይደለም:: ፖለቲከኞች እውቀትም ሞራልም ሆነ ተሞክሮው ላይኖረን ይችላል፣ በአመዛኙም እንደዚህ ነው:: መፍትሔው ግን ፖለቲከኞች ሞራል ስለሌላቸው ሞራል ያላቸው ምሁራን መሳተፍ ወይንም ሌሎች ብቃቱና እውቀቱ እንዲሁም ሞራሉ ያላቸው ወገኖች እንዲታገሉ መታገል ነው::

## 10ኛ. ፀረ ዘረኝነት ዘመቻ ማወጅ

ሁላችንም አንድ የሚያደርገን አንድ ነገር ካለ የመጀመሪያው ፀረ ዘረኝነት ዘመቻ ይመስለኛል:: በዘረኝነት የሚያንስ፣ የሚከሰስና የሚጎዳ እንጂ እነዚህ እውነቶች ተቃራኒው የገጠመው ግሰብም ሆኖ ማኅበረሰብ ማቅረብ አንችልም:: “Groups are more immoral than individuals” (ቡድኖች ከግለሰቦች ይልቅ ኢሞራላዊ ናቸው) እንዳሉት ዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ በሀገራችንም ሆነ በሌሎች ሀገሮች የምንመሰክረው ከዚህ የተለየ አይደለም:: ዘረኝነት የአንድን ዘመን ትውልድ ብቻ ሳይሆን ያልተወለዱ ልጆቻችን ሀፍረት ስለመሆኑ ብዙ ማጣቀሻዎች ማቅረብ ይቻላል:: በሀገራችን ዕያየን ያለነው የዘረኞችና ዘረኝነት የይዋጣልን ጥሪ በጊዜ እልባት ካልፈለግንለት ልንነቃ ወደ ማንፈለግበት ክፉ ህልም ይዞን ይወርዳል:: እንደ ሀገር እንደ ትውልድም ሆነ እንደ ሕዝብ ከዘረኝነት በላይ የሚያከስረን የሚያረክሰንና የሚያሳንሰን የክፋ ደዌ ሊኖር አይችልም:: ስለዚህ በዘረኝነት ላይ ግንባር ላለመፍጠር ማናችንም በቂ ምክንያት ሊኖረን አይችልም::

## 11ኛ. “በራሳችሁ ላይ እንዲደረግ የማትሹትን በሌሎች ላይ አትድርጉ”

ይህ ኃይለ ቃል የሃይማኖቶቻችን ሁሉ ወርቃማ መርህ ነው:: ምንአልባት ስንክሳር ለበዛበት የፖለቲካ ችግራችን ትልቁ መፍትሔ ይመስለኛል:: ለራሱ ሰብኣዊ ክብር ጥቅምና ነጻነት ቀናኢ የሆኑ ሁሉ ከልብ ሊታጠቁት የሚገባ እውነት ይመስለኛል:: ሞራላዊ ግባችንን ኢሞራላዊ በሆነ መንገድ ማሳካት ፈፅሞ ተገቢነት አይኖረውም:: የሰው ልጅ ትልቁን ሽልማትም ሆነ ቅጣት ከህሊናው ይቀበላል:: ለእኔ ሁልጊዜ ወደ ሞት አፋፍ ሲወርድ በሰዎች ላይ ስላደረኩት ክፋት ማድረግ ሲገባኝ ስላልፈፀምኩት ተግባር መጸጸት የሞት ሞት ይመስለኛል:: በመሆኑም ለሁላችንም በጎ በሆኑና በሚጠቅሙ ጉዳዮች ላይ መቆም ብሎም መታገል ተገቢ ነው::

## 12ኛ. ፍቅር እንዲያሸንፍ እንፍቀድለት

ዶ/ር ኪንግ፣ ኒቼ ፍቅርን አቅመቢስ እንደሆነ የቆጠረው ፍቅር ውስጥ ያለውን ኃይል ስለማያውቅ ነው፤ ይላሉ:: በግሌ ሰላማዊ ትግል ላይ የሙጥኝ ስል የፍቅር መንገድ ፍፁም የሆነ የግፍና የአንባገነንነት ማርከሻ መሆኑን በማመኔ ነው:: ከኃይል ሁሉ የበረታው ኃይል ፍቅር ውስጥ ያለው ነው:: ምንም እንኳን ዛሬ የኢትዮጵያ ሰላማዊ ትግል መንገድና ውጤት ከቁብ የሚፅፈው ያለ ባይመስልም ፣በፍቅር ዘመንጠገቡን የአገዛዝ ተራራ ለመናድ ፣ሳይገድሉ ለመሞት የቆረጡ ወጣቶቻችን የፈፀሙት ገድል ከሁሉ ለከበረው እውነት የተከፈለ መስዋዕትነት ነው:: ማናችንም በፍቅር ማሸነፍ እንደምንችል አሁን ያለንበት ዘመን እማኝነቱን ይሰጣል:: ዶ/ር ዐቢይ በፍቅር ብዙዎችን ትጥቅ አስፈትተዋል:: የጓድ መንግሥቱም ሆነ የአቶ መለስ አፈ ሙዝ መማረክ ያልቻለውን የኢትዮጵያውያንን ልብ ዝቅ ብለው በፍቅር እየማረኩ ይገኛሉ:: ትልቅ ማስተዋል ነው:: አሁንም ለፍቅር ተጨማሪ እድል አብዝተን ልንሰጠው ይገባል:: የምናጭደው ስኬት ዛላም እንዲሁ እጥፍ ድርብ ይሆናል::

## 13ኛ. የተስፋ ፅናት ይኑረን

ኢትዮጵያችን ሁሉም ነገር በጅምር የሚገኝባት ሀገር ነች:: የመጣነው መንገድ ቀላል ባይሆንም እራሳችንን ለእረፍት ለማዘጋጀት የሚበቃ ውጤት ላይ በአንዳንችንም ዘርፍ ላይ አልደረሰንም:: ይህ ሁኔታ ልብ ያዝላል፡፤ በመከራ ውስጥ ውጤት እንደሚገኝ ማመን የሰው ልጅ የትኛውንም የአገዛዝም ሆነ የችጋር ድቅድቅ የሚገፍ ኃይል የተሞላ መሆኑን ማመን ወሳኝ ነው:: በተስፋ ሙላትና በአይበገሬነት የተሞሉ ኢትዮጵያውያን በየዘመኑ የሰሩትን ማስታወስ በዚህ ዘመን ትልቅ ዋጋ ይኖረዋል:: በሰዎች ላይ በግፍ እስካልተነሳ ንድረስ የሚጨነግፍ ተስፋ አይኖርም:: አሁን ከመቼውም ጊዜ በላይ የተስፋ እጦትን በተስፋ ሙላት የምንተካበት ዘመን ነው::

ለዘመናት በጥይት ባሩድ የጠቆረው ሰማያችን የዴሞክራሲ ጠል እስኪያንጠባጥብ ድረስ በተስፋ ሙላት ልንታገል ይገባል:: ጥላቻና ዘረኝነት ያነፈራቸው የወገኖቻችን ልቦች ፍቅርና ወንድማማችነት እስኪያብቡባቸው ድረስ በተስፋ እንፀናለን:: በአሉታዊ ገፅታዋ የምትታወቀው ሀገራችን የዓለም ሀፍረት ሳይሆን የአለም ጌጥ እስክትባል ድረስ በተስፋ እንፀናለን:: አሁን የቆምንበት የነፃነት ብልጭታ ወደ ደማቅ የሕዝባዊ ልዕልና ንጋት እስኪለወጥ ተስፋን ተሞልተን ርዕያችንን ለመጨበጥ እንተጋለን::

ፍትህ እንደቀትር ፀሐይ፣ ፍቅር እንደ ሃይለኛ ጅረት ፣ወንድማማችነት እንደ አበባ ጉንጉን፣ በኢትዮጵያ ላይ ለዘመናት ይንገሥ!



ብሩክ መኮንን

# ከተማ ይፍሩ

## ፓንአፍሪቃዊው ዲፕሎማት

ከዛሬ ስድሳ ዓመት በፊት የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት እንዲመሠረት ጉልህ ድርሻን የተጫወቱትን ፓን አፍሪቃዊው ኢትዮጵያዊ ዲፕሎማት ከተማ ይፍሩን ሕይወትና ሥራ በዚህ እትማችን ለመዘከር ወደድን እነሆ፤

ከተማ ይፍሩ በቀድሞው የሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት በምስራቅ ሐረርጌ በጋራ ሙለታ አውራጃ በግብርና ሥራ ከሚተዳደር ቤተሰብ በሕዳር ወር በ1922 ነው የተወለዱት::

በተራራማው የጋራ ሙለታ ከተማ የተወለዱት ከተማ ይፍሩ በወቅቱ አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ውስጥ በማለፍ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በመከታተል አጠናቀቁ:: ወጣት ከተማ ይፍሩ በትምህርት አቀባበላቸው፣ ራሳቸውን ለማሻሻል፣ ለመለወጥ በሚያደርጉት ጥረትም ውጤታማ መሆናቸውን ተከትሎ በ19 ዓመታቸው በ1941 ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ አቀኑ::

በአሜሪካ ለስድስት ዓመታት የከፍተኛ ትምህርታቸውን ሲከታተሉ ቆዩ:: ብዙዎች በወቅቱ የነበረውን የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሣዊ አገዛዝ ያጠኑ ተመራማሪዎች፣ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት በወቅቱ በሀገሪቱ የዘመናዊ ትምህርትን ለማዳረስ ከሚያደርገው ጥረት በተጨማሪ ለሥርዓቱ ቅርብ የሆኑ የመሳፍንቱና የመኳንንቱ ቤተሰቦችና ልጆቻቸውን ብቻ ሳይሆን እንደነ ከተማ ይፍሩ ያሉ ደሀ የገበሬ ልጆችንም የከፍተኛ ትምህርት እንዲማሩ በማድረግ ፣ቀጣዮቹ የሀገሪቱ የመንግሥት ሹማምንት የሥራ መሪዎች እንዲሆኑ የሚያስችል ተግባር ለመከናወኑ ከተማ ይፍሩ ምሳሌ ናቸው፤ ይላሉ::



ለስድስት ዓመታት በአሜሪካ ከፍተኛ ትምህርታቸውን የተከታተሉት ከተማ ይፍሩ፣ ትምህርታቸውን ጨርሰው ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ በቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ፊት በመቅረብ ከሌሎች ከውጭ ሀገር የተመለሱ ኢትዮጵያውያን ጋራ ከንጉሠ ነገሥት መመሪያ ተቀበሉ::

ከ1944 እስከ 1950 ዓ.ም ድረስ በውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት የተለያዩ የሥራ ዘርፎች በኃላፊነት የሰሩት ከተማ ይፍሩ፤ ሰውን የማይንቁ ፣መወያየት መከራከር ፣የበታች ሠራተኞችን ያሳተፈ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት፣ ሁሉን አቀፍ ለውጥ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ለማምጣት የሚጣጣሩና ለፕሮቶኮል ደንታ የሌላቸው ታታሪ ሹም ነበሩ::

በዚህም የተነሳ ወደ ጽህፈት ሚኒስቴር በመዘዋወር ከረዳት ሚኒስቴርነት እስከ ሚኒስቴር ዴኤታነት በኋላም ላይ የንጉ ነገሥቱ ልዩ ጽህፈት ቤት ሹም በመሆን ለከፍተኛ ኃላፊነት ተመድበው አገልግለዋል::

የፓን አፍሪቃዊ ርዕዮት አቀንቃኝ ከተማ ይፍሩ፣ የዛሬ ስድሳ ዓመት የተባበሩት መንግስታት የአፍሪቃ ኢኮኖሚ ኮሚሽን እንዲቋቋምና መቀመጫውን በአዲስ አበባ ከተማ እንዲሆን ከፍተኛውን የዲፕሎማሲያዊ ትግል ካደረጉ ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቶች ውስጥ የአንበሳውን ድርሻ እንደሚወሰዱ በበርካቶች ዘንድ ይነገራል::

በ1960 ዓ.ም አብዛኛዎቹ የአፍሪቃ ሀገራት ነጻነታቸውን መቀዳጀታቸውን ተከትሎ በሀገሮች መካከል ፖለቲካዊ ውህደትን ለመፈጠር እንቅስቃሴዎች በመካሄድ ላይ ነበር::

በወቅቱ በጋናው ኩዋሜ ኑኩርማህ፣ በጊኒው መሐመድ ሴኩቲሪ፣ በማሊው ሚዲቦ ኬይታ መሪነት በሞኖሮቪያ ላይቤሪያ ውስጥ የተወሰኑ የአፍሪቃ ሀገራትን ያቀፈ እንቅስቃሴ በአንድ ወገን፤

በሞሮኮው ንጉሥ ሐሰን፣በግብፁ ከማል አብዱልናስር፣በአልጄሪያው ቤብቤን አሰባሳቢነት የተለያዩ ሀገራት የካዛካላካ ቡድን በሚል ስያሜ በሌላ ጎራ ተሰልፈው እንቅስቃሴ ይጀምራሉ::

በወቅቱ የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው ሀገራቸውን በማገልገል ላይ የነበሩት ከተማ ይፍሩ፣ ይህ የሁለት ወገኖች እሽቅድድምና ሽኩቻ ከፓንአፍሪቃኒዝም ርዕዮት ያፈነገጠ መሆኑን በመገንዘብ ፣አፍሪቃዊያን በአንድነት ለአህጉራዊ ብልፅግና ሰላም በጋራ እንዲሰሩ በዚህም ኢትዮጵያ የበኩልዋን ሚና እንድትጫወት የሚያስችል ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ ለማካሄድ ከንጉሠ ነገሥቱ ይሁንታ እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ::ንጉሠ ነገሥቱም የከተማ ይፍሩን ሐሳብ በመደገፍ እንዲቀጥሉበት ይፈቅዳሉ::

ከተማ ይፍሩ የሚመሩት የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስተር ባልደረቦች የተካተቱበት ቡድን በመላው አፍሪቃ ሀገራት በመዘዋወር ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ ማካሄድ ይጀምራል::

በዚህም ዘመቻ የፓን አፍሪቃ ኢትዮጵያዊ ዲፕሎማት ከተማ ይፍሩ የሚመራው የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን በሞርኖቪያው ሀገሮች መንግሥታት በጠሩት የሚኒስትሮች (የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች) ጉባኤ ላይ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በእንግድነት እንዲገኙ በማድረግ የቡድኑ የመሪዎች ቀጣይ ጉባኤ በአዲስ አበባ ከተማ እንዲካሄድ ጥያቄ አቀረበ::

ከተማ ይፍሩ ሀገራቸው የሞርኖቪያውን መሪዎች ጉባኤ እንዲያዘጋጅ በመመረጠዋ ጥያቄው ተቀባይነት በማግኘቱ ከፍተኛ ደስታ ቢሰማቸውም፣የካዛብላንካው ሀገራት ቡድን በካይሮ ሊያካሄደው ያቀደው ጉባኤ አፍሪቃዊውያንን ወደ ኅብረት ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሚፈጥረውን አሉታዊ ገፅታን ለማስወገድ የሚያስችል ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ ማካሄድ እንዳለባቸው አመኑ::

ስለዚህ ዲፕሎማሲያዊ ተልዕኮን እንዴት እንዳካሄዱት እንዳቀዱ አንድ ወቅት ተጠይቀው ክቡር አቶ ከተማ ይፍሩ በሰጡት ምላሽ "እንዲህ አይነቱ የተናጠል የሚደረጉ ስብሰባዎች ከቀጠሉ በአፍሪቃዊውያን መካከል ያለው ልዩነት እየሰፋ ስለሚሄድ ፣ይህ ከመሆኑ በፊት ኢትዮጵያ የራሷን ሚና ለመጫወት እንድትችል በካይሮው ስብሰባ ላይ የሚካፈሉት የጊኒው ርዕሰ ብሔር ሴኩቲሬ ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በኩል ጥሪ እንዲቀርብ መላ ተቀየሰ ::

የጊኒው ፕሬዝዳንት ሴኩተሬም ጥሪውን በመቀበል ኢትዮጵያን ለመጎብኘት ሲመጡ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ በኤርትራ የኢትዮጵያ ባህር ኃይል የምርቃት ስነ ስርዓት ስለነበሩ የጊኒው ፕሬዝዳንት አስመራ ሲገቡ የጋራ አቀባበል ተደረገላቸው::

በሁለቱ መሪዎች መካከል በተደረጉ ውይይቶችም የኢትዮጵያ ሐሳብ ተቀባይነትን አግኝቶ በጉብኝቱ መገባደጃ ላይ በሁለቱ ሀገሮች መካለል በተደረሰው ስምምነት መሰረትን ያደረገ የጋራ መግለጫ ወጣ:: በዚህም መሰረት በቀጣዩ አመት የሚደገው የሞርኖቪያ ቡድን ስብሰባ የመላ አፍሪቃዊ ስብሰባ እንዲሆን ሁለቱ መሪዎች የደረሱበትን ስምነትን ይፋ አደረጉ::

መግለጫው በያለበት ከመሰራጨቱም በተጨማሪ ፕሬዝዳንት ሴኩቱሬ የሚቀርቧቸው የሀገራት መሪዎችን በጉባኤው ላይ እንዲገኙ የማግባባት ሥራን እንዲሠሩ ቀሪውን ደግሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ለማሳመን ዘመቻ ለማድረግ ከስምምነት ላይ ተደረሰ::

ይህንንም ተከትሎ የጃንሆይን ልዩ መልዕክት የጥሪ ደብዳቤን በመያዝ እኔና ፀሐፊዬ አቶ አያሌው ማንደፍሮ በጋራ በመሆን ካይሮ፣ ትሪፖሊ፣ አልጀርስ፣ ራባት፣ ዳካር በአጠቃላይ ወደ ሃያ አምስት የሚጠጉ የአፍሪቃ ሀገራት በመዞር መሪዎቻቸውን በማናገር በአፍሪቃ ስም እየጠራን ለመንን፤ ከብዙ ደጅ ጥናት በኋላም ሁሉም ፈቃደኝነታቸውን በደብዳቤ አሳወቁን፤ በዚህም ልባችን በኩራት ተሞላ፤ ተስፋችን ለመለመ፣ ይህንን ታላቅ ብስራት ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሪፖርት አደረኩ፤ ግርማዊነታቸውን በጣም ተደሰቱ::

ጉባኤውን በአዲስ አበባ ለማካሄድ ዝግጅቱ በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ተጠናቆ ሰላሳ ሁለት ነፃ የአፍሪቃ መሪዎች ጉባኤውን ለመታደም ከፍተኛ ልዑካኖችን እየመሩ ወደ አዲ አበባ መጡ፤ በዚህም ጉባኤ የአፍሪቃ አንድነት ድርጅት ተመሰረተ፤ ቻርተሩም ተፈረመ::

# ግዮን መጽሔት

## በአጭር ጊዜ ገበያ ውስጥ ለመግባት የቻለችው ግዮን የእርስዎ መፅሔት

መጽሔታችን ከተጀመረች ጀምሮ የእናንተ ውድ አንባቢያን አቀባበልና አስተያየት ሳይለየን ቆይተናል። በአዲስ ዓመት በአዳዲስ አምዶች

**ትምህርት፡-** በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ ያሳያል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት ፍኖተ ካርታን በተመለከተና ከትምህርት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች

**ኢትዮጵያዊነት፡-** አገራችን የአንድነት ጉዞ በምትጀምርበት ወቅት ኢትዮጵያዊነት ምንድን ነው? በሚልና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በተከታታይ እናቀርባለን።

በእነዚህ አምዶች ላይ ባለሙያ የሆናችሁና የተለየ ሀሳብ አለን የምትሉ ተሳታፊዎች በኢሜል ፅሁፍ መላክ ትችላላችሁ።

በልዩ አቀራረብ፣ በአዳዲስ አምዶችና በሳል ፀሃፊያን በመታገዝ

## በየሳምንቱ ቅዳሜ ከእጅዎ ትደርሳለች።

ቢጨመር ፣ ቢሻሻል የሚሉትን ከወዲሁ ይጠቁሙን!






+251 911 227661
+251 912 165606
+251 118 122333

www.faceboook.com/enqu2013
Facebook
Gihon-meg Fekadu

ኢ-ሜይል፡
enqu2013@gmail.com
Ghion2011mag@gmail.com